# መሠረተ ሕይወት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልጆች መማሪያ መጽሐፍ

### አራተኛ ክፍል

አዘጋጅ - ቀሲስ ሰሎሞን መሉጌታ

www.zeorthodox.org

ነሐሴ
፳፻፰ ዓ.ም

© ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ ፳፻፩ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ሥርዓት እና ትውፊት መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት

አድራሻ፡-
ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ ዘውዴ
ፖ.ሳ.ቁ 43200
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- kesisolomon@gmail.com
Website፡- www.zeorthodox.org

www.zeorthodox.org

የኮምፒውተር ሌይ አውት ዲዛይን
ልደት አስፋው

# ምስጋና

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት የተሰለፉትን ዲ. ዘላለም ረድኤትና ዲ. ዮናታን ኢያሱን፣ መጽሐፉን በማረም የተባበሩትን መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብርን፣ መምህር ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔርን፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን፣ እና አቶ አስራት ከበደን እንዲሁም በኮምፒዩተር የለቀማ ሥራ ያገለገሉትን ልደት አስፋውን፤ መጻሕፍቱን ለማጠናቀቅ ሳደርግ በነበረው ጥረት ውድ ባለቤቴና ልጆቼ የእንቅልፍና የእረፍት ሰዓታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት በማድረግ ስላሳለፉ ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ዋጋ ከፋይ ነውና ዋጋቸውን ይክፈላቸው እላለሁ። በመጨረሻም የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያከናውኑ የመርሐ ግብራችን አስተባባሪ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሰንበቴ የሥራ አስፈጻሚ አባላትን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጠብቅልኝ ሳልል አላልፍም።

# መታሰቢያነቱ



በመልካምና በአስቸጋሪ ጊዜያት መንፈሳዊ ምክራቸው ሳልተለየኝ ለአባቴ ለአባ ይትባረክ ወልደ ሥላሴ ይሁንልኝ።

www.zeorthodox.org

# ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ተሰራጭቶ የሚገኘው ገቢ በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም፣ በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል፣ በቦሌ ሰሚት መካነ ሰላም መድኃኔዓለም እና ወደ ፊትም በተለያዩ አጥቢያዎች ለሚከናወኑ የሕፃናት፣ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ወላጆች ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚውል ይሆናል።

# ማውጫ


| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| | መቅድም | I | | | |
| | መግቢያ | III | | | |
| 1. | አዲስ ዓመት | 1 | | አንደኛ | |
| 2. | ለአዳም እና ሔዋን የተሰጠ ሥልጣን | 5 | | ሁለተኛ | |
| 3. | አቤል እና ቃየል | 7 | | ሦስተኛ | |
| 4. | አባታችን ኖኅ | 9 | | አራተኛ | |
| 5. | የቤተሰብን ጉድለት እንዴት ይያዛል? | 11 | | አምስተኛ | |
| 6. | አብርሃም የእምነት አባት | 13 | | ስድስተኛ | |
| 7. | ካህኑ መልከጼዴቅ እና አብርሃም | 15 | | ሰባተኛ | |
| 8. | ሙሴ | 17 | | ስምንተኛ | |
| 9. | የኤልያስ መሥዋዕት ዐረገ | 20 | | ዘጠነኛ | |
| 10. | የኢሳይያስ ራእይ | 23 | | ዐሥረኛ | |
| 11. | አቤሜሌክ ኤርምያስን ረዳ | 26 | | ዐሥራ አንደኛ | |
| 12. | የሠለስቱ ደቂቅና የዳንኤል ጾም | 28 | | ዐሥራ ሁለተኛ | |
| 13. | ዳንኤል የንጉሡን ሕልም ተረጎመ | 32 | | ዐሥራ ሦስተኛ | |
| 14. | ነህምያ /አንድ/ | 35 | | ዐሥራ አራተኛ | |
| 15. | ነህምያ /ሁለት/ | 39 | | ዐሥራ አምስተኛ | |
| 16. | ሕፃኑን እና እናቱን ይዘህ ሽሽ | 42 | | ዐሥራ ስድስተኛ | |
| 17. | የምሥራቹ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል | 45 | | ዐሥራ ሰባተኛ | |
| 18. | ቅዱስ ኒቆላዎስ | 47 | | ዐሥራ ስምንተኛ | |
| 19. | እግዚአብሔርን መፍራት | 51 | | ዐሥራ ዘጠነኛ | |
| 20. | ቅዱስ ጊዮርጊስ | 54 | | ሃያኛ | |
| 21. | ሐዋርያት ተከተሉት | 56 | | ሃያ አንደኛ | |
| 22. | እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም | 58 | | ሃያ ሁለተኛ | |
| 23. | ፊሊጶስ ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው | 60 | | ሃያ ሦስተኛ | |
| 24. | የሳውል መመለስ | 62 | | ሃያ አራተኛ | |
| 25. | ፍቅር የሕግ ፍጻሜ | 64 | | ሃያ አምስተኛ | |
| 26. | ቅዱስ ፖሊካርፐስ | 67 | | ሃያ ስድስተኛ | |
| 27. | ታማኝ አገልጋይ | 70 | | ሃያ ሰባተኛ | |
| 28. | ኒቆዲሞስ | 73 | | ሃያ ስምንተኛ | |
| 29. | ሆሣዕና | 75 | | ሃያ ዘጠነኛ | |
| 30. | የክርስቶስ ትንሣኤ | 77 | | ሠላሳኛ | |


www.zeorthodox.org

| ተ.ቁ. | አርእስት | ገጽ | ወር | ሳምንት | ልዩ በዓል |
|---|---|---|---|---|---|
| 31. | ሊቀ ቅዱስ ያሬድ | 80 | | ሠላሳ አንደኛ | |
| 32. | ኅብስተ ሕይወት | 83 | | ሠላሳ ሁለተኛ | |
| 33. | ልደታ ለማርያም | 86 | | ሠላሳ ሦስተኛ | |
| 34. | ዕርገት | 88 | | ሠላሳ አራተኛ | |
| 35. | ለሌሎች መልካም አርአያ መሆን | 90 | | ሠላሳ አምስተኛ | |
| 36. | ቅዱስ ላሊበላ | 93 | | ሠላሳ ስድስተኛ | |
| 37. | ማመስገን | 98 | | ሠላሳ ሰባተኛ | |
| 38. | የቤተክርስቲያን ትርጉም | 101 | | ሠላሳ ስምንተኛ | |
| 39. | የቤተክርስቲያን ባሕርያት | 103 | | ሠላሳ ዘጠነኛ | |
| 40. | በዓለ ጰራቅሊጦስ | 107 | | ዐርባኛ | |
| 41. | ዘመነ ሐዋርያት | 109 | | ዐርባ አንደኛ | |
| 42. | ቤተክርስቲያን የሆነው የጣዖት ቤት | 112 | | ዐርባ ሁለተኛ | |
| 43. | ሃይማኖት /መግቢያ/ | 114 | | ዐርባ ሦስተኛ | |
| 44. | ሃይማኖት/ሁለት/ | 117 | | ዐርባ አራተኛ | |
| 45. | ስለ እግዚብሔር ኀልውና የሚያስረዱን | 120 | | ዐርባ አምስተኛ | |
| 46. | የእግዚአብሔር ባሕርይ | 122 | | ዐርባ ስድስተኛ | |
| 47. | የቃል ኪዳኑ ታቦት | 126 | | ዐርባ ሰባተኛ | |
| 48. | አስማተ እግዚአብሔር | 129 | | ዐርባ ስምንተኛ | |
| 49. | ቅድስት ሥላሴ | 132 | | ዐርባ ዘጠነኛ | |
| 50. | ጾመ ፍልሰታ | 135 | | ሃምሳኛ | |


www.zeorthodox.org

# መቅድም

በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች ቤተ ክርስቲያናቸውን እያወቁ በመልካም ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚያደርግ፣ ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ብሎም ችግሮቻቸውን የሚፈታ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት የመኖሩ አስፈላጊነት በብዙዎቻችን ዘንድ ይታመንበታል። ቤተ ክርስቲያናችንም በዚሁ ዙሪያ በርካታ ተግባራትን እንደምታከናውን እምነቴ ነው።

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክ ለተስተካከለ ዕድገታቸው አስተዋጽዖ በማድረግ የወላጅነት ሓላፊነታቸውን ለመወጣት ፍላጐቱ አላቸው። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቻቸት የተነሣም ይሁን በሌላ ምክንያት ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እንዲማሩላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ ምእመናን እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች ማሳያዎች ሆነውኛል።

ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት በእግዚአብሔር ፈቃድ በምሠራበት መሥሪያ ቤት በኩል ለተዘጋጀ ሙያዊ ሥልጠና ከአገር ውጪ ባደረግሁት ጉዞ ዘወትር አብረውኝ የሚቆሙ ቤተሰቦቼ ምክንያት ሆነው ግብጽንና ገዳማቱን የመጐብኘት ዕድል አገኘሁ። ይህም የተቀደሰ አጋጣሚ ስለ ልጆች፣ በቅድመ ጋብቻ ስላሉ ወጣቶችና በትዳር ስለሚኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን የተናጠል መርሐ ግብር እንዳስብ አደረገኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድም በኅዳር ወር ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቀ ዮሐንስና አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን የልጆች መርሐ ግብር በሃያ አራት ልጆች ተጀመረ። አሁን ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሆኑ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ልጆች፤ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ቀን ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጠውን መንፈሳዊ ትምህርት ይከታተላሉ። በርካታ ምእመናንም በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ አሥራ ሁለት እስከ ሁለት ሰዓት ለአዋቂዎች በተዘጋጀው የትምህርት መርሐ ግብር ተሳታፊዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ ሁሉንም ልጆች በየትምህርት ደረጃቸው በመመደብ ማስተማር የሚያስችል መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም ቀድመው የተዘጋጁትን ትምህርቶች ተካተውበት ለዚሁ ሥራ እገዛ የሚያደርጉ ወንድሞች ጋር በመመካከር ዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ዲያቆን ዘላለም ረድኤት ተገኝተውበት ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ጥረት ተጀመረ። እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ከአራት ዓመታት ጥረት በኋላ፤ ለሥርዓተ ትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ በኋላ አጋዥ የሆኑ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ የሆኑ አሥራ ሦስት ጥራዝ የማስተማርያ መጻሕፍት ዝግጅት ተጠናቅቆ ለኅትመት እንዲበቁ ለማድረግ ወደ ማተሚያ ቤት ገብተዋል።

www.zeorthodox.org

በማስተማርያ መጻሕፍቱ ዝግጅት፤ ለመረጃ የምንገለገልባቸው ምንጮች፣ የምእመናን የኑሮና የትምህርት ደረጃ፣ የመኖሪያ ሥፍራዎችና የባህል ልዩነቶች፣ እንዲሁም በአገር ውስጥ እና ከሀገር ዉጪ በሚገኙ ኢትዮጵያዊያን መካከል ያሉ የአኗኗርና የሥራ ሁኔታዎችና አካባቢያዊ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገቡ ተሞክሮአል። በዚህ ሥራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላደረጉት ለዲያቆን ዮናታን ኢያሱ እና ለዲያቆን ዘላለም ረድኤት፤ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን እላለሁ።

ይኸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሙዓለ ሕፃናት እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ላሉ ወጣቶች ለሚሰጠዉ ‹‹መሠረተ ሕይወት›› መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ መጻሕፍት ለኅትመት በቅተዉ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ እገልጻለሁ።

***"እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል።" ፩ኛ ሳሙኤል ፯ ፥ ፲፪***

www.zeorthodox.org

# መግቢያ

የዚህ መንፈሳዊ ሥርዓተ ትምህርት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ትውፊተ ቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ጥርት ያለውን የቅድስት ቤተ ክርስቲንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ታሪክ ከመልካም ሥነ ምግባር ጋር፤ በዓለማዊ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ሕፃናት፣ አዳጊዎችና ወጣቶች እንዲደርስ ለማድረግ፤ በየትምህርት ደረጃቸው እና ዕድሜአቸው እንዲመጥን ሆኖ የሥርዓተ ትምህርት አዘገጃጀትን ስልት በመከተል ለማዘጋጀት ተሞክሮአል፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ልጆች ትምህርቱን በሚገባ ተረድተዉ ማስታወስ እንዲችሉ በየደረጃዉ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በድጋሚ ተካትተዋል፡፡

ትምህርቶቹ በየወሩ ተከፋፍለው በቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላትም ጋር እየተቀራረቡ እንዲዘጋጁ ጥረት ተደርጎአል፡፡ በየመካከሉ ለሚኖሩ ክፍተቶች በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል አገልግሎት ላይ እንዲውል ሆኖ የማሟያ ትምህርቶቹ ተወስደው ተካትተዋል፡፡ ያም ሆኖ እንደየ ጊዜው ሁኔታ ዘመኑን እንዲዋጅ መሻሻልና መዳበር ያለበት መሆኑ ግን የማይዘነጋ ነው፡፡

በሙዓለ ሕፃናት የሚገኙ ልጆች በጣም አጫጭር ታሪኮችን ብቻ ሰምተው ጥቂቶቹን ብቻ ማስታወስ የሚችሉ ናቸው፡፡ ረጅም ጽሑፍና ሐሳብ በትኩረት አንብበዉ በቀላሉ ለመረዳትም ሆነ ለማስታወስ ስለማይችሉ ወይም ስለሚቸገሩ በመምህራን እንዲሁም በወላጆች መታገዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተረት፣ በታሪክ፣ በሕልምና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት አገናዝቦ ለመረዳት ይቸገራሉ፡፡ በጣም ፈጠራ የታከለባቸው የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች የሚያስፈልጓቸው ቢሆኑም መምህራ ኖቻቸው የሚዘምሩላቸዉን መዝሙሮች ማስታወስና በአእምሮአቸው መያዝ፣ በትምህርታዊ ጨዋታዎቻቸውም ሆነ በማንኛውም ሁኔታ መምሰልና ማስመሰል ይችላሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የሚንቀሳቀሱና የተለያዩ ድምፆች ያሉባቸውን ነገሮች እንዲሁም ከሌሎች ጋር መጫወትንና ያዩትን በተግባር ማሳየትን ይወዳሉ፡፡

www.zeorthodox.org

ልጆች ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸው ደስታን እንዲፈጥርላቸውና ፈጽመውም የሚወደዱ መሆናቸውን እንዲሰማቸው ማድረግ እንጂ ቶሎ ሊያስደነግጣቸው ወደ ሚችል አቀራረብና ቅጣት ማዘንበል አይገባም፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ልጆችን የሚያስተምሩ መምህራን በተፈጥሮ ለልጆች ፍቅር ያላቸውና ፍቅራቸውንም መግለጽ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የሚጠበቁ መልካም ውጤቶችም በሚቀርቡላቸው መርጃዎችና በመምህራኑ ጥረት ላይ የተመረኮዙ ናቸው፡፡ መምህራኑ ልጆችን ለመሳብ ብሩህ ፈገግታና ፍቅር ያለው አቀራረብ እንዲሁም፤ ደመቅ ያሉ ቀለማትን፣

ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ቢጠቀሙ መዝሙራትንም ቢያዘምሩላቸው ለትምህርቱ ታላቅ ኃይል ይሆናል፡፡ ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መምህራን ልጆቹን በየዕለቱ የትምህርት መርሐ ግብሮች መዝሙራትን ሊዘምሩላቸውና ሊያስጠኑአቸው ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሥዕላትን ቢያሳዩአቸዉ፣ ቢሰጡአቸው የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታወስና ለሌሎችም ለማስረዳት የበለጠ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ልጆች ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ ይህንኑ ለማገዝም በቀለም የሚቀቡ ሥዕሎችና የመዝሙር ጥራዞችን ዝግጅት አጠናቀናል፡፡ በሙዓለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ልጆች ከትምህርታቸዉ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርእሰ ጉዳይ ሥዕሉን ቀለም በመቀባት የሚቀስሙት ትምህርት የበለጠ ስለሚሆን የተዘጋጁትን ሥዕሎች በአግባቡ ቀለም እንዲቀቡአቸው የወላጆች እገዛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በዓመቱ ውስጥ ባልተካተቱት ሁለት ሳምንታትም ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን መጐብኘታቸውና ክትትል ባለበት ሁኔታ በማኅበራዊ ነገሮች ተሳታፊ መሆናቸውም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን መምህራን ለዚህ አገልግሎት በትጋት መጸለይና በየመካከሉ የሚቀሩ ወይም ጨርሰው ያልመጡ ልጆችንም መጐብኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራንን ማግኘት በማይቻልባቸው ሥፍራዎች ወላጆች በሥርዓተ ትምህርቱ በመመራት ልጆችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊው ትምህርት እስከአሁን ድረስ ያደጉበት ሁኔታ ያልተመጣጠነ ስለሆነ የክፍል ደረጃቸው ከፍ ቢልም ከሙዓለ ሕፃናት መጽሐፍ ደረጃ ጀምረው መማራቸው ለመንፈሳዊዉ ዕዉቀታቸዉ መሠረት ስለሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተከፈቱ ትምህርት ቤቶችም ይህንን ሥርዓተ ትምህርት መጠቀማቸው ልጆች በየደረጃው ቤተ ክርስቲያናችንን እያወቁ፣ ሃይማኖታቸውን ተረድተውና በበጐ ሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይኽን ዝግጅት የበለጠ ለማሻሻል የሁሉም አስተያየትና ምክር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እገዛችሁ እንዳይለየኝ እያልኩ አስቀድሞ በተጠቀሱት አድራሻዎች አስተያየቶቻችሁን እንድትልኩልኝ ስል በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

www.zeorthodox.org

# አዲስ ዓመት

## አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** በትምህርቱ መጨረሻ አዲስ ዓመት ምን ማለት እንደሆነ ለይተው ይረዳሉ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ፡፡"*** መዝ. ፷፬ (፷፭) ፥ ፲፩፡፡

**ምንባባት፡-** የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፡፡

### መግቢያ

ልጆች እንኳን ከዘመን ዘምን አሸጋገራችሁ፡፡ የኢትዮጵያውያን አዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን፡- ዘመን መለወጫ ፣ ዐውደ ዓመት ፣ እንቁጣጣሽ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ… በሚባሉ መጠሪያዎች ይታወቃል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ አዲስ ዓመት እንማራለን፡፡

**የመግቢያ ጥያቄዎች**

1. ዓመትን አዲስ የሚያደርገው ምንድነው?
2. ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስ፣ ዘመነ ዮሐንስ ሲባል ሰምታችኋል? ለምን የተሰጠ ስያሜ ነው?
3. የአዲስ አመት አቀባበልና አከባበር እንዴት መሆን ያለበት ይመስላችኋል?

## የሳምንቱ ትምህርት

ርእሰ ዐውደ ዓመት (አዲስ ዓመት) መንፈሳዊና ብሔራዊ አከባበር ያለው በዓል ነው፡፡ የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ቀን በተለያዩ ስያሜዎችም ይጠራል፡፡ ከነዚህም መካከል ዘመን መለወጫ፣አዲስ ዓመት፣ እንቁጣጣሽ፣ዐውደ ዓመት በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ይህ ቀን አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዘመን መተካቱን በማብሰር ይከበራል፡፡ ዘመን አዲስ የሚሆነው ጉድለትን በማረም ራሳችንን ከማሻሻል ጋር ስናከብረው ነው፡፡

www.zeorthodox.org

የተፈጥሮን ዑደት ተከትሎ የሚጀመረው የሀገራችን ዘመን አቆጣጠር 365 ¼ ቀናትና 13 ወራት አሉት፡፡ ዑደትም ምድር በፀሐይ ዙሪያ የምታደርገው መዞር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ***13 ወራትን በመያዙና በመስከረም በመጀመሩ*** ከምዕራባዉያን (ጎርጎሮሳዉያን) የዘመን አቆጣጠር ይለያል፡፡

## መሠረተ ሕይወት አራተኛ ክፍል

የአዉሮጳዉያን አቆጣጠር አንድ ዓመት 12 ወራት አሉት፡፡ የዘመን አቆጣጠራቸው በ1582 ዓ.ም እንደገና በቀመረው የሮም ፖፕ ጎርጎርዮስ ስም ጎርጎርሳዊ ይባላል፡፡ ከወራት ስያሜዎቻችን እንደምንረዳዉ የእኛ ዘመን አቆጣጠር የተፈጥሮን ሂደት መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መምህር ስያሜዎቹ ከግብርናና ከተፈጥሮ ሂደት ጋር ያላቸውን አንድነት በተጨማሪ ምንባብ በተጠቀሱት መጻሕፍት ዋቢነት ያብራሩላቸው፡፡

| ስያሜው | ትርጉሙ | | የቀናት ብዛት |
|---|---|---|---|
| መስከረም September | ከረመ ፣ ከክረምት በኊላ | | 30 ቀናት |
| | ሰባተኛ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| ጥቅምት October | ጠቀመ ጥቅም ፍሬ ያለው ወር | | 30 ቀናት |
| | ስምንት ማለት ነው፡፡ | | 31 ቀናት |
| ኅዳር November | ኀደረ አደረ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | ዘጠኝ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| ታሕሣስ December | ኀሠሠ ፈለገ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | አሥር ማለት ነው፡፡ | | 31 ቀናት |
| ጥር January | ጠርየጥሪት ያዘ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | ጃኑስ ከሚባለው የጣዖት ስም የተወሰደ ስያሜ ነው፡፡ | | 31 ቀናት |
| የካቲት February | ከተተ ሰበሰበ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | መዘጋጀት ማለት ነው፡፡ | | 28 ወይም 29 ቀናት |
| መጋቢት March | መገበ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | የጦርነት አምላክ በሚባለው ጣዖት በማርስ የተሰየመ ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| ሚያዝያ April | መሐዘ ፣ ምዕዘ፡- ተጎዳኘ ፣ መልካም መዓዛ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | አፍሮዳይት በሚባለው የፍቅር ጣዖት ስም የተሰየመ ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| ግንቦት May | ገነባ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | ማርያ በተባለች የሴት ጣዖት ስም የተሰየመ ነው፡፡ | | 31 ቀናት |
| ሰኔ June | ሰነየ ዐመረ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | የጋብቻ አምላክ በሚባለው ጣዖት ስም ተሰይሞል፡፡ | | 30 ቀናት |
| ሐምሌ July | ሐምለ፡- ለመለመ ማለት ነው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | በ16ኛ መክዘ የአውሮፓውያን አቆጣጠር እንደገና ባስቀመረው ጁሊየስ ቄሳር መታሰቢያ ተሰየመ፡፡ | | 31 ቀናት |
| ነሐሴ August | ነሐሰ ሠራ የሚል ትርጉም አለው፡፡ | | 30 ቀናት |
| | አውግስጦስ ለሚለው የሮም ነገሥታት መታሰቢያ የተሰጠ ነው፡፡ | | 31 ቀናት |
| ጳጉሜን | ትርፍ ማለት ነው፡፡ | | 5 እና 6 ቀናት |

www.zeorthodox.org

በጥንት ዘመን ሮማውያንና አይሁድ አዲስ ዓመት የሚያከብሩት በመጋቢትም መቁጠር ጀምረው በሰባተኛው ወር ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሴፕቴምበር - ሰባተኛ ተብሎል፡፡ የኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በመስከረምአቆጣጠር ወር ሲጀምር የአዉሮጳዉያን በእኛ አቆጣጠር ታኅሣስ 23 በእነሱ አቆጣጠር ጃንዋሪ 1 ይጀምራል፡፡

ጳጉሜን አምስት ቀናት ያሉዋት ወር ስትሆን በየ አራት ዓመቱ አንዴ ስድስት ቀናት ትሆናለች፡፡ የዚህ ምክንያቱም የሚከተለው ነው፡፡ ምድር በፀሐይ ዙርያ ለመዞር 365 1/4ኛ ቀናት ወይም 365 ቀንና 6 ሰዓታት ይፈጅባታል፡፡ ስድስቱ ሰዓታት በአራት ዓመት 24 ሰዓታት ወይም አንድ ቀን ይሆናሉ፡፡ በምዕራባውያን አቆጣጠር ይህንን በአራት ዓመት የሚሞላ ቀን ለማምጣት የወራትን ቁጥር በመቀነስና ቀናትን ደግሞ በመጨመርና በመቀነስ ሊያሟሉት ሞክረዋል፡፡ ወራቶቻቸው 12 ቀናቶቻቸውም 28፣ 29፣ 30 እና 31 የሆኑት ለዚህ ነው፡፡ የእኛ አቆጣጠር ግን ትርፎቹን ቀናት በጳጉሜን ወር በማካተት በአራት ዓመት አንዴ ስድስተኛዋን ቀን ያመጣል፡፡

በእኛ ዘመን አቆጣጠር እያንዳንዱ ዘመን በወንጌላውያን ተሰይሟል፡፡ እነርሱም፡- ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስ እና ዘመነ ዮሐንስ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የዘመናት ስያሜና አቆጣጠር ከአምስት ሺሕ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የዓመቱን መጀመሪያ መስከረም 1 ቀን እናከብራለን፡፡

## አዲስ ዓመትን ለምን እናከብራለን?

**እግዚአብሔርን ለማመስገን፡-** የጊዜያት አስገኚና ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ዘመናትን እያፈራረቀ አዲሱን ዘመን ስለመረቀልን ለማመስገን እናከብራለን፡፡

**በአዲስ መንፈስ ቀጣዩን ጊዜ ለመጀመር፡-** በመጸለይ መልካሙን ሁሉ ለመመኘት፣ ለማቀድና ለመዘጋጀትም የአዲሱን ዓመት መጀመሪያ ማክበር ይጠቅማል፡፡

www.zeorthodox.org

## አዲስ ዓመት እንዴት ይከበራል ?

**በምሥጋና፡-** በየዓመቱ መስከረም 1 ከዋዜማዉ ጀምሮ ዘመናትን ለሚያፈራርቀው ለእግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችን የምሥጋና መሥዋዕት ይቀርባል፡፡ ምዕመናንም፡- በማስቀደስ፣ በመዘመር፣ ቃለ እግዚአብሔርንና አዋጁን በመስማት ይሳተፋሉ፡፡

**ወንጌል ይነበባል፡-** እግዚአብሔር የዘመናት ባለቤት መሆኑን የሚያበስሩና የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይነበባሉ፡፡ ለምሳሌ፡-መዝ. ፷፬ (፷፭) ፥ ፲፩ ፣ ሉቃ. ፬ ፥ ፲፮...

**የዓመቱ በዓላትና አጽዋማት ይታወቃሉ፡-** በዕለቱ በካህኑ አማካይነት፣ በአዲሱ ዓመት የሚዉሉት በዓላት (ለምሳሌ ትንሣኤ)፤ አጽዋማትም መቼ እንደሚገቡና እንደሚወጡ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ዐቢይ ጾምና ጾመ ሐዋርያት መቼ እንደሚጀመሩ የሚታወጀው በመስከረም አንድ ነው ፡፡

**በባሕላዊ መንገድም፡-** ባሕላዊ ልብስ በመልበስ፣ ችቦ በማብራት፣ድፎ ዳቦ በመጋገር፣ ስጦታ በመለዋወጥ ይከበራል፡፡ በሌላ በኩል ሕፃናት መልካም ምኞታቸዉን መዝሙር በመዘመር፣ ሥዕል በመሣል ለቤተሰብና ለጎረቤታቸዉ ሲሠጡ፤ አዋቂዎችም ለልጆች የሚገባ ስጦታ ይሠጣሉ፡፡ ጳጕሜን ጸበል የሚጠመቁበት፣ ከዝናቡም እንጥብጣቢ የሚርሱበት አሉ፡፡ ይህም ከሌላ ባዕድ አምልኮ ጋር እስካልተገናኘ ድረስ በክርስትናው አይከለከልም፡፡

## ማጠቃለያ

- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በምድራችን ካሉ ጥንታዊ የዘመን አቆጣጠሮች አንዱ ነው፡፡ አሁን ያለው የአውሮፓውያን አቆጣጠርም በ16ኛው መ/ክ/ዘ የተከለሰ ነው፡፡
- የእኛ አንድ ዓመት 13 ወራት ሲኖሩት የአውሮፓውያኑ 12 ወራት አሉት፤ ሆኖም አጠቃላይ የዓመቱ ቀናት ብዛት ግን አንድ ነው፡፡
- አዲስ ዓመት ብሔራዊና መንፈሳዊ በዓላችን ነው፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን ለሀገሪቱ ካበረከተቻቸው ስጦታዎች አንዱ ነው፡፡
- መስከረም አንድ የሚጀመረው የዘመን አቆጣጠር ርእሰ ዐውደ ዓመት ተብሎ ይከበራል፡፡ በተጨማሪም የዘመን መለወጫ ቀናችን አዲስ ዓመት፣ እንቁጣጣሽ፣ ዐወደ ዓመት የሚባሉ ስያሜዎችም አሉት፡፡
- አዲስ ዓመትን የምናከብረዉ የዘመናት ባለቤትና የስጦታ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን በማመስገን፣ ለመጪው ዘመን በመዘጋጀት እና መልካም ምኞታችንን በመግለጥ ነው፡፡ አዲስ ዓመት በሃይማኖታዊና ባሕላዊ መንገዶች ይከበራል፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

- ከአዲሱ ዓመት ዋዜማ ጀምሮ ትምህርታችሁን፣ የቤተሰቦቻችሁን እና የአገራችሁን እቅድ እግዚአብሔር እንዲባርክላችሁ ጸልዩ፡፡
- የሚከተለዉን መዝሙር አጥንታችሁ ለወላጆቻችሁ ዘምሩ፡፡

**መዝሙር**

ዐውደ ዓመት ለባርኮ (2)

ንዒ ማርያም(3) ለምሕረት ወሣህል

# ለአዳም እና ሔዋን የተሰጠ ሥልጣን

## ሁለተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስላለው ፍቅርና ክብር መግለጽ።

**ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ። "*** ዘፍጥ. ፩፥፳፮

**ምንባብ፡-** ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ እና ፪።

### መግቢያ

ልጆች ከዚህ በፊት ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ሃይማኖት ስንማር እግዚአብሔር ፈጣያችን እንደሆነ እና እንደሚወደንም ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም ይህንኑ የሚያስረዳ ከሆነው የትምህርት አካል ክፍል አንድን እንማራለን።

### የሳምንቱ ትምህርት

1. **እጅግ መልካም የሆነው የሰው ተፈጥሮ**

የሰው ልጅ ሁሉም ፍጥረታት ከተፈጠሩ በኋላ፣ በእግዚአብሔር እጅ ፣በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌም ተፈጠረ፤ በአፉም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር ሆነ። ወንድ እና ሴትም አድርጎም ፈጠራቸው። ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ***እጅግ መልካም*** ነበር። ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፮ - ፳፯።

2. **ሥልጣንን ሰጣቸው**

የሰው ወዳጅ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር በመፍጠር ብቻ አልገለጸውም። ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ላይም ሾመው እንጂ። ***" እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።"*** ዘፍጥ. ፩፥፳፰።

3. **ምግብ ሰጣቸው**

***" እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ፥ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ"*** ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፱

www.zeorthodox.org

## 4. አንድ ነገር ብቻ ከለከላቸው

አዳም በገነት በነበረበት ጊዜ ሁሉ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔርም ከአዳም ጋር ይነጋገሩ ነበር፡፡ እግዚአብሔር አዳምን ‹‹በገነት ውስጥ ያሉትን ሁሉ እፅዋት መብላት ትችላልህ ግን ከእዚህ መብላት አትችልም፡፡›› አለው፤ አዳምም ይህንኑ አውቆ ሁሉንም የዛፍ ፍሬዎች ሲበላ ተው የተባለውን ግን አልበላም ነበር፡፡

## 5. ወንድና ሴት አደረጋቸው

አዳም በገነት ውስጥ ብቻውን ነበር፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሁሉንም እንስሳት ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ሁሉም እንደሚታዘዙት አያቸው፡፡ እንስሳትም በአንድነት ይጫወቱ ነበር፡፡ አይጥ ከድመት ጋር የበግ ግልገል ከነብር ጋር ዝሆን ከአህያ ጋር ይጫወታሉ፡፡

እግዚአብሔርም አዳምን ***"ለእንስሳቱ በሙሉ ስም አውጣላቸው"*** አለው፡፡ ከዚያም አዳም ውሻ፣ ድመት፣ አንበሳ... እያለ ለሁሉም ስም አወጣላቸው፡፡ አዳምም እግዚአብሔርን አመሰገነ፡፡

ሁሉም እንስሳት በየወገናቸው ሲጫወቱ አዳም ግን ብቻውን ነበር፡፡ እርሱን የሚመስል ሰው አልነበረም፤ እግዚአብሔርም አዳም ብቻውን እንደሆነ አየ፡፡ አዳም ብቻውን ይኖር ስለ ነበር ብቸኝነቱን አይቶ ሔዋንን ከአዳም ጎን ፈጠራት፤ አዳም እና ሔዋንም በገነት በአንድ ላይ ይኖሩ ነበር፡፡ እግዚአብሔር **ወንድ እና ሴት አድርጎ የፈጠራቸውን አዳምና ሔዋንን ነገሥታት ሆነው ሁሉንም እንዲያዙና እንዲገዙም** ፈቀደላቸው፡፡

## ማጠቃለያ

- እግዚአብሔር ለአዳም እንስሳቱ ሁሉ እንዲገዙለትና እንዲታዘዙት አደረገ፡፡ በጣም አስፈሪዎቹ እንስሳትም ሁሉ ከአዳም ጋር በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡
- አዳምም ሁሉንም እንስሳት ይወዳቸዉ ይንከባከባቸውም ነበር፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

- ልክ እንደ አዳም የቤትም ሆነ የዱር እንስሳትን ተንከባከቡ፡፡
- እግዚአብሔር ከፈጠራቸው እንስሳት የምትወዱትን እንስሳ ሥዕል ሳሉ፡፡

***<u>መዝሙር:-</u>***

| | |
|---|---|
| ኩሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር | እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ አደረገ |
| በሰማይኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ | በሰማይ እና በምድር በባሕርም |
| ወበኩሉ <u>ቀላያት (4)</u> | ሁሉም ባሕሮችም |
| | *መዝ. ፻፴፭ ፥ ፮- ፱* |

# አቤል እና ቃየን

## ሦስተኛ ሳምንት

***የትምህርቱ ዓላማ፡-*** *የአቤል እና ቃየን ሕይወት እንዴት እንደሆነ መግለጽ፡፡*

***የሚጠና ጥቅስ፡-*** ***"አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፥ በዚህም ፥ እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር፥ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት ፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።"*** ዕብ. ፲፩ ፥ ፬

***ተጨማሪ ምንባብ፡-*** ዘፍጥ.፬ ፥ ፩ - ፲፯

## መግቢያ

ልጆች አዳምና ሔዋን በገነት ሲኖሩ ስለ ተሰጣቸውን ሥልጣን ተምረናል፡፡ ሆኖም ከጥቂት ዘመናት በኋላ ግን አትብሉ የተባሉትን በልተው ወደ ዚህ ምድር ወረዱ፤ ልጆችንም ወለዱ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የመጀመሪያዎቹ ሰዎች የአዳም እና ሔዋን ልጆች ስለሆኑት ስለ ስለ አቤል እና ቃየን ታሪክ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ቃየን የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን አቤል ሁለተኛ ልጅ ነበር፡፡ ሁለቱም አድገው የየራሳቸውን ሥራ መሥራት ጀመሩ፡፡ አቤል በግ ጠባቂ፣ ቃየን ምድር የሚያርስ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ለብዙ ጊዜ ኖሩ፡፡

አንድ ቀን ሁለቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ፡፡ አቤል ከበጎቹ የተሻለውንና ንጹሑን መርጦ አቀረበ፡፡ ቃየንም ከምድር ፍሬ ያገኘውን ሁሉ ሰብስቦ አቀረበ፡፡ እግዚአብሔር ወደ አቤልና መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ቃየንንና መሥዋዕቱን ግን አልተቀበለም፡፡

www.zeorthodox.org

ቃየን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በወንድሙ ቀንቶ ሊገድለው ይጠባበቅ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም የቃየንን ልብ አውቆ ወንድሙን በመግደል እንዳይሳሳት አስጠነቀቀው፤ ***"ፊትህ ለምን ጠቆረ ፣ መልካም ብታደርግ የሚበራ አይደለምን፡፡ ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋ ወደ አንተ ነው፡፡ እወቅባት"*** ቢለውም ቃየን ግን አልሰማም፡፡ ሁለቱም ብቻቸውን በሆኑበት አንድ ቀን ቃየን ወንድሙን አቤልን ወደ ሜዳ እንሂድ አለው፡፡ አቤልም እሺ ብሎ ከወንድሙ ጋር ብቻቸውን ሄዱ፡፡ ቃየንም ድንጋይ አንስቶ አቤልን በድንጋይ ገደለው፡፡

ምንም እንዳላደረገ ሰው ወደ ቤቱ ተመልሶ መጣ፡፡ እግዚአብሔርም ‹‹*ወንድምህ አቤል የት አለ?*›› አለው፡፡ እርሱም ‹‹*እኔ የወንድሜ ጠባቂው ነኝን?*›› አለ፡፡ እግዚአብሔርም ‹‹የወንድምህ ደም ይጮኻል፡፡ እነሆ የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች ምድር አንተ የተረገምህ ነህ ፣ ምድርም ፍሬዋን አትሰጥህም አለው፡፡›› ቃየንም ‹‹ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት፥ ያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል፡፡›› አለ፡፡ እግዚአብሔርም ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረለት፡፡ በምድር ላይም ተቅበዝባዥ ሆኖ ኖረ፡፡

## ማጠቃለያ

ቃየንና አቤል ወንድማማቾች ሆነው በእረኝነትና ምድርን በማረስ ይኖሩ ነበር፡፡ መሥዋዕት ሲያቀርቡም አቤል እግዚአብሔር ንጹሕ ነውና ለእግዚአብሔር የተመረጠውን አቀረበ፤ ቃየን ግን የተገኘውን ሁሉ ሳይመርጥ አቀረበ፡፡ የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ሲወደድለት የቃየን ግን ሳያርግት ቀረ፡፡ ቃየንም በዚህ ቀንቶ ወንድሙን አቤልን ገድሎታል፡፡

እኛም ከአቤል ለእግዚአብሔር የተመረጠውንና ንጹሑን ነገር ማቅረብ እንዳለብን እንማራለን፡፡ ለእግዚአብሔር የምንቀርበው የመጀመሪያው ነገር ደግሞ ራሳችንን ነው፡፡“ ***እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።” እንዳለ*** ሮሜ. ፲፪ ፥ ፩

ከቃየን የምንማረውም ኃጢአትን ማቆም ገና በኃልዮ ሳለች (ስትታሰብ) እንደሆነ ነው፡፡ ወደ ኃጢአት እንዳንገባ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ሲመክረንም መስማት አለብን፡፡ **ለምሳሌ**፡- እግዚአብሔር ቤተሰብን፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ መልካም ጓደኛን፣ መጻሕፍትን… ምክንያት አድርጎ ይመክረናል፡፡ እኛም አታድርጉ የተባልነውን በመተው በማስተዋልም ከክፉ መንገዳችን መመለስ አለብን፡፡

## ተግባር

www.zeorthodox.org

1. መጽሐፍ ቅዱስ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ ማንበብ ጀምሩ፡፡
2. ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትመጡ በንጽሕናና በይቅርታ መንፈስ ሆናችሁ የተጣላችሁትን ታርቃችሁ ወይም ይቅርታ ጠይቃችሁ ግቡ፡፡

# አባታችን ኖኅ

## አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ኖኅ መልካም ምግባር መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ”* ዕብ. ፲፩ ፥ ፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ. ከምዕ. ፮ - ፱

## መግቢያ

ኖኅ ዓለም በሙሉ በኃጢአት ይኖር በነበረበት ዘመን በቅድስና ይኖር የነበረ ሰው ነው፡፡ በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ብዙ ክፋቶችን ይፈጽሙ ነበርና እግዚአብሔር የኃጢአት ጽዋቸው መሙላቱን አውቆ ሊያጠፋቸው ወሰነ፡፡

ኖኅን ግን ጻድቅ ሰው ነበርና አብሮ ሊያጠፋው አልፈለገም፡፡ በዛሬው ትምህርታችን በኃጢአተ ኞች የሆነባቸውንና ስለ ኖኅ መዳን እንማራለን፡፡

## የትምህርቱ ይዘት

ኖኅ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን የነበሩት ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ አምጸው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ሰውን በመፍጠሩ አዘነ፡፡ ኖኅ ግን እግዚአብሔርን የሚወድና ጻድቅ ሰው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ኖኅ ራሱን፣ ቤተሰቡን፣ እንስሳትንም ከየዝርያቸው እንዲያድን መርከብ እንዲሠራ አዘዘው፡፡ አሠራሩንም ነገረው መስኮት፣ በርና ሌሎችም የመርከቡ ክፍሎች እንዴት እንደሚሠሩም አስተማረው፡፡

www.zeorthodox.org

ኖኅም እንደታዘዘው አደረገ፡፡ በምድር ላይ ዝናብ በብዛት ወረደ ከምድርም ውኃ ፈለቀ፡፡ ይህም ለ40 ቀናት በምድር ላይ ሆነ፡፡ ከሰው እስከ እንስሳ በኖኅ መርከብ ካሉት ውጪ ሁሉም ጠፉ፡፡ ከ150 ቀናት በኋላም ዉኃው ደርቆ ምድር ተገለጠ፤ መርከቧም አራራት በተባለ ተራራ ላይ ዐረፈች፡፡

ኖኅ ውኃው መድረቁን ለማረጋገጥ ቁራን ላከ በዚያው ቀረ፡፡ ርግብን ሲልክም ማረፊያ ስላጣች ተመልሳ መጣች፤ ከሰባት ቀናት በኋላ ኖኅ ርግብን ዳግመኛ ሲልካት የወይራ ቅጠል ይዛ መጣች፤ ኖኅም በዚህ ምድር መድረቋን አወቀ፡፡

ከዚያም እግዚአብሔር ኖኅን ከቤተሰበና ከእንስሳቱ ጋር ከመርከበቧ እንዲወጣ አዘዘው፡፡ ኖኅ ከመርከብ ሲወጣ የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው መሠዊያ ሠርቶ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም የኖኅን መስዋዕት ተመለከተ፡፡ በጥልቅ እምነትና ከእንስሳቱም መርጦ አቅርቧልና እግዚአብሔር ***«ምድርን ዳግመኛ በንፍር ውኃ አላጠፋም»*** ብሎ ቃል ገባለት፤ ***«ፍሬያማ ሁን»*** ብሎም ባረከው፡፡ ***«በቀስተ ደመና»*** ምልክትነትም ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውኃ እንደማያጠፋት ቃል ገባለት፡፡ ቃል ኪዳኑንም **‹‹በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥ ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው፤ ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ፥ የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል፡፡›› በማለት አተመው፡፡** ዘፍጥ. ፱ ፥ ፲፪

## ማጠቃለያ

- ምድር በኃጢአት ስትጠፋ ኖኅና ቤተሰቡ ለዘር ከቀሩት ከእንስሳቱ ጋር ተርፈዋል፡፡ መልካምነት ቢዘገይም ዋጋ ያለው ሲሆን ክፋት ግን ቢዘገይም ያጠፋል፡፡

## ተግባር

- ከክፉዎች ጋር አትተባበሩ፡፡

### ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ምድርን በውኃ ለማጥፋት ለምን ፈለገ?
2. ኖኅና ቤተሰቡንስ ለምን አዳነ ?
3. ኖኅና ቤተሰቡስ እንዴት ነበር የዳኑት?
4. ዝናቡ ለስንት ቀናት ዘነበ፤ ውኃውስ ለስንት ቀናት ቆየ?
5. ኖኅ የምድርን መድረቅ ለማወቅ ምን አይነት አዕዋፍን ላከ? የትኛው ተመለሰ?
6. ኖኅ ከመርከብ ሲወጣ በመጀመሪያ ያደረገው ምንድን ነው?
7. እግዚአብሔር ከኖኅጋር የገባው ኪዳን ምንድነው? ምልክቱስ ምንድነው?
8. የኖኅ ታሪክ የተጻፈበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጥቀስ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቤተሰብን ጉድለት እንዴት ይያዛል?

## አምስተኛ ሳምንት

**ትምህርቱ ዓላማ፡-** ስህተትን አላግባብ መግለጥ እንደማይገባ ማስረዳት።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።"* ገላ. ፮ ፥ ፪

**ተጫማሪ ምንባብ፡-** ዘፍጥ. ፱ ፥ ፳ - ፳፱

**መግቢያ፡-** አንዳንድ ልጆች በቤተሰቦቻቸውና እነርሱ በቅርበት በሚያውቋቸው ሰዎች ላይ ሌላው ሰው እስኪታዘባቸው ድረስ ይዘብታሉ። የቤተሰቦቻቸውን ጉድለት በውጭ ላለ ሰው አውጥተው የሚያወሩም አሉ። ልጆች ሆይ ከቤተሰብ አንድ ሰው አጥፍቶ ከሆነ መማካከርና መታረም ያለበት በቤተ ውስጥ ነው። እናንተ ከቤተሰብ አንድ ሰው የተሳሳተ ነገር ሲያደርግ ብታዩት ምን ታደርጋ ለችሁ? በክፍልና እና በቤት ውስጥ ተወያዩበት። በዛሬው ትምህርታችን የአንድን ታላቅ አባት ስህተት ልጆቹ ያስተናገዱበትን መንገድ እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

አባታችን ኖኅ እግዚአብሔርን የሚፈራና ደግ ሰው ነበር። በቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደምናገኘውም በጾምና በጸሎት የጸና ነበር። ዓለም በውኃ ሲጠፋ ከሰውና ከእንስሳት ዘርን ለማስቀረት እግዚአብሔር የመረጠውና የተጠቀመበት አባትም ነበር። ኖኅና ልጆቹ ከመርከብ ወርደው ኑሮአቸውን ጀመሩ። ኖኅ ገበሬ መሆን ጀመረ። አዝርእትና አትክልትን እየተከለና እየዘራ መመገብ ጀመረ። ወይንም ተከለ፤ ከፍሬው በልቶ ውኃውን መጠጣት ጀመረ። አንድ ቀንም የከረመውን ወይን ጠጣ። ኖኅ በተጋድሎ ሰውነቱ ደክሞ ስለነበር ወዲያው ሰከረ። አሁን የምንማረው የስካርን አስከፊነት እንድንረዳ የተጻፈልንን ታሪክ ነው። ልጆች! አልኮል ያሰክራል፤ ስካር ደግመሞ እራስን መሳት ነው። መጽሐፍ ቅዱሰ አብዝቶ መጣጣትንና ስካርን ይቃወማል። *"ዋይታ ለማን ነው? ኀዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለ ምክንያት መቊሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን? ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሴ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ። በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል።"* ምሳ. ፳፫ ፥ ፳፱ - ፴፪።

www.zeorthodox.org

***“የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና።”***

*፩ኛ ጴጥ. ፬ ፥ ፫*

ወደ ተነሳንበት ታሪክ እንመለስ፡- ታላቁ ኖኅ ሰክሮ እርቃኑን ሆነ። ከሦስቱ ልጆቹ አንዱ ካም የአባቱን ራቁትነት አየ። መጥቶም ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው። ወንድሞቹም ሸማ ወስደው በጫንቃቸው ላይ አደረጉ። የኋሊትም ሄደው የአባታቸውን ራቁትነት አለበሱ። ዘፍጥ. ዘፍጥ. ፱፥፳-፳፫። ልጆች ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ? በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።

ካም ሁለት ጥፋት አጥፋቷል። ጥፋቶቹም የአባቱን እርቃን ማየትና ለሌላው መንገር ናቸው።

**ሊያየው የማይገባውን የአባቱን ድካም አየ፡-** ልጆች በአጋጣሚ ወደ ዐይናችሁ የመጣ ነገርሁሉ አይታይም፤ ዘወር ይባላል እንጂ። ለዚህ ነው ቤተሰቦቻችሁ አንዳንድ ነገሮችን እንዳታዩ የሚከለክሉአችሁ። እናንተም ማስቸገር የለባችሁም። የማይጠቅመንንና የሚጎዳንን ነገር ማየት የለብንም።

**ያየውን አወራ፡-** ያየውን ክፉ ነገር ዐይቶ አባቱን መርዳት ወይም እንዳላየ ሆኖ ማለፍ ነበረበት። ሆኖም ለወንድሞቹ ሄዶ አወራ። ልጆች የሚወራና የማይወራ ነገር አለ። አንዳንድ ልጆች ክፉ የወሬ ሱስ አለባቸው። ሲያወሩም ቤት የተበላው ሁሉ አይቀራቸውም። አንዳንዶቹ ደግሞ ለማን ምን መነገር እንዳለበት አይመርጡም። ለምሳሌ በቤተሰብ ውስጥ የተሠራ ጥፋት ለቤተሰብ፣ ለወላጅ ወይም ለታላቅ ተነግሮ እርምት እንዲሰጥበት ማድረግ ሲገባ ከዚህ በተቃራኒው በመንገድ ላገኙት ሁሉ የቤተሰባቸውን ጉዳይ የሚናገሩ ልጆች መታረም ያስፈልጋቸዋል።

ሁለቱ ልጆች ሴምና ያፌት ከላይ ካየነው ከካም ድርጊት በተቃራኒው ነው ያደረጉት። እነርሱም የአባታቸውን እርቃን ላለማየት ወደ ኋላ ሄዱ። ሸማ በትከሻቸው ላይ አድርገው ሲደርሱ የአባታቸውን ራቁትነት አለበሱ። ***“ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።”*** ገላ. ፮ ፥ ፪። ክርስቶስ በመስቀል ኃጢአታችንን እንዳስወገደልን፤ እኛም ለቤተሰቦቻችን ልበ ሰፊ ልንሆን ይገባል። ኖኅ ሲነቃ ሁሉንም ዐወቀ፤ሁለቱንም ወንድሞቹንም ባረካቸው። እንደባረካቸውም በሕይወታቸው አገኙ።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

የቤተሰብ ድካም በትዕግሥት፣ በፍቅርና በምክር ይሸፈናል። ***“ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው፥ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።”*** *ያዕ*.5፡19-20

**ተግባር፡-** በትዕግሥት የሚታለፍና የሚያስቀጣ ጥፋትን ከቤተሰብ ጠይቃችሁ ተረዱ።

# አብርሃም የእምነት አባት

## ስድስተኛ ሳምንት

***ዓላማ:-*** የአብርሃምን የእምነት ሕይወትና ስለ ተሰጠው ቃል ኪዳን ማስገንዘብ::

***የሚጠና ጥቅስ:-*** ***«እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ*** በእነርሱ ***አያፍርም»*** ዕብ. ፲፩ ፥ ፳፮

***ተጨማሪ ምንባባት:-*** ዘፍጥረት ፲፪ - ፲፫ እና ፳፩ - ፳፪

### ***መግቢያ:-***

አባታችን አብርሃም የእምነት አባት ነው:: ልጅ ሳይኖረው እግዚአብሔር ልጅ እንደሚሰጠው በገባለት ቃል ጸንቶ ለረጅም ዓመታት ኖረ:: እእግዚአብሔርም ልጆቹን እንደ ምድር አሸዋ እንደሚ ያበዛለት ቃል ገባለት:: ዛሬ የአብርሃምን የእምነት ጉዞ፣ ለእግዚአብሔር በእምነት በመታዘዝ የተስፋው ልጅ ይስሐቅም አባቱን እንዴት እንደታዘዘዉ እንማራለን::

### የትምህርቱ ይዘት

አብርሃም ካራን በምትባል ምድር ከሚስቱ ከሣራና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር ይኖር ነበር:: አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን ጠርቶ ***«ከአገርህ፣ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ»*** አለው:: እንደሚባርከው፣ ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገው እንደሚያበዛውምና የምድር ነገዶች ሁሉም በእርሱ እንደሚባረኩ ቃል ገባለት::

አብርሃም የሚሄድበትን ሀገርም ሆነ በዚያ ካሉት ማንንም አያውቅም ነበር፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር እምነት ነበረውና ሚስቱን ሣራን፣ የወንድሙን ልጅ ሎጥንም ይዞ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀለት ምድር - ወደ ከነዓን ወጣ::

አብርሃም ባለጸጋ ሆነ ከሎጥም ጋር ብዙ መንጎች ነበሩአቸው:: ልጅ ግን አልነበረውም:: ከብዙ ዓመትም በኋላ ሣራ ልጅ ስላልወለደች ከአገልጋይዋ ከአጋር ልጅ እንዲወልድ ለአብርሃም አማከረችው:: አብርሃምም ልጅ ወለደ ስሙንም እስማኤል አለው:: ሆኖም ይህ ልጅ በእነሱ ፍላጎት እንጂ እግዚአ ብሔር ቃል የገባለት ልጅ አልነበረም::

አብርሃም 99 ዓመት ሲሞላው እግዚአብሔር ተገልጦ ከሣራ ልጅ እንደሚሰጠው ነገረው፤ ሣራ ግን ልጅ ለመውለድ የማትችልበት ዕድሜ ላይ እንደደረሰች አስባለችና ሳቀች፤ እግዚአብሔርም ከመጋረጃ ውስጥ ሆና በልቧ አስባ የሳቀችውን ሣራን አውቆ:: **«ሚስትህ ሣራ ለምን ሣቀች... በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?»** አለው:: ልጆች ምን ታስባላችሁ? እግዚአብሔር ሊያደርገው የማይችለዉ ነገር አለ? በፍጹም የሚሳነው የለም::

www.zeorthodox.org

በዓመቱ ሣራ ፀነሰች:: እግዚአብሔር እንደማለላቸው ወንድ ልጅ ወለደች:: አብርሃምም ስሙን ይስሐቅ አለው:: ይስሐቅ ጠንካራ ልጅ ሆኖ አደገ፥ አባቱንና እናቱንም ያገለግል ነበር::

የአብርሃበና የሣራ ብቸኛ ልጅ ካደገ በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው:: ልጅህ ይስሐቅን መስዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ አለው:: አብርሃም ልጁ ይስሐቅን በጣም ቢወደውም፣ ቤቱን የሚወርሰው እርሱ እደሆነና፣ ልጆቹም ምድሪቱን እንደሚወርሱ እግዚአብሔር ቃል የገባለት ቢሆንም ከፍቅሩና ከተስፋው በላይ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ አብርሃም ከባዱን ጥያቄ በእሽታ መለሰ:: ይስሐቅን ለእግዚአብሔር ሊሠዋውም ወሰደው::

የሦስት ቀን መንገድ ተጉዘው መሠዊያው ጋር ሲደርሱ አብርሃም ይስሐቅን ለእግዚአብሔር ሊሰዋው እንዳመጣዉ ነገረው:: ይስሐቅ ለመሮጥ ወይም ለመታገል አልሞከረም፤ አብርሃም ምን ያህል እንደሚወደው ያውቃልና:: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸምም አላቅማማም::

አብርሃም ይስሐቅን አስሮ በመሰዊያው አጋደመው:: ሊሰዋው ቢላውን ሲያነሣም የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ አቆመው:: የታሠረ የበግ ጠቦት አሳየውና በጉን ሰዋው አለዉ:: እግዚአብሔርም፦ ***«በራሴ ማልሁ ይህን አድርገሃልና አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእዉነት በረከትን እባርክሃለው::»*** ብሎ ቃል ገባለት::

## ማጠቃለያ

እእግዚአብሔር የሚደሰተው በእምነት ነው:: «***ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና:: ::***» ዕብ. ፲፩ ፥ ፲፮ አብርሃም በእምነት በመኖሩ እግዚአብሔርን አስደስቷል:: አብርሃም በእምነት አባታችን ነው፤ እኛም ከአባታችን ከአብርሃም በእምነት መኖርን ተምረናል::

## ተግባር

እንደ ይስሐቅ በማንኛውም ነገር ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፤ ማታ ሲመጡ እግራቸውን በማጠብ በረከታቸውንም ተቀበሉ::

www.zeorthodox.org

**መዝሙር፦ አማን በአማን (2) መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም::**

***ጥያቄዎች፦***

1. እግዚአብሔር አብርሃምን ወዴት እንዲሄድ አዘዘው? አብርሃምስ ወደ ተባለው ሥፍራ ሄደ?
2. አብርሃም ከአባቱ ቤት ሲወጣ ምንን ይዞ ወጣ? እግዚአብሔር ለአብርሃም የማለለት ምን ነበር?
3. ከሣራ ለአብርሃም ልጅ እንደሚሠጠው እግዚአብሔር ቃል ሲገባለት ሣራ ለምን ሣቀች?
4. አብርሃም እንዲሰዋ የታዘዘዉ ምን ነበር? አብርሃም ታዘዘ? ለምን?

# ካህኑ መልከ ጼዴቅ እና አባታችን አብርሃም

## ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ መልከ ጼዴቅ እና አብርሃም መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤" ዕብ. ፯ ፥ ፩***

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ዘፍጥ. ፲፬ ፥ ፲፬ - ፳፬፣ ቅዳሴ ጎርጎርዮስ ከቁጥር ፸፫ - ፹፫

## መግቢያ

ልጆች ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን ስለ አባታችን አብርሃም የእምነት ጉዞ ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የእምነት አባት የሆነው አብርሃም፤ በታላቁ የእግዚአብሔር ካህን በመልከ ጼዴቅ መባረኩን እንማራለን፡፡

### *የክለሳ እና የመግቢያ ጥያቄዎች፡-*

1. አብርሃም ወዴት ተጠራ?
2. የአብርሃምን እምነት የሚያሳየን ምን ነበር?
3. ይስሐቅ ከአብርሃም ጋር ሲሄድ ምን አደረገ?
4. አብርሃም በስንት ዓመቱ ልጅ ወለደ?
5. መልከ ጼዴቅ ማነው? ከአብርሃም ጋር ምን አደረገ? የምታውቁትን ተርኩ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

**የሎጥ መማረክ፡-** ሎጥ በራሱ በመረጠው ምድር የነበረው የሰዶም ንጉሥና ሌሎች በአካባቢው የነበሩ ነገሥታት ለኤላም ንጉሥ ለኮሎዶጎምር 12 ዓመታት ገበሩ፡፡ በ13ኛው ዓመት አምጸው በኮሎዶጎምር ላይ ተነሱበት፡፡ በ14ኛው ዓመት ጦርነት አደረጉ፡፡ ኮሎዶጎምር አሸነፋቸው፡፡

በሲዲም ሸለቆ በተደረገው ጦርነት የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት በሸለቆው እና በኮሎዶጎምር በሚመራው ሠራዊት መሐል ገቡና ብዙ ወታደር በጉድጎድ ገብቶ ሲሞትባቸው ነገሥታቱ ሸሹ፡፡ አሸናፊዎቹ ወደ ከተማው ገብተው ያገኙትን ሁሉ ማረኩ፤ በሰዶም የነበረው ሎጥም ተማረከ፡፡ ***‹‹የሰዶምንና የገሞራን ከብት ሁሉ መብላቸውንም ሁሉ ወስደው ሄዱ፡፡ በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥን ደግሞ ከብቱንም ወስደው ሄዱ፡፡››*** ዘፍ. ፲፬ ፥ ፲፩ - ፲፪

**አብርሃም ወንድሙን ታደገ፡-** ከምርኮ የተረፈ አንድ ሰው ለአብርሃም የወንድሙን የሎጥን መማረክ ነገረው፡፡***‹‹አብራምም ወንድሙ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ የተወለዱትን ሦስት መቶ አሥራ ስምንት (318) ብላቴኖቹን አሰለፈ፥ ፍለጋቸውንም ተከትሎ እስከ ዳን ድረስ ሄደ፡፡››*** ዘፍጥ.፲፬ ፥ ፲፬ አብርሃም ከእርሱ ጋር የነበሩትን ***‹‹ብላቴኖቹንም ከፍሎ››*** ወንድሙን ለማስመለስ ተዘጋጀ፡፡ ከዚያም ***በሌሊት እርሱ ከባሪያዎቹ ጋር*** የኮሎዶጎምር ሠራዊት እና የተማረኩት ባሉበት ደረሰ፤ ሠራዊቱም ላይ ***‹‹ወረደባቸው ፥ መታቸውም፥ ..... ሖባ*** እስከተባለ ሥፍራ ድረስም ***"አሳደዳቸው፡፡"*** ጦሩን አሸንፎ ሲመለስ ***‹‹ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፥ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን... መለሰ፡፡››*** ዘፍ. ፲፬ ፥ ፲፭ - ፲፮

**አብርሃም እና መልከ ጸዴቅ፡-** ከድል መልስ ሸሽቶ የተደበቀው የሰዶም ንጉሥ አብርሃምን ሊቀበለው መጣ፡፡ አብርሃም ግን መልከ ጼዴቅ ወደ ነበረበት ዋሻ ሄደ፡፡ በበሩም ላይ ቆሞ ***የእግዚአብሔር ሰው ሆይ!* *የእግዚአብሔር ሰው ሆይ!* *የእግዚአብሔር ሰው ሆይ!*** ብሎ ተጣራ፡፡ ጢሙ የረዘመ ግርማው የሚያስፈራ የእግዚአብሔር ካህንና የጽድቅና የሰላም ንጉሥ የነበረው መልከ ጼዴቅ ኅብስትና ወይን ይዞ ወጣ፡፡ አብርሃምም ባየው ጊዜ ወደ ምድር ወደቀ፤ መልከ ጼዴቅም አብርሃምን እጁን ዘርግቶ አነሳውና ‹‹***ወደ እኔ የላከህ እግዚአብሔር፤ ወዳንተ ይመጣል ብሎኛል››*** አለው፡፡ ሁሉቱም ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ተነጋገሩ፡፡

መልከ ጼዴቅ በኅብስት እና በወይኑ ለእግዚአብሔር *መሥዋዕት* አቀረበ፡፡ አብርሃምንም እንዲህ ሲል ባረከው፡- ***‹‹አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፡፡ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም፡፡ አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው፡፡››*** ዘፍጥ. ፲፬ - ፲፰ - ፳፡፡

አብርሃምን የባረከው መልከ ጼዴቅ ካህን ነበር፡፡ አብርሃም የክህነትን ክብር ስለሚያውቅ ተባረከ፡፡ ***ታናሽ በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነውና፡፡***

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ወንድሙን የሚወደው አብርሃም፣ ወንድሙን ለመታደግ ሲሄድ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና ድልን ሰጠው፡፡ ካህናትን ያከብር ስለነበርም በካህኑ በመልከ ጼዴቅ ለመባረክ ሄዶ በረከትን ተቀበለ፤ ካለውም አሥራትን አወጣ፡፡

## ተግባር

ፍቅራችሁ በተግባር የሚታይ ይሁን፤ ትባረኩም ዘንድ ጥረት አድርጉ፡፡

# ሙሴ

# ስምንተኛ ሳምንት

***ዓላማ፡-*** ስለ ሙሴ ሕይወት እና መልካምነት መማር፣

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ‹‹*ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም*›› ዮሐ. ፲፭ ፥ ፲፫

**ምንባባት፡-** ኦሪት ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁ እና ዘዳግም፡፡

## መግቢያ

ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ወደ ነፃይቱ ምድር ያወጣ ነው፡፡ የተወለደውም ከእሰራኤል የተወለደ ወንድ ሁሉ እንዲሞት አዋጅ በተነገረበት ወቅት ነበር፡፡ እናቱ ግን እንደተወለደ ለሦስት ወራት ከደበቀችው በኂላ በሳጥን አድርጋ በወንዝ ዳር አስቀመጠችው፤ የፈርዖን ልጅም አግኝታ ወሰደችው፥ እንደልጅ አድርጋም አሳደገችው፡፡

እናቱም እንደሞግዚት ሆና ታሳድገውና ታስተምረው ስለነበረም ዕብራዊ መሆኑን አወቀ፡፡ ሕዝቡ በባርነት እንዴት እንደሚሠቃዩ እያየም አደገ፡፡

አንድ ቀንም አንድ ዕብራዊ እና ግብፃዊ ሲጣሉ አይቶ ግብፃዊውን ገደለው፡፡ ይህም ዜና በግብፅ ተሠማ፤ ስለዚህም ሙሴ ከፈርዖን ቤት ሸሽቶ ምድያም በተባለች ምድር መኖር ጀመረ፡፡ በዚያም ሚስት አግብቶ ሁለት ልጆች ወለደ፡፡ የአማቹን የዮቶርን ከብቶች ሲያግድ 40 ዓመት ኖረ፤ ከብቶቹን በኮሬብ (የእግዚአብሔር ተራራ በሚባለው) እየጠበቀም በቁጥቋጦ መሐል በሚነድ እሳት እግዚአብሔር ተገለጠለት፡፡

www.zeorthodox.org

በዛሬው ትምህርታችን ሙሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ሕይወት እንማራለን፡፡ ይህም ጊዜ እግዚአብሔር ከተገለጠለት በኂላ ያለው ጊዜ ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

***ሙሴ መልካም ልብ ያለው ሰው ነበር፡፡*** ስለ ሕዝቡ መከራ ያለውን ሀብትና ሥልጣን ሁሉ ትቶአል፡፡ ሕዝቡ እየተሠቃየ በንጉሡ ቤተ መንግሥት መኖር አላስደሰተውም፡፡ በዚህም እስራኤልን ነፃ ሊያወጣ እግዚአብሔር ሾመው፡፡

***ሙሴ ትጉህ ሰው ነበር።*** እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ ሊያወጣ ወደፈርዖን እንደሚልከው ሲነገረው ‹‹***ወደ ፈርዖን የምሄድ የእሰራኤልንም ልጆች ነፃ የማወጣ እኔ ማን ነኝ***› ዘጸ.3÷11 ነበር ያለው ሙሴ። እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር እንደሆነና የሚናገረውን ቃል እንደሚፈጽምለት እና ሕዝቡንም በእርሱ እጅ በእግዚአብሔር ኃይል እንደሚያወጣ ነገረው።

***ሙሴም ወደ ፈርዖን ሄዶ እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል አለው።*** እግዚአብሔር እንዳዘዘው በትሩን ወደ ምድር ጥሎ እባብ ሲሆን እንደ መጀመሪያ መልዕክት ለፈርዖን አሳየው። ፈረዖንም አዲስ ነገር እንዳልሆነ በመግለፅ ጠንቋዮች አምጥቶ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። የሙሴ በትር ግን የጠንቋዮቹን በትሮች በዋጠቻቸው። ፈርዖን ግን ሕዝቡን አልቀቀም በዚህም እግዚአብሔር አሥር መቅሠፍቶችን አመጣባቸው። በመጨረሻም ፈርዖን ሕዝቡ እንዲሄዱ ፈቀደ።

***ሙሴ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲያስቡ በተደጋጋሚ ያሳስባቸው ነበር።*** እነርሱ ግን ሁሌም ይጠራጠሩና እግዚአብሔርን ያስቆጡ ነበር። ወደ ቀይ ባሕር ሲወጡም የፈርዖን ጦር ተከትሎዋቸው ነበር፤ ሕዝቡም ፈርተው በሙሴ ላይ አለቀሱ። ‹‹***ልትገድለን አወጣኸን***›› አሉት ሙሴ ግን ‹‹***የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ***› አላቸው። ባህሩንም በበትሩ መታው፤ ለሁለት ተክፍሎላቸውም ተሻገሩ። ሙሴ በጉዞአቸውም ታላላቅ ተአምራትን ያደርግላቸው ነበር። መና ከሰማይ፣ ውሃ ከዐለት፣ በጦርነት ድሎችን እየሠጠም ወደ ተስፋይቱ ምድር አደረሳቸው።

***ሙሴ የጾምና ፀሎት ሰው ነበር።*** ሙሴ ሁለቱን ጽላቶች ሲቀበል 40 ቀንና ሌሊት ጾሞ ነበር።

***ሙሴ ከራሱ ደኅንነት ይልቅ ስለሕዝቡ ያስብ ነበር።*** እንዴ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ስለ አመጹ እግዚአብሔር ይህን ሕዝብ አጥፍቼ በሌላ ሕዝብ ላይ እሾምኃለሁ አለው። ሙሴ ግን በሌላ ሕዝብ ላይ መሾም እንደማይፈልግና ሕዝቡን እንዲያድንለት ተማጸነ። ‹‹ይህ ካልሆነ ግን ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ ነበር ያለው።›› እግዚአብሔርም የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ ሕዝቡን አዳነ።

***ሙሴ በቅዱሳን አማላጅነት ያምን ነበር።*** ሙሴ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያድን ሲማጸን እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የማለላቸውን መሐላ አስቦ እንዲያድናቸው ነበር የጸለየው። እግዚአብሔርም ተቀብሎ ፈጸመለት። ዘጸ.፴፪ ፥ ፲፫

www.zeorthodox.org

***እግዚአብሔር ቅዱሳንን እንድናከብር ይፈልጋል።*** ሕዝቡ በሙሴ ላይ ሲያጉረመርም እግዚአብሔር ተቆጥቷል።የማራቸውም በሙሴ ምልጃ ነበር። ወንድሙን አሮንን የገሠጸው እኅቱ ማርያምንም በለምፅ የመታት ወዳጁና ቅዱሱን ሙሴን ስለተቃወሙበት ነበር። ዘኁ. ፲፪ ፥ ፩-ፍጻሜ

***ሙሴ ወደ ቃል ኪዳኒቱ ምድር ከመግባቱ በፊት በ120 ዓመቱ ሞተ፡፡*** እግዚአብሔር ምድሪቱን በሩቅ አሳየው፣እስራኤልም ለአንድ ወር አለቀሱለት፡፡ ሙሴም ኢያሱ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያስገባ ከመሞቱ በፊት ተክቶላቸው ነበር፡፡ ዘዳ. ፴፪ ፥ ፲፩ - ፴፡፡

***ሙሴ አምስቱን መጻሕፍት ጽፏል፡፡*** ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉትን መጻሕፍት ጽፏል፡፡

## ማጠቃለያ

ሙሴ ለ120 ዓመታት በዚህ ምድር ሲኖር እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ለወገኖቹና ለአምላኩ ቀናዒ የነበረ አባት ነበር፡፡ እኛም ከእርሱ ሕይወት የምንማራቸውን በመተግበር ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

***"ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ"*** ዕብራ. ፲፩ ፥ ፳፬ እንደተባልን እኛም ዓለም የምታቀርብልንን ኃጢአትና ክፋት እምቢ ማለትን መልመድ አለብን፡፡

## ተግባር

- ሙሴ ከእናቱ የተማረው እንደጠቀመው እኛም ከቤተ ሰቦቻችንን መልካሙን ሁሉ መማር አለብን፡፡ በተጨማሪም ወላጆቻችሁን ተመሳሳይ ታሪክ እንዲተርኩላችሁ ጠይቁ፡፡

***ጥያቄዎች፡-***

1. የሙሴ እናት በሣጥን አድርጋ ወንዝ ዳር ያስቀመጠችው ለምን ነበር? የት አደገ?

_______________________________________________

2. ሙሴ የዕብራውያንን እምነትና ባሕል እንዴት ተማረ?

_______________________________________________

3. ሙሴ እስራኤል በቀይ ባሕር ሲያለቅሱበት ምን አላቸው?

_______________________________________________

4. ሙሴ አሥርቱን ትዕዛዛት ከመቀበሉ በፊት ስንት ቀንና ሌሊት ጾመ?

_______________________________________________

5. እግዚአብሔር ለሙሴ መጀመሪያ ሲገለጥለት እንዴት ነበር?

_______________________________________________

6. ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ነፃ ታወጣለህ ብሎ ሲልከው የሙሴ መልስ ምን ነበር?

_______________________________________________

7. እስራኤልን በማመፃቸው ሊያጠፋቸው ከወሰነ በኂላ እግዚአብሔር የራራላቸው ለምን ነበር?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

# የኤልያስ መሥዋዕት ዐረገ

## ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔር እውነኛ አምላክነት የተገለጠበትን ታከረ ማስተማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባራቸው ተደፍተው፡፡ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ፡፡"*** ፩ኛ ነገሥ. ፲፰ ፥ ፴፱

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ፩ኛ.ነገሥ. ፲፰ ፥ ፩ - ፴፱

### መግቢያ፡-

ልጆች በድሮ ዘመን ነቢዩ ኤልያስ የተባለ ቅዱስ እግዚአብሔር አስነሳ፡፡ ኤልያስ የተነሳው የእስራኤል መንግሥት ለሁለት በተከፈለበት ዘመን ነበር፡፡ ያኔ የነበሩ ነቢያት በተነሱበት አገር የእስራኤልና የይሁዳ ነቢያት ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ኤልያስ የተነሳው በእስራኤል ቢሆንም ሁለቱንም ያገለገለ ነቢይ ነው፡፡ ኤልያስ በተወለደበት አካባቢ ቴስቢያዊ ይባላል፡፡ በዘመኑ ንጉሥ አክአብ እና ሚስቱ ኤልዛቤል በእስራኤልን ነበሩ፡፡ በእነኚህ ነገሥታት መሪነት የጣዖት አምልኮ ተስፋፋ፡፡ የእግዚአብሔርም መሠዊያ ፈረሰ፡፡ ኤልያስም ይህን ተቃውሞ ለእግዚአብሔር በመቅናቱም ብዙ መከራ ደረሰበት፡፡ ዛሬ ከሰፊው የኤልያስ አገልግሎት ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያደረገበትን ታሪክ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

#### ኤልያስ

ኤልያስ ማለት እግዚአብሔር አምላክ ነው! ማለት ነው፡፡ ንጉሥ አክአብ ከአሕዛብ ወገን በሆነችው ሚስቱ በኤልዛቤል ምክር ሄደ፡፡ በሚስቱ ምክር ተታሎ አምልኮ ጣዖትን አስፋፋ፡፡ ነብዩ ኤልያስም አክዓብ ንጉሥ ነው ብሎ ሳይፈራ ገሠጸው፤ ሆኖም አክዓብ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማም፡፡

www.zoorthodox.org

#### ሰማይ እንዳያዘንብ ሰማይን ለጎመ

ኤልያስም "***ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤***" ያዕ. ፭ ፥ ፲፯ ለአክዓብም ***"በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው፡፡"*** ፩ኛ ነገ ፲፯ ፥ ፩፡፡ እግዚአብሔርም ኤልያስን እንዳይገድሉህ በዮርዳኖስ ማዶ ባለች ቦታ ተሸሸግ አለው፡፡ በዚያም

የሚመግበውን ቁራና ወራጅ ወንዙን ባረከለት፡፡ ይህንን እየተመገበም ኖረ፡፡ ***ከብዙ ቀንም በኋላ በምድር ላይ ዝናብ አልነበረምና ወንዙ ደረቀ፡፡*** ልጆች እግዚአብሔር ወዳጆቹን ይሰማል፤ ዝናብ የቆመው በኤልያስ ጸሎት ነው፡፡ ኤልያስ በሕዝቡ የደረሰውን መከራ ተረድቶ ዝናብ ይዝነብ ብሎ እንዲጸልይ ኤልያስ እንዲራብ አደረገው፡፡ ከዚያም ይህንን የበለጠ ማወቅ የሚችልበት ቦታ ወሰደው፡፡ በስራፕታ የምትመግበው ሴት አዘጋጀለት፡፡ እዚያ ሲደርስም አንዲት ሴት እንጨት ስትለቅም አገኛት፡፡ ውኃና ምግብ ጠየቃት ***"እርስዋም፦ አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ከእፍኝ ዱቄት፥ በማሰሮም ካለው ከጥቂት ዘይት በቀር እንጀራ የለኝም እነሆም፥ ገብቼ ለእኔና ለልጄ እጋግረው ዘንድ በልተነውም እንሞት ዘንድ ጥቂት እንጨት እሰበስባለሁ አለች።"*** ኤልያስም ዝናብ እስኪዘንብ ማድጋዋና ማሰሮዋ አይጎድልም ብሏል እግዚአብሔር አላት፡፡ በእርስዋም ቤት ኖረ፡፡ እግዚአብሔር እንዳለውም ለብዙ ቀናት እየተመገቡ ኖሩ፡፡

### አክዓብና ኤልያስ ተገናኙ

በሦስተኛው ዓመት በሰማርያ ራብ እጅግ ስለጸና፦ ንጉሡ አክዓብ አብድዩ ከተባለው አገልጋዩ ጋር ውኃ ፍለጋ ወጡ፡፡ በተለያየ መንገድም መፈለግ ጀምሩ፡፡ ኤልያስም በእግዚአብሔር ተነግሮት ወጣ፡፡ መጀመሪያ አብድዩን፣ ከዚያም አክዓብን አገኛቸው፡፡ ኤልያስ፦ ኤልዛቤል እየቀለበች ያስቀመጠቻቸውን 450 የጣዖት ካህናት እንዲሰበስብለት ለአክዓብ ነገረው፡፡

### ለሕዝቡ የቀረበ የአምልኮ ምርጫ

አክዓብም የጣዖት ካህናቱንና ነቢያቱን በቁርሜሎስ ተራራ ሰበሰበ፡፡ ሕዝቡም ተሰበሰቡ፡፡ ***"ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ። እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ።"*** ፩ኛ ነገ. ፲፰ ፥ ፳፩፡፡ ሁለት ወይፈኖች ቀርበው አንዱን 450ው የጣዖት ካህናት አንዱን እርሱ እሳት ሳያደርጉ ለመሥዋዕት እንዲያቀርቡ፡ ***"እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፥ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን፦ሕዝቡም ሁሉ። ይህ ነገር መልካም ነው ብለው መለሱ።"***

www.zeorthodox.org

### መሥዋዕት ቀረበ

የጣዖት ካህናቱ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሙሉ ቀን እየጮሁ በዓል ሆይ ስማን ሲሉ ዋሉ፡፡ ሆኖም የሚመልስ አልነበረም፡፡ የሠርክ ጸሎት የሚደረግበት ሰዓት ሲደርስ እነርሡ ጨርሰው ተቀመጡ፡፡

ኤልያስ ተነሳ፡፡ የፈረሰውን የእስራኤል መሠዊያ ሠራ፤ በእስራኤል ልጆች ቁጥር፣ ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ወስዶ ለመሰዊያ ደረደረ፡፡ በመሠውያው ዙርያ ጉድጓድ ቆፈረ፡፡ እንጨት ረብርቦም

ወይፈኑን በብልት በብልት አስቀርጦ ደረደረ፡፡ ከዚያም ውኃ አምጡ አለ፤12 ጋን ውኃ በመሠዊያው ላይ አፈሰሱ፡፡ ***"ውኃውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ ደግሞም ጕድጓዱን በውኃ ሞላው።"***

*መሥዋዕተ* ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ። ***‹‹አቤቱ፥ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፥ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፥ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፥ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ። አንተ፥ አቤቱ፥ አምላክ እንደ ሆንህ፥ ልባቸውንም ደግሞ እንደ መለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ፥ አቤቱ፥ ስማኝ አለ።››***

## የእግዚአብሔር አምላክነት በመሠዊያው ተገለጠ

የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን *መሥዋዕቱንም* እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፥ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች። ሕዝቡም ሁሉ ያንን ባዩ ጊዜ በግምባ ራቸው ተደፍተው። እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው አሉ፡፡

ኤልያስ የእግዚአብሔርን አምላክነት ከገለጠ በኋላ የሐሰት ነቢያትና የጣዖት ካህናት የሆኑት ተቀጡ፡፡ ምድሪቱም ዝናብ እንድታገኝ ኤልያስ ጸለየ ዝናብም ዘነበ፡፡

## ማጠቃለያ

ኤልያስ ታላቅ ነቢይ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር አምልኮ ቀንቷል፤ ሰማይን ሦስት ዓመት ዝናብ እንዳታዘንብ ከልክሏል እንደገናም እንዲዘንብ አድርጓል፡፡ ልጆች እናንተም ስለ ራሳችሁ ስለ ቤተሰብ እና ስለ ሀገራችሁ በእምነት ጸልዩ እግዚአብሔር ይሰማችኋል፡፡***"እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች፡፡"*** *ያዕ. ፭ ፥ ፲፯ - ፲፰፡፡*

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ነው፡፡ ኤልያስ የእግዚአብሔርን አምላክነት በእምነት እንደገለጠ እኛም በእውነተኛ ይቱ እምነት ሆነን ስለ እግዚአብሔር አምላክነት እና ጌትነት በኑሯችን፣ በትምህርትና በምናገኘው አጋጣሚ መግለጥ አለብን፡፡

www.zeorthodox.org

ኤልያስ በመልካም ሥራው የተነሣ ብዙ መከራ ተቀብሏል፡፡ እውነተኛ መሆንና ሃይማኖትን መያዝ መከራ ያመጣል፡፡ ሆኖም ሁሉም በእግዚአብሔር ኃይል ድል ይደረጋል፡፡

**ተግባር፡-** ጠዋት ከእንቅልፋችሁ ስትነሱም ሆነ ማታም ከመኝታ በፊት መጸለይን አታስታጉሉ፡፡

# የኢሳይያስ ራእይ

## ዐሥረኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ዓላማ የመፈጸምን አስፈላጊነት መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-***"የጌታንም ድምፅ፡፡ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ፡፡ እኔም፡፡ እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ አልሁ፡፡"* ኢሳይ. ፮ ፥ ፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ትን.ኢሳ. ፮ ፥ ፩ - ፍም፣ ትንቢተ ኢሳይያስ ንባቡና ትርጓሜው መግቢያ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 162፡፡

### የክለሳ እና የመግቢያ ጥያቄዎች

1. ነቢያት የይሁዳና የእስራኤል የተባሉት ለምንድነው? ኤልያስ የት የነበረ ነቢይ ነው?
2. ኤልያስ በዘመኑ ያጋጠመው አሳዛኝ ነገር ምን ነበር? እርሱስ ምን አደረገ?
3. ራእይ ምንድነው? ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ ምን ታውቃላችሁ? በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

### መግቢያ፡-

ኢሳይያስ እግዚአብሔር አዳኝ ነው ወይም መድኃኒት ማለት ነው፡፡ በትምህርቱና በትንቢቱ እንዲያድን አውቀው ቤተሰቦቹ ኢሳይያስ ብለው ሰይመውታል፡፡ ኢሳይያስ፡- ዖዝያን፣ ኢዩአታም፣ አካዝና ሕዝቅያስ በተባሉ የይሁዳ ነገሥታት ዘመን ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው፡፡ኢሳ. ፩ ፥ ፩ በመጨረሻዎቹ ሁለት ነገሥታት ዘመን የቤተ መንግሥት አማካሪ ነበር፡፡ ዖዝያን አጥፍቶ ባለ መገሠጹና ባለማረሙ ተቀጥቷል፤ ሆኖም ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔር ተገልጦለት ለነቢይነት ጠራው፡፡ ኢሳ. ፮ ፥ ፩ - ፱፡፡ ኢሳይያስ በዘመኑ ስለነበሩት ነገሥታት፣ ስለኢየሩሳሌም ምርኮ እና መመለስ፣ ስለ ክርስቶስም ግልጽ ትንቢቶችን የተናገረ ነቢይ ነው፡፡ በዚሁ አገልግሎቱ እንደጸና በመጋዝ ተሰንጥቆ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡ ሊቃውንት ቅዱስ ጳውሎስ *"በመጋዝ ተሰነጠቁ"* ዕብ. ፲፩ ፥ ፴፯ ያለው ኢሳይያስን እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ከነቢዩ ትንቢቶች ለነቢይነት የተጠራበትን ራእይ በአራት ክፍለን እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

### የእግዚአብሔር የተገለጠበት ዘመንና ሁኔታ

***" ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር፡፡ "*** ኢሳ. ፮ ፥ ፩

ከ40 ዓመታት በላይ ይሁዳን ያስተዳደረው ዖዝያን በዘመኑ መጨረሻ ታበየ። ለካህናት ብቻ የተፈቀደውን አደረገ። በቤተ መቅደስ ገብቶም አጠነ። እግዚአብሔርም በለምጽ ቀሰፈው። በአንድ ቤት ለብቻው ተቀምጦ ቀሪውን ዘመኑን ኖረ። ልጁም አገሪቱን ያስተዳድር ነበር።

ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ተገለጠ፤ የተገለጠውም እንደ ንጉሥ ሆኖ፣ ከነገሥታት በተለየ ረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ነው። የሰማያዊው ንጉሥ ልብስም በመቅደሱ ሙሉ ነበር።

ልጆች አስተዋላችሁ? ዖዝያን የሚፈራ ንጉሥ ቢሆንም ሟች ሰው ነበር። ከፍታውና ዘመኑም የተገደበ ነው። ይህ ንጉሥ ይህን ዘንግቶ በትዕቢት የሰማዩን ንጉሥ ቤት ተዳፈረ። ቤተ መቅደሱን እንደ ራሱ ቤት ሊያዝበት ፈለገ። እግዚአብሔር ለኢሳይያስ ያሳየው ይህንኑ ነው።

## የሰማዩ የምሥጋና ሥርዓት

***"ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። አንዱም ለአንዱ። ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር። የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፥ ቤቱንም ጢስ ሞላበት።"*** ኢሳ ፮ ፥ ፪ - ፬።

ልጆች የሱራፌልን አቋቋም ኢሳይያስ ባየው መሠረት በሥዕል አሳዩ። ምን ዓይነት ቅርጽ ይታያችኋል? አዎን  የዚህ ዓይነት የመስቀል ቅርጽ አለው። ሱራፌል ከመላእክት ነገድ አንደኛዎቹ ናቸው። ሲቆሙና ሲበሩ እጁን እንደዘረጋ ሰው ወይም እንደሚበር አሞራ የመስቀል ምልክት እየሰሩ ነው። እኛም ስናማትብ፣ ነጠላችንን በመስቀል ቅርጽ ስንለብስ፣ እጃችንንም ዘርግተን ስንጸልይ የክርስቶስን ለዓለም መሰቀል እየመሰከርን ነው። በመስቀሉም ታላቅ ኃይል አለ።

ምሥጋናቸው አንዱ ለአንዱ እየተቀባበለ ነው። በቤተ ክርስቲያን ወረብ ወይም ቅዳሴ ላይ በመቀባበል የምናመሰግነው ከመላእክት ተምረን ነው። መድረኩ በምሥጋናውና በጢስ ተሞላ። መላእክት ሳያርፉ ጮኸው ያመሰግናሉ። እናንተም ስትዘምሩ አትቀጥቡ። (መምህር የማኅሌትን ሥርዓት ያነጻጽሩላቸው።)

www.zeorthodox.org

## የኢሳይያስ ትሕትናና ንስሐ

***"እኔም። ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፥ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ ! አልሁ። ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፥ በእጁም ከመሠዊያው በጕጠት የወሰደው ፍም ነበረ። አፌንም ዳሰሰበትና። እነሆ፥ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል በደልህም ከአንተ ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ።"*** ኢሳ ፮ ፥ ፭ - ፯

ልጆች ለጸሎት ስንቆም ታላቁ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር በፊታችን አለ፡፡ እናም እንደ ኢሳይያስ ኃጢአትን በማሰብ፣ በመናዘዝና በፍጹም ትሕትና መሆን አለበት፡፡

እግዚአብሔርም ለኢሳይያስ ሱራፌልን እንደላከ ለእኛም ካህናትን ይልክልናል፡፡ እነሱም በተሰጣቸው ሰማያዊ ሥልጣን ኃጢአትን ያስተሰርያሉ፡፡ በደልንም ያስወግዳሉ፡፡

## የእግዚአብሔር ጥሪና የኢሳይያስ መልስ

**ልዑል እግዚአብሔር *"ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?"*** አለ፡፡ ልጆች የሰማዩ አባታችን ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን የሚላክለት ይፈልጋል፤ በዘመኑ በምድር ላይ ብዙ ሰዎች ነበሩ ፡፡ ሆኖም ለእግዚአብሔር ለመላክ አልበቁም ነበር፡፡እናም ሰው ፈልጎ ማንን እልካለሁ ማንን ይሄድልናል አለ፡፡ ኢሳይያስ ከላይ እንዳየነው ንስሐ ስለገባና ስለተፈወሰ "እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ" አለ፡፡ እግዚአብሔርም ሂድ ብሎ ላከው፡፡ እርሱም መልእክቱን ይዞ ሄደ ለ60 ዓመታትም የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ በነቢይነት ኖረ፡፡

ልጆች እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ይጠራል፡፡ ኢሳይያስን በራእይ እንደጠራው፣ ሌሎችን በሕልም፣ ሌሎችን ቃሉን በማሰማት፣ ሌሎችንም በአባቶች እና በካህናት ሲጠራ ነበር፡፡ እኛንም ከተጠመቅንበት ቀን ጀምሮ ጠርቶናል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ***መጠራታችሁን ተመልከቱ*** ፩ኛ ቆሮ. ፩ ፥ ፳፯ በማለት ያስታውሰናል፡፡ ከእናንተ ለመዝሙር፣ ለነቢይነት፣ ለመምህርነት፣ ለመሪነት፣ ለካህንነት፣ ሰዎችን ለመርዳት.... የተጠራ አለ፡፡ እንደ ኢሳይያስ በጸሎት፣ በትሕትናና በንስሐ ከቆምን የተላክንበትን በተለያየ መንገድ ይነግረናል፡፡

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ የሆነ የሰማይና የምድር የሚታየውና የማይታየውም ንጉሥ ነው፡፡ ለእርሱ መታመንን እርሱን ማገልገል ከሁሉም ይበልጣል፡፡

የቤተ ክርስቲያናችን ዜማ ከዓለመ መላእክት የተወሰደ ነው፡፡ ይህንን ዜማ ማወቅም እንደ መላእክት በአንድነት ማመስገን ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ለጸሎት ስንቆም በእግዚአብሔር ፊት መቆማችን ነው፡፡ እናም በትሕትናና ኃጢአትን በማመን መቆም ይገባናል፡፡ ለእግዚአብሔር ጥሪ መታዘዝ ደግሞ ያስባርከናል፡፡

## ተግባር

መዝሙር ዘምሩ፤ ትሕትናና ያለበትን ጸሎት አዘውትሩ፡፡

# አቤሜሌክ ኤርምያስን ረዳ

## ዐሥራ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ለእውነት መቆምንና የእግዚአብሔርን ሰዎች መርዳትን መገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ** *"በዚያ ቀን አድንሃለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። ፈጽሜ አድንሃለሁ ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፥ በእኔ ታምነሃልና፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡"* ኤር. ፴፱ ÷ ፲፯ - ፲፰

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ኤርም. ፴፰ እና ፴፱፣ ተረፈ ኤር. ፪ ÷ ፰ - ፬ ÷ ፳፯

### መግቢያ

የዛሬው ትምህርታችን አቤሜሌክ ስለ ተባለ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ በመልካምነቱ እግዚአብሔር በሀገሪቱ ከሚደርሰው መከራ አድንሃለሁ ብሎ በብቸኝነት ያተረፈው ሰው ነው፡፡ ልጆች የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ነቢዩ ኤርምያስን ታውቁታላችሁ? ምን ሠርቷል? በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡
2. አቤሜሌክ ማለት ምን ማለት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ስም የሚጠሩ ሰዎችን አስታውሱ... የትኞቹን አስታወሳችሁ? ለመምህር ንገሩ፡፡

መምህር ስለ ነብዩ ኤርምያስ አወያይተው፣ በጥቂቱ ያብራሩላቸው? በተጨማሪም በዘፍ. ፳፩ ÷ ፳፪ - ፴፬፣ ፳፮ ÷ ፩ - ፴፫፣ መሳፍ. ፰ እና ፱፣ ሩት. ፩ ÷ ፪ - ፫፣ ፩ኛ ዜና. ፲፰ ÷ ፲፮ ላይ አቤሜሌክ በሚል ስም የተጠቀሱትን ሰዎች ሥራ በአጫጭር ትረካ ያብራሩላቸው፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

#### አቤሜሌክ ማነው?

አቤሜሌክ የንጉሥ አገልጋይ ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው በንጉሥ ሴዴቅያስ ዘመን በኢየሩሳሌም ቤተ መንግሥት የነበረ ጃንደረባ ነው፡፡ ልጆች ጃንደረባ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ትርጉም አለው፡፡ ለንጉሥ ታማኝ የሆኑ አገልጋዮች ጃንደረባ ይባሉ ነበር፡፡ ዘፍ. ፴፱ ÷ ፩፣ የሐዋ. ፰ ÷ ፳፯፣ ፪ኛ.ነገሥ. ፳ ÷ ፲፰፣ አስ. ፪ ÷ ፫ - ፲፭፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጌታችን ሦስት ዓይነት ጃንደረቦች አሉ ሲል አስተምሯል፡፡ *"በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች*

***አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ።"*** ማቴ. ፲፱ ፥ ፲፪። በዚህ መሠረት አቤሜሌክ በንጉሡ የሚታመን፣ የሚደመጥና የሚወደድ አገልጋይ ነበር። የስሙ ትርጉምም እንዲሁ ይህንኑ ያብራራል። ይህ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራና በነቢዩ ኤርምያስ የተነገረውን ቃል የሚሰማ ነበር። በተጨማሪም በኤርምያስ አገልግሎት ተሳትፏል። ተረፈ ኤር. ፪ ፥ ፰ - ፬ ፥ ፳፯።

**ኤርምያስ እውነት በመናገሩ የደረሰበት መከራ፡-** በኢየሩሳሌም የነበሩት ነገሥታቱና ሕዝቡ እግዚአብሔርን አሳዘኑ። ክፉ ኃጢአትም አደረጉ። እግዚአብሔርም ኤርምያስንና ሌሎች ነቢያትን ልኮ ንስሐ እንዲገቡ መከራቸው። ሆኖም ***"በነቢዩ በኤርምያስ እጅ የተናገረውን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም።"*** ኤር. ፴፯ ፥ ፪።

ሴዴቅያስ በኢየሩሳሌም ነገሠ። ባቢሎናውያንም ኢየሩሳሌምን ከበቡ። በዚህ የተጨነቀው ንጉሥ ወደ ነቢዩ ኤርምያስ የእውነት ንስሐ ሳይገባ ***ጸልይልን*** ብሎ መልእክተኞች ላከ። እግዚአብሔርም ኢየሩሳሌም ባቢሎን ንጉሥ እጅ ተላልፋ እንደምትሰጥ ለኤርምያስ ነገረው። ኤርምያስም ለመልእክተኞቹ፤ እግዚአብሔር ያለውን ደግሞ ለሕዝቡ ነገራቸው።

ቢነገራቸውም ንስሐ አልገቡም፤እንዲያውም አለቆች የተባሉት ወደ ንጉሡ ቀርበው፡- *‹‹ክፉት እንጂ ሰላምን አይመኝም፣ ሕዝቡን ያደክማልና ይገደል።››* አሉ። ንጉሡም በሐሳባቸው ባይስማማም ማስቆም ስላልቻለ ፈቀደላቸው። እነርሱም በረሃብና በጥም እንዲሞት ኤርምያስን አስረው ውኃ በማይገኝበት ጭቃ ባለበት ጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። ኤርምያስም ወደ ጭቃው ውስጥ ገባ።

**የአቤሜሌክ እርዳታ፡-** ይህንን የሰማው አቤሜሌክ ንጉሡን ቀርቦ ኤርምያስን ለማውጣት ለመነ። ንጉሡም ፈቀደለት። 30 ሰዎችንና አሮጌ ልብስ ይዞ ወረደ። ልብሱንና ጨርቆችን ወደ ኤርምያስ ጣለለትና በብብትህ አድርግ አለው። ገመዱንም ላከለት። ጎትተውም አወጡት። ኤርምያስም በጉድጓዱ ውስጥ ከመሞት ዳነ። ኤርምያስ እንደተናገረው ኢየሩሳሌም ተማረከች። አቤሜሌክም ስለ ሠራው መልካም ሥራ እግዚአብሔር ***"በዚያ ቀን አድንሃለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። ፈጽሜ አድንሃለሁ ነፍስህም እንደ ምርኮ ትሆንልሃለች እንጂ በሰይፍ አትወድቅም፥ በእኔ ታምነሃልና፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡"*** ኤር. ፴፱ ፥፲፯-፲፰ ብሎ በኤርምያስ እንደተናገረው ከምርኮው ኤርምያስ የበለስ ፍሬ ለማምጣት ልኮት ተረፈ።

www.zeorthodox.org

**ማጠቃለያ፡-** እውነትን መስማትና መልካም ማድረግ ይጠቅማል። ጭካኔና አለመታዘዝ ይጎዳል።

**ተግባር፡-** የእግዚአብሔርን ቃል በፍርሐት ስሙ። ዘወትር ለተገፋ ሰውና ለእውነት ቁሙ።

# የሠለስቱ ደቂቅ እና የዳንኤል ጾም

# ዐሥራ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በጾም ስለሚገኝ በረከትና ኃይል መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ እውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው ዳንኤልም በራእይና በሕልም ሁሉ አስተዋይ ነበረ።"*** ዳን.፩፥፲፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዳን. ፩ ፥ ፩ - ፳፣ ትንቢተ ዳንኤል ከዘመነ ባቢሎን እስከ ዓለም ፍጻሜ ከገጽ 22–33 በዲ/ን ዳንኤል ክብረት፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች፡-**

1. ኤርምያስ ስለ ኢየሩሳሌም ምን ትንቢት ተናገረ?
2. እግዚአብሔር አይሁድና ኢየሩሳሌም በባቢሎን እንዲማረኩ ለምን ፈቀደ?
3. የኤርምያስን ትንቢት የሰሙ ሰዎች ምን አደረጉ?
4. ኤርምያስን የረዳው ሰው ማን ይባላል? ለምን ይህንን አደረገ?

## መግቢያ

ናቡከደነፆር ከ፮፻፭ - ፭፻፷፪ ዓ.ዓ የነበረ የባቢሎን ንጉሥ ነው፡፡ ይህ ንጉሥ ሁለት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቷል፡፡ የመጀመሪያው በይሁዳው ንጉሥ በኢዮአቄም ዘመነ መንግሥት ሲሆን ፤ ሁለተኛውም በልጁ በሴዴቅያስ ዘመን ነው፡፡(፪ኛ ዜና. ፴፮፥፭-፯፣ ፲፩-፳)

በመጀመሪያው ወረራ የግብጽን ንጉሥ ኒካዑን አሸነፈ፡፡ ኢየሩሳሌምንም ያዘ፡፡ እርሱ የበላይ ሆኖ ከአይሁድ ልጆች ነገሥታት ይሾም ነበር፡፡ አይሁድ ሲያምጹ ከተማይቱን አፈራረሳት፤ ቤተ መቅደሱንም አቃጠለ፡፡ ሕዝቡንም ማርኮ ወሰደ፡፡ ኤር. ፶፮፥፪፣ ፪ኛ ነገ. ፳፬፥፩-፯፣ ፪ኛ.ዜና ፴፮፥፲፯-፳፩

www.zeorthodox.org

ከተማረኩት ወጣቶች ዳንኤልና ሦስቱ ጎደኞቹ ይኙበታል፡፡ ዳን. ፩፥ ፩ - ፯ በዛሬው ትምህርታችን እነዚህ ወጣቶች ከርኩስ ነገር ለመሸሽ ጾምን መምረጣቸውንና በዚህም መጠቀማቸውን እንማራለን፡፡ ለታሪኩ ፍሰት እንዲረዳንም የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል እንከተላለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

***"የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ከበባት።ጌታም የይሁዳን ንጉሥ ኢዮአቄምን ከእግዚአብሔርም ቤት ዕቃ***

***ከፍሎ በእጁ አሳልፎ ሰጠው እርሱም ወደ ሰናዖር ምድር ወደ አምላኩ ቤት ወሰደው፥ ዕቃውንም ወደ አምላኩ ግምጃ ቤት አገባው።"*** ዳን. ፩፥፩ ይህም የመጀመሪያው ወረራ ነው፡፡

ልጆች አይሁድ እግዚአብሔርን አሳዘኑት፤ እርሱም ለተግሳጽ ከፍሎ ለምርኮ ሰጣቸው፡፡ የሚወዷቸውና የሚባረኩባቸው ዕቃዎች (ንዋያተ ቅዱሳትም) ተወሰዱባቸው፡፡ ይህ ለአይሁድ ከባድ ቅጣት ነበር፡፡ በዚህ ደንግጠው ንስሐ እንዲገቡ እግዚአብሔር ይህን አደረገ፡፡ እኛም ስናጠፋ እግዚአብሔር በቤተሰብ በኩል፣ ወይም በካህናት አልፎም በሌሎች ሰዎች ይመክረናል፤ ይገስጸናልም፡፡ እኛም ስንቀጣና ስንገሰጽ ልንታረም ይገባል፡፡ ***"እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር። ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል፡፡"*** ዕብ. ፲፪ ፥ ፭፡፡

***"ንጉሡም ነውር የሌለባቸውንና መልከ መልካሞቹን፥ በጥበብ ሁሉ የሚያስተውሉትን ዕውቀትም የሞላባቸውን ብልሃተኞችና አስተዋዮች የሆኑትን፥ በንጉሡም ቤት መቆም የሚችሉትን ብላቴኖች ከእስራኤል ልጆች ከነገሥታቱና ከመሳፍንቱ ዘር ያመጣ ዘንድ የከለዳውያንንም ትምህርትና ቋንቋ ያስተምሩአቸው ዘንድ ለጃንደረቦች አለቃ ለአስፋኔዝ ነገረ። ንጉሡም ሦስት ዓመት ያሳድጉአቸው ዘንድ፥ ከዚያም በኋላ በንጉሡ ፊት ይቆሙ ዘንድ ከንጉሡ መብል ከሚጠጣውም ጠጅ በየዕለቱ ድርጎአቸውን አዘዘላቸው።"*** ዳን. ፩ ፥ ፪ - ፭፡፡

ልጆች ከለዳውያን በዛሬዋ ኢራቅ እና አከባቢዋ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡ በጥንት ዘመን ኃያል መንግሥት አቋቋሙ፡፡ ያኔ የሒሳብ፣ የከዋክብት ጥናት፣... ከአስማትና ጥንቆላ ጋር እንደ ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡

***ናቡከደነጾርም*** አስፋኔዝ በተባለ ሰው የሚመራ ትምህርት ቤት አቋቋመ፡፡ ዓላማውም የከለዳውያንን ቋንቋና ትምህርት ማስተማር ነበር፡፡ መመዘኛውም፡- መልክ፣ ማስተዋልና የነገሥታት ልጆች ዘር መሆን ነበር፡፡ የተፈለጉትም በንጉሡ ፊት እንዲያገለግሉ ሲሆን ሥልጠናው ለሦስት ዓመት ነበር፡፡

ይህን ዓላማ ለማስፈጸም የተመረጡት ልጆች ወደ ሥልጠናው ገቡ፡፡ ***"በእነዚህም መካከል ከይሁዳ ልጆች ዳንኤልና አናንያ ሚሳኤልና አዛርያ ነበሩ። የጃንደረቦቹም አለቃ ስም አወጣላቸው ዳንኤልን ብልጣሶር፥ አናንያንም ሲድራቅ፥ ሚሳኤልንም ሚሳቅ፥ አዛርያንም አብደናጎ ብሎ ጠራቸው።"*** ዳን. ፩ ፥ ፮ - ፯፡፡

www.zeorthodox.org

የአስፋኔዝ ሥራ ከላይ በተጠቀሰው ዓላማ መሠረት፤ ለባቢሎን ቤተ መንግስት ብቁ ልጆችን ማፍራት ነበር፡፡ ይህን በሚገባ ለመፈጸም የመጀመሪያ ሥራው ስም መቀየር ነበር፡፡ የሰማይ አምላክ የሚጠራበትን ስም በባቢሎን አማልክት ስም ቀየረው፡፡ ትርጉማቸውን ከሰንጠረዡ እንጻጽሩ፡፡

| ስማቸው | ትርጓሜው | ባቢሎናዊ መጠሪያ | ትርጓሜው |
|---|---|---|---|
| ዳንኤል | እግዚአብሔር ዳኛ ነው | ብልጣሶር | የበኣል ልጅ (መስፍን) |
| አናንያ | እግዚአብሔር ቸር ነው | ሲድራቅ | የአኩ አምሳል |
| ሚሳኤል | እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል | ሚሳቅ | እንደ ሻቅ ማነው |
| አዛርያ | እግዚአብሔር ይረዳዋል | አብደናጎ | የነጎ አገልጋይ |

በአል የባቢሎናውያን ዋና ጣዖት መጠሪያ፤ አኩ የጨረቃ አምላክ የሚሉት ጣዖት፤ ሻቅ የመሬትና የውበት አምላክ የሚልዋት ጣዖት ነበረች፡፡ ነጎ ወይም ሄቦ የፀሐይ አምላክ የተባለ ጣዖት ነበር፡፡

ይህም አይሁድ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው የደረሰባቸውን ምርኮ አስከፊነትን ያሳየናል፡፡ ይህን ቢታገሱም የባሰ መጣ፡፡ ***"ከንጉሡ መብል ከሚጠጣውም ጠጅ"*** አቀረቡላቸው፡፡ ልጆች ይህ ታዲያ ምን ችግር አለው? እንል ይሆናል፡፡ ለተራ ሰው ችግር የለውም እንደ ዳንኤልና ጓደኞቹ እግዚአ ብሔርን በንጽሕና ለሚያምን ግን ርኩሰት ነበረበት፡፡ ይህ መብል ከተዘጋጀ በኋላ ንጉሡን ይጠብቃሉ፣ ይረዳሉ፣ በጦርነትም ድል ይሰጡታል፤ የሚሆነውም ሁሉ ለሚሉዋቸው ጣዖታት በመሥዋዕትነት ቀርቦ የሚመጣ ነው፡፡ በተጨማሪም አይሁድ በእስራኤል ሕግ እንዳይበሉ የታዘዙት ሁሉ ተቀላቅለው በንጉሡ መብልነት ይመጡ ነበር፡፡

በመሆኑም ዳንኤል ለአምላኩ ሕግና ትእዛዝ ታማኝ ስለነበር ***"በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ እንዳይረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ለመነ።"*** ዳን. ፩፥፰፡፡ የማትፈልጉትን ነገር ሰዎች ሲያመጡባችሁ እንደ ዳንኤል በትሕትና አነጋግሩ፡፡ ዳንኤል የባቢሎን ምርኮ እንደማይቀር ኤርምያስ የተነበየውን ያውቃል፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ መሆኑንም ያምናል፡፡ በመሆኑም በትሕትና ከገዢዎቹ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ እናንተም ትሑታን ሁኑ… ትሕትናውን ያየ ***"እግዚአብሔርም በጃንደረቦቹ አለቃ ፊት ለዳንኤል ሞገስንና ምሕረትን ሰጠው።"*** ዳን. ፩ ፥ ፱፡፡ ይህ ባይሆን ባቢሎናውያን ከንቀት ቆጥረውት በቀጡዋቸው ነበር፡፡ ***"የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች ሸካራ ቃል ግን ቍጣን ታስነሣለች።"*** ምሳ. ፲፭ ፥ ፩፡፡ እኛም ለአምላካችን ስንቀና በትኅትናና በእምነት በመመስከር ይሁን፡፡

***"የጃንደረቦቹም አለቃ ዳንኤልን፦ መብሉንና መጠጡን ያዘዘላችሁን ጌታዬን ንጉሡን እፈራለሁ በዕድሜ እንደ እናንተ ካሉ ብላቴኖች ይልቅ ፊታችሁ ከስቶ ያየ እንደ ሆነ፥ ከንጉሡ ዘንድ በራሴ ታስፈርዱብኛላችሁ አለው።"*** ዳን. ፩፥፲፡፡ አስፋኔዝ የፈራው ቢከሱት ንጉሡ ሊቀጣው ስለሚችል ነው፡፡

www.zeorthodox.org

ዳንኤል መፍትሔ አዘጋጀ፡፡ አስፋኔዝ አራቱ ወጣቶች ላይ የሾመው ሜልዳር የተባለን ሰው ነው፡፡ ዳንኤል ሜልዳርን *"እኛን ባሪያዎችህን ዐሥር ቀን ያህል ትፈትነን ዘንድ እለምንሃለሁ የምንበላውንም ጥራጥሬ የምንጠጣውንም ውኃ ይስጡን፡፡ ከዚያም በኋላ የእኛን ፊትና ከንጉሡ መብል የሚበሉትን የብላቴኖችን ፊት ተመልከት እንዳየኸውም ሁሉ ከባሪያዎችህ ጋር የወደድኸውን አድርግ አለው።"* ሜልዳርም *አሥር ቀን* ፈተናቸው፡፡

ከአሥር ቀንም በኋላ ከንጉሡ መብል ከበሉ ብላቴኖች ሁሉ ይልቅ ፊታቸው አምሮ ሥጋቸውም ወፍሮ ታየ። ሜልዳርም መብላቸውንና የሚጠጡትን ጠጅ አስቀርቶ ጥራጥሬውን ሰጣቸው። እነርሱም በጥሬ እየጾሙ ሥልጠናውን ፈጸሙ፡፡ ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወትና በአካል ያደጉ ክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነቱን ከፍተኛና ከባድ ጾም ይጾማሉ፡፡

ጾም ጸጋና በረከት ያሰጣል፡፡ ‹‹*ለእነዚህም ለአራቱ ብላቴኖች እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ ዕውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው ዳንኤልም በራእይና በሕልም ሁሉ አስተዋይ ነበረ።*›› ዳን ፩ ፥ ፲፯። ሦስቱ ጥበብና ማስተዋልን ዳንኤልም ከእነዚህ በተጨማሪ ሕልምን መተርጎም ተጨመረለት፡፡ ለበጎ ነገር መሪ መሆን የተለየ ጸጋ ያስገኛል፡፡

ከሌሎቹ ጋር በንጉሡ ፊት ቀርበው ሲፈተኑም፡-*"ከብላቴኖቹ ሁሉ እንደ ዳንኤልና እንደ አናንያ እንደ ሚሳኤልና እንደ አዛርያ ያለ አልተገኘም፡፡ በንጉሡም ፊት ቆሙ። ንጉሡም በጠየቃቸው በጥበብና በማስተዋል ነገር ሁሉ በግዛቱ ሁሉ ከሚኖሩ የሕልም ተርጓሚዎችና አስማተኞች ሁሉ እነርሱ አሥር እጅ የበለጡ ሆነው አገኘባቸው።"* ዳን. ፩ ፥ ፱ - ፳፡፡

## ማጠቃለያ

ኃጢአት በጠላት እጅ ያስማርካል። አይሁድ የተማረኩት የነቢያትን ቃልና ትምህርት ባለመስ ማታቸው ነበር። የእኛ ዋና ጠላትም ሞትን የሚያመጣው ዲያብሎስ ነው። ፩ኛ ቆሮ. ፲፭።

ዳንኤልና ሦስቱ ወጣቶች በክፉም ቀን ለእግዚአብሔር ታማኞች ነበሩ። በመከራና በክፉ ቀን መታመን ታላቁና የሚበልጠው ታማኝነት ነው። እናንተም በማንኛውመ ጊዜ ለአምላካችሁ ለልዑል እግዚአብሔር ታማኝ ሁኑ።

www.zeorthodox.org

ጾምና ጸሎት በእምነት የምንፈጽመውና በረከትና ጸጋ የምናገኝበት መሳሪያ ነው። እነ ዳንኤል እንዳይረክሱ ጾምን መረጡ። ክርስቲያኖች በኃጢአት እንዳንረክስ የሥጋን ክፉ ምኞት በጾም እንዋጋዋለን። ክርስቶስም በስሙ አምነን በጾምና በጸሎት ስንጋደልና ስንማጸነው ድል ይሰጠናል።

## ተግባር

ለምትሰሙት የእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሁኑ። ትሕትናና ጹኑ እምነትም ይኑራችሁ።

# ዳንኤል የንጉሡን ሕልም ተረጎመ

## ዐሥራ ሦስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር ምሥጢራትን እንደሚገልጥ መገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ጥበብንና ኃይልን የሰጠኸኝ፥ እኛም የለመንንህን ነገር አሁን ያስታወቅኸኝ፥ አንተ የአባቶቼ አምላክ ሆይ፥ የንጉሡን ነገር አስታውቀኸኛልና እገዛልሃለሁ አመሰግንህማለሁ።"* ዳን. ፪፥፳፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ትንቢተ ዳንኤል ምዕ. ፪ እና ፬፡፡

### መግቢያ

ዳንኤል በባቢሎን ምርኮ ዘመን (ከ586-516 ዓ.ዓ አካባቢ) የተነሳ ሲሆን ትንቢታቸውን በጽሑፍ ካስተላለፉት ነቢያት አንዱ ነው፡፡ ትንቢተ ዳንኤል፣ተረፈ ዳንኤል እና መጽሐፈ ሶስና የዳንኤል መጻሕፍት ናቸው፡፡ ዳንኤል የዘመኑና የወደፊቱን እግዚአብሔር ገልጾለት ጽፏል፡፡ በዛሬው ትምህርት ናቡከደነጾር ያየውን ሕልም ዳንኤል መተረጎሙንና ነዚህም የተገለጸለትን ምሥጢር እናያለን፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ናቡከደነጾር ማነው በኢየሩሳሌም ምን አደረገ?
2. ሦስት የዳንኤል ጓደኞች ማን ይባላሉ?
3. በጾምና ጸሎት ራሳቸውን በመጠበቃቸውና ለአምላካቸው ሥርዓት በመቅናታቸው ምን አገኙ?

### የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

**የተሰወረው የናቡክደነጾር ሕልም፡-** ንጉሡ አንድ ቀን በአልጋው ላይ ሆኖ ሕልም አየና ተነሳ፤ ሕልሙ እጅግ ቢያስጨንቀውም ሕልሙን ማስታወስና መተርጎም አልቻለም፡፡ በቤተ መንግሥቱ ያሉትን ጠቢባን በሙሉ ጠርቶ ሕልሙንና ትርጉሙን እንዲነግሩት ቢጠይቃቸውም መተርጎም አልቻሉም፡፡ ንጉሡም እንዲገደሉ አዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ ዳንኤል ሊገድል ትእዛዝ የተሰጠውን የዘበኞችን አለቃ አርዮክን ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ተፈቀደለት፡፡

**በጸሎት ሕልሙ ከነፍቺው ተገለጠ፡-** ዳንኤል ከሦስት ጓደኞቹ ጋር ጸሎት ያዙ። እግዚአብሔርም ገለጠለት። ወደ ንጉሡ ገብቶም ‹‹***ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ፥ እርሱም በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታውቆታል። በአልጋህ ላይ የሆነው ሕልምና የራስህ ራእይ ይህ ነው።›› ምሥጢርንም የሚገልጠው የሚሆነውን ነገር አስታውቆሃል።››*** አለው፡፡

***ሕልሙ፡-** ዳንኤል ናቡከደነጾርን እንዲህ አለው፡- አንተ፥ ንጉሥ ሆይ፥ ታላቅ ምስል* አየህ ... የዚህም ምስል ራስ ጥሩ ወርቅ፥ ደረቱና ክንዶቹም ብር፥ ሆዱና ወገቡም ናስ፤ ጭኖቹም ብረት፥ እግሮቹም እኩሌ ብረት እኩሌም ሸክላ ነበረ። እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ። የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፥ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጨ፥ በአውድማ እንዳለ እብቅ ሆነ ነፋስም ወሰደው፥ ቦታውም አልታወቀም ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ፡፡

**ፍቺው፡-** ዳንኤል ትርጉምንም ተናገረ፡- ከወርቅ እስከ ሸክላ ያለው የምስሉ አካል ከባቢሎኑ ንጉሥ እስከ ሮም የሚነሱት ነገሥታት ሲሆኑ፤ እጅ ሳይነካው የወረደው ድንጋይም የእግዚአብሔር መንግሥት መሆኑን ተረጎመለት፡፡ ንጉሡም ተደስቶ ከዙፋኑ ተነሳ፤ ለዳንኤልም ሰገደለት፡፡ ***"ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክ፥ የነገሥታትም ጌታ፥ ምሥጢርም ገላጭ ነው ብሎ ተናገረው፡፡"***

***የእግዚአብሔር መንግሥት፡-** ዳንኤል "**በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች።"** ብሎ የመሰከረላት መንግሥት የክርስቶስ ዘለዓለማዊና ሰማያዊት መንግሥት ናት፡፡ ይህች መንግሥት ታላቁ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ **"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ"** ማቴ. ፬ ፥ ፲፯ በትሕትና በመስበክ የመሠረታት ናት፡፡ ሐዋርያት የሰበኩላት፤ እኛም ተስፋ የምናደርጋት ናት፡፡*

www.zeorthodox.org

*ልጆች በዚያች የእግዚአብሔር መንግሥት ጨለማ፣ ሕመም፣ ሞት የለባትም፡፡ አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፥ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤... የዚያች መንግሥት አባላት የሚሆኑት ያመኑ፣ ንሥሓ የገቡና ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉት ናቸው፡፡ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም፡፡ ራእ. ፳፩ ፥ ፳፯፡፡*

## ማጠቃለያ፡-

- እስራኤል በኃጢኣታቸው ተማረኩ፤ ሕዝቡን ፈጽሞ የማይረሳ እግዚአብሔር አይረሳምና፤ ዳንኤልንና ሕዝቅኤል የመሳሰሉ ነቢያት እያስነሳ በጸሎትና በትምህርት ይጠብቃቸው ነበር፡፡
- ናቡከደነጾር ሕልም ቢያልምም ሕልሙ ከነትርጉሙ ጠፍቶበት ነበር፡፡ ዳንኤል በእግዚአብሔር ገላጭነት ተገልጦለት ተርጉሞለታል፡፡ የእግዚአብሔርን ምሥጢር የምንረዳው በጸሎት ነው፡፡
- የእግዚአብሔር መንግሥት አባል ለመሆን ከጸያፍ ነገሮች፣ ከርኩሰትና ውሸት መራቅ ይገባል፡፡

## ተግባር

እንደ ዳንኤል ሊገደሉ የተፈረደባቸውን በጥብብ የምታድኑአቸው ሁኑ፡፡ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበባችሁ በፊት ጸልዩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ነህምያ (አንድ)

## ዐሥራ አራተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የነበረውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ማጥናት፡፡ ከነህምያ መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራበትን መንገድ መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"አትፍሩአቸው ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ፥"*** ነህ. ፬ ፥ ፲፬፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** መጽሐፈ ነህምያ

## መግቢያ

ባለፉት ተከታታይ ትምህርቶች አይሁድ በባቢሎናውያን በተማረኩበት ዘመን የተነሱትን ነቢያት አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከምርኮ በኋላ የምርኮው ዘመን ማብቂያ ላይ ከተነሱት የእግዚአብሔር ሰዎች አንዱ የሆነውን ነህምያን እናያለን፡፡

***መምህር፦*** ልጆች ትምህርቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው እያነበቡ እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### ነህምያ

***"እግዚአብሔር መጽናኛ ነው (አለው፡፡)"*** ማለት ነው፡፡ በፋርስ ንጉስ በአርጤክስስ ዘመነ መንግስት ጠጅ አሳላፊ ነበር፡፡ ነህ ፩ ፥ ፩፣ ፪ ፥ ፲፩፡፡ ልጆች በድሮ ዘመን ጠጅ አሳላፊነት ለታማኞች ብቻ የሚሰጥ ሥራ ነበር፡፡ ነህምያ በዘሩባቤል መሪነት ከተመለሱት አይሁድ አንዱ ነው፡፡ ነህ. ፯፥፯፣ ዕዝ ፪፥፪፡፡ ነህምያ ከ፬፻፵፭ - ፬፻፵፯ ቅ.ል.ክ. የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለማሠራት አስፈቀደ፡፡ ነህ ፪፥፩ ፣ ፭፣፯፣፲፩፡፡

የከተማያቱን ፍርስራሽ አይቶ ከተማይቱን ለማሠራት ሹማምንትን አነሣሣ፡፡ ተቃውሞውን ሳይፈራም በሃምሳ ሁለት ቀናት የኢየሩሳሌምን ቅጥር አሠራ፡፡ ነህ ፪፥፲፪፣ ፯፥፲፭፡፡

በመሪነትና ሕዝቡን በመምከር ለ12 ዓመታት በኢየሩሳሌም ቆየ፡፡ ነህ ፭ ፥ ፲፬፣ ፲ ፥ ፩፣ ፲፫ ፥፯፡፡ ከዚያም ወደ አርጤክስስ ሄዶ እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፡፡ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን አይቶ አረመ፡፡ ነህ ፲፫፡፡ ነህምያ ካህን ወይም ሌዋዊ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ አባል (ምዕመን) ብቻ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናገኛቸው መጻሕፍት አንዱን የጻፈልንን የነህምያን መጽሐፍ ከዚህ ቀጥለን እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

# መጽሐፈ ነህምያ

## ሀ.አጠቃላይ የመጽሐፉ ይዘት

ነህምያ ከምርኮ በኋላ ሕዝቡን ለበጎ ሥራ የመራ ነው። ከነበረበት ከሱሳ ግንብ ሁለት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዷል። የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት ከሆነው ከዚህ ታሪክ ተነስተን መጽሐፈ ነህምያን በሁለት አበይት ክፍሎች እንከፍለዋለን።

የመጀመሪያው የኢሩሳሌምን አጥር ለመስራት ነው።(፩-፲፪) በዚህ ክፍል ነህምያ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅጥሩን በብዙ ፈተና እንደሠራ እናነባለን።

ሁለተኛው ክፍልም ወደ ሱሳ ሄዶ ለሁለተኛ ጊዜ መመለሱን ይተርካል።(፲፫) በዚህም ሥርዓተ መቅደስንና ሕግጋተ እግዚአብሔርን ያበላሹትን መገሰጹንና ማረሙን እናነባለን።

## ለ. የመጽሐፈ ነህምያ ዝርዝር ይዘት

ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ሲሰማ ያደረገው ፩፥፩ -፪፥፳።

### ሀ. ሰማ

ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ወገኖቹ ጠየቀ። ከዚያ የመጡት ወንድሙ አናኒ እና ሌሎች ሰዎች የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረሱንና የቀሩት አይሁድ በነቀፌታ እንዳሉ ነገሩት።

### ለ. አዘነ ፣ አለቀሰ ፣ ጾመ ፣ ጸለየ

ነህምያ አሳዛኙን ታሪክ ሲሰማ ከልቡ አዝኖ አለቀሰ፤ በጾምና በጸሎትም ወደ እግዚአብሔር ለመነ።***"መከራን የሚቀበል ...ቢኖር ይጸልይ"*** ያዕ. ፩ ፥ ፲፫።

### ሐ. ንጉሡን አስፈቀደ

በጸሎት እግዚአብሔርን ከጠየቀ በኋላ በእግዚአብሔር ወደ ተሾመው ንጉሥ ቀርቦ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለማነጽ እንዲችል አስፈቀደ። ልጆች ማንኛውም ሥራ የሚመለከተውን አስፈቅዳችሁ ብቻ ሥሩ።

## የሥራ መጀመሪያ በኢየሩሳሌም ፪ ፥ ፱ - ፳

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ፥ ከሥራው በፊት ዝግጅቱንም እንደሚከተለው አከናወነ፡-

***ሀ.ተጉዞ ኢየሩሳሌም ደረሰ***

ለሹማምንቱ የንጉሡን ፈቃድ አስታወቀ። ሦስት ቀንም ተቀመጠ።

www.zeorthodox.org

*ለ. ቅጥሩን ጎበኘ*

*ሥራውን* ከመጀመሩ በፊት የሚሠራውን አየ።

*ሐ. ሕዝቡን አበረታታ*

*ሥራው* በግል አይፈጸምምና ሕዝቡን ጠርቶ አበረታ ለሥራም አነሳሳ።

*መ. የመጀመሪያው ተቃውሞ*

ለእስራኤል መልካም የሚያስብ መምጣቱን የማይወዱት ጦቢያ፣ ሰንባላጥና ጌሳም ተቃውመው፣ በንቀት አፌዙባቸው። ነህምያም ***"የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን"*** ነህ ፪ ፥ ፳ አለ።

የቅጥሩ አዳሾች ዝርዝር (፫ ፥ ፩ - ፴፫)

ለሥራው የተሰለፉት በዚህ ተጽፈዋል። መልካም ሥራ በሕይወት መጽሐፍ ያጽፈናል። ለሥራ ስንነሳ በስሜት መነሳት የለብንም ያለንን አቅም ማወቅ አለብን። ቅጥሩን ያደሱት ሰዎች መዘርዘ ራቸውም ውለታ ማስታወስን ያስተምረናል። ዝርዝሩ በሰሩበት በር በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በደቡብና በምሥራቅ አቅጣጫ ተቀምጧል።

## የጥገናው ሁለተኛ ተቃውሞ (፬ ፥ ፩ - ፳፫)

ተቃውሞውን ችል ብለው ቅጥሩን ሠሩ። በዚህ ጊዜ እነ ሳንባላጥ ተቆጡ። ሁለተኛ ዙር ተቃውሞ ተነሳ። ይህ ተቃውሞ በንቀት በፌዝና በዛቻ የተገለጠ ነበር።

*ሀ. ንቀትና ፌዝ*

ሰንባላጥ በንቀት ***ቀበሮ ቢመጣ ያፈርሰዋል*** አለ። ነህምያም ***"አምላካችን ሆይ፥ተንቀናልና ስማ"*** አለ። ክፉውን በጸሎት ኃይል እየመከቱ ሥራቸውን ቀጠሉ።

www.zoorthodox.org

*ለ. ዛቻ*

ሕዝቡም ለሥራው ልቡ ጨከነ። በአራቱም አቅጣጫዎች የተሰራው አጥርም እኩሌታ ተጋጠመ። በዚህ እነኚሁ ተቃዋሚዎች ***ኢየሩሳሌምን ይወጉና ያሸብሩ ዘንድ ሁሉም በአንድነት ተማማሉ።*** ነህምያና ሕዝቡም ጸለዩ። ከዚያም ሕዝቡን አስታጥቆ። ጠባቂዎችን አደረገ። አለቆችንም ***"አትፍሩአቸው ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ።›››*** አለ። ሥራውንም ቀጠለ።

*ሐ. በተሻለ ዝግጅት ሥራቸውን ቀጠሉ።*

ሕዝቡ ይዋጉና ያሸብሩ ዘንድ የተማማሉትን ሲሰማ ፈርቷል። ሆኖም ሥራው አልቆመም። ነህምያም በቀንና በሌሊት ጠባቂዎች አደረገ። አናጢዎችም በአንድ እጃቸው ይሰሩ በአንድ እጃቸው የጦር መሳሪያቸውን ይይዙ ነበር። ተበታትነው እየሠሩ አደጋ ቢመጣ ለመሰብሰብ እንዲችሉ መለከት የሚነፋ ተደረገ። ልጆች ስንሠራም ሆነ ስንማር ከጸሎት ጋር ዝግጅት በማድረግ መሆን አለበት።

## ማጠቃለያ

ልጆች ለቤተ ክስቲያንና ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ለመስራት፤ ታማኝ መሆን፣ ትጋትና የመንፈስ ጥንካሬ ያስፈልጋል። ይህን ለማዳበር በጥናትና ቤተሰብን በማገዝ ትጉኅ ሁኑ። ለመልካም ሥራ እተጋችሁ ተቃውሞ ቢደርስባችሁ አትደናገጡ። እየጸለያችሁ ሥራችሁን ቀጥሉ፣ አጥኑ።

## ተግባር

የተሰጣችሁን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቡ፣ ለእግዚአብሔር ቤትና ለወገኖቻችሁ ቅናት ይኑራችሁ።

www.zeorthodox.org

# ነህምያ (2)

# ዐሥራ አምስተኛ ሳምንት

**<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>፡-** ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የነበረውን የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ መረዳትና ከነህምያ መንፈሳዊ ሥራ የሚሰራበትን መንገድ መገንዘብ፡፡

**<u>የሚጠና ጥቅስ</u>፡-** ***" ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፥ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል? "*** ነህ. ፮ ፥ ፫

**<u>ተጨማሪ ምንባብ</u>፡-** መጽሐፈ ነህምያ ከምዕራፍ ፭ እስከ ፲፫

## መግቢያ

ባለው ሳምንት ትምህርታችን ነህምያ የኢሩሳሌምን አጥር ለመሥራት መምጣቱን ተምረናል፡፡ ተቃውሞ ቢነሳበትም የአጥሩን እኩሌታ መስራቱንም አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ቀጣዩን ክፍል እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### *የውስጥ ችግሮች:*

አይሁድ በምርኮው ምክንያት ምጣኔያቸው ወርዷል፡፡ ሕዝቡም በረሃብና በጦርነት ደኅይቷል፡፡ አለቆችና ሹማምንትም መሬት፣ እርሻ፣ ቤትና ልጆቻቸውን በባርነት እየያዙ ብድር ይሰጡ ነበር፡፡ ነኅምያ የሕዝቡ አለቃ ተደርጎ ከንጉሥ አርጤክስስ ተሹሟል፡፡ እርሱም ለድሆች የሚያዝን ነበር፡፡ ሆኖም ለሥራ የተነሱት ሹማምንት ሕዝቡን በወለድ የሚያስጨንቁ ነበሩ፡፡እናም ድሆች ጮሁ፡፡

*ሀ. የድሆች ሮሮ ተሰማ፡-* አንዳንዶቹ ድሆች የሚበሉት ስላጡ፤ ሌሎቹም ያላቸው በእዳ ስለተያዘ ጮሁ፡፡ ይህን ክፋት ያደረጉትም በወንድሞቻቸው ላይ የተሾሙት አይሁድ ናቸው፡፡

*ለ. የዕዳ መሠረዝ፡-* ነህምያ ወንድሞቻቸውን በእዳ ስለሸጡ አለቆችን ተቆጣ፡፡ እዳቸውን እንዲሰርዙም በካህናት አስማለ፡፡ እነርሱም ይህንኑ ፈጸሙ፡፡

*ሐ. የነህምያ አርአያነት፡-* ነህምያ ሌላውን እየተቆጣ እርሱ በድሎት አልኖረም፡፡ የሕዝቡ አለቃ ሆኖ በመሾሙ የሚያገኘውን ስንቅ ከድሆች አልተቀበለም፡፡ እንዲያውም መቶ ሃምሳ ሰዎች በማዕዱ ያስቀምጥ ነበር፡፡ ይሕን ሁሉ ሲያደርግም ለሰው ሳይሆን ***"አምላኬ ሆይ፥ ለዚህ ሕዝብ ያደረግሁትን ሁሉ ለበጎነት አስብልኝ"*** ነህ. ፭ ፥ ፲፱ እያለ ነበር፡፡

www.zoorthodox.org

## ልዩ ልዩ ፈተና ውስጥም የቅጥሩ ሥራ ቀጠለ (፮፥፩ - ፮፥፲፱)

የበሮች ሳንቃ ብቻ ሲቀሩ ቅጥሩ ተሰርቶ አለቀ። እነ ጦቢያ ሰንባላጥና ጌሳም ይህን ሰሙ። ስልት ቀይረው በሌላ መንገድ ሥራውን ለማስቆም ተነሱ። እንዲህም አደረጉ፡-

*ሀ. ነህምያ ለማጥመድ ሙከራ ተደረገ፡-* ጦቢያና ሰንባላጥ በነህምያ ክፉ ለማድረግ አስበው፡- በንጉሡ ለማመጽ መፈለግህ ተሰምቶብሃል እና እንድንማከር ወደ መንደሮችና ብለው ላኩበት። እርሱም ***"ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፥ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል?"*** ነህ. ፮ ፥ ፫ አለ። ይህንንም አምስት ጊዜ አደረጉበት። በደብዳቤም አስፈራሩት ነህምያም ሰንባላጥን ***"አንተ ከልብህ ፈጥረኸዋል እንጂ እንደ ተናገርኸው ነገር ምንም የለም.."*** አለው፡፡***"አሁንም፥አምላክ ሆይ፥እጄን አበርታ።"*** ነህ ፮ ፥ ፰ -፱ ብሎ ጸለየ፡፡ ይህ ያልተሳካላቸው ሰዎች በነህምያ መንፈሳዊነት ለመግባት ሌላ ወጥመድ አዘጋጁ፡፡

*ለ. ሐሰተኛ ነቢያት መግዛት፡-* ጦቢያና ሰንባላጥ በብር የገዙዋቸው የሐሰት ነቢያት ***በቤተ መቅደስ እንገናኝ፤*** አሉት። ነህምያም ***"እንደ እኔ ያለ ሰው*** (ካህን ያልሆነ ማለቱ ነው፡፡)***የሸሸና፥ ነፍሱንስ ያድን ዘንድ ወደ መቅደስ የገባ ማን ነው? እኔስ አልገባም"*** አለ። እንደተለመደው ጸሎቱን አድርሶ ሥራውን ቀጠለ።

*ሐ. ቅጥሩ ተጠናቀቀ፡-* በ52 ቀናት ሥራው ተጠናቀቀ። ክፉዎችም አንገታቸውን ደፉ።

## ከምርኮ ተመላሾች እና በከተሞች መቀመጣቸው(፯)

የኢየሩሳሌም ቅጥር ከተሰራ በኋላ ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ በቅጥሩ ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። ይህንንም፡- የኢየሩሳሌም ጥበቃ በማዘጋጀት ጀመረው። የተመላሾችን ዝርዝር አገኘ፣ አጣራ፣ በእየከተሞቻቸው ተቀመጡ።

## የዕዝራ ስብከትና የሕዝቡ ንስሐ።( ፯ - ፲)

www.zeorthodox.org

ሕጉ መጽሐፍ በትርጎሜ ተብራርቶ ተነበበ፣ ከዚያም የዳስ በዓል አከበሩ። ሕዝቡም የጾም፣ የንስሐና የኑዛዜ ቀን አደረጉ። እግዚአብሔር ያደረገላቸው ሁሉመወ ተተረከ። ሕዝቡም አምላካቸውን በመበደ ላቸው ኃጢአታቸውን ተናዘዙ፤ቃል ኪዳናቸውንም አደሱ።

## አዲሶቹ ነዋሪዎች እና ካህናቱ (፲፩ - ፲፪)

አዳዲስ ነዋሪዎች በይሁዳና በኢየሩሳሌም ሰፈሩ። ካህናትና ሌዋውያን ተዘርዝረው ታወቁ ቦታም ተሰጣቸው። ቅጥሩ ተመረቀ፣ ነህምያ ቅጥሩ ሊሰራለት ያስፈለገውን ሕዝብ በቦታው ካስገባ በኋላ ሥራውን አስመረቀ። ከዚያም ወደ ንጉሡ ወደ ሱሳ ግንብ ተመለሰ።

## የነህምያ ሁለተኛ የአስተዳደር ዘመን (፲፫)

ነህምያ በሌለበት ብዙ ስህተቶች ተሠሩ። ከእነዚህ አንዱ በቤተ መቅደሱ የማይገባቸው ሰዎች መግባታቸው ነበር። በመሆኑም ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፣ ጦቢያን አባረረ፣ ድጋሚ አድሶ ሕዝቡን አደራጀ፣የቤተ መቅደስ አገልጋዮችን ድርሻ ወሰነ።

ሰንበትን ቀደሷት፣ የተበላሸ የጋብቻን ሕይወት የማንጻት ሥራ ሠራ፣ በኵራት እንዲሰጥም አደረገ።

## ማጠቃለያ

መንፈሳዊ ሥራ ፈተና አለው። ቢሆንም ፍሬው ጣፋጭ ነው፣ የድል ሕይወትም ነው።

## ተግባር

ዘወትር በካህናት፣ በመምህራን፣ በሽማግሌዎች፣ በወላጆች፣... የምትመከሩት ስሙ፣ ምክሩንም በተግባር አውሉት።

www.zeorthodox.org

# ሕፃኑን እና እናቱን ይዘህ ሽሽ

## ዐሥራ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ወርኃ ጽጌን መነሻ በማድርግ ስለ መንፈሳዊው ሕይወት መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች፡››***

ራእ. ፲፪፥፮

**ምንባባት፡-** ራእየ ዮሐንስ ፲፪ ፥ ፩ - ፮ እና ማቴ. ፪ ፥ ፩ - ፳፡፡

## መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ሰብአ ሰገል የተባሉ ጥበበኞች ***የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው? እያሉ*** ከሩቅ አገር መጡ፡፡ በነርሱም የተነሣ ከተማይቱ ታወከች፡፡ በዚህ ግዜ የኢየሩሳሌም ንጉሥ(ሄሮድስ) ንግሥናየን የሚወስድብኝ ንጉሥ ተነሳብኝ ብሎ ተጨነቀ ከአማካሪዎችም የአይሁድ ንጉሥ የሚወለድበት ቦታና ዘመን አወቀ፡፡ እርሱም ሰብአ ሰገልን ጠርቶ ቤተልሔም በተባለች ቦታ እንደሚወለድ ነገሮ፤ ካገኙት እርሱም ሊሰግድለት ስለሚፈልግ ተመልሰው እንዲነግሩት አሳስቦ ሰደዳቸው፡፡ ክፉ ሓሳቡ ግን ሥልጣኑን እንዳይቀማው ማስገደል ነበር፤ ሰብአ ሰገልም በኮከብ ተመርተው ጌታችን ካለበት ደረሱ፤ በዚያም ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር አግኝተው ሰግደው ስጦታ ገበሩለት፡፡ የሄሮድስን ክፉ ሐሳብ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፡፡

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል ያሰበውን ለመፈጸም እንዳላስቻሉት ባወቀ ጊዜ በቤተልሔም እና በአካባቢዋ የተወለዱትን ሕፃናት ባስገድል ክርስቶስንም አገኝዋለሁ ብሎ በስጦታ ስም ሁለት ዓመት የሞላቸውን ሕፃናት ሰብስቦ ለመግደል ተዘጋጀ፡፡

በዛሬው ትምህርትታችን በዚሁ ምክንያት ጌታችን ከእመቤታችን እና ከቅዱሳኑ ጋር መሰደዱን አስመልክቶ በየዓመቱ በዚህ ወቅት ቤተክርስቲያን የምታስበውን ታሪክ እና ትምህርት እናያለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

በዚህ ምክንያትም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ እናቱ ድንግል ማርያምን እና ልጅዋን መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዞ ወደ ግብፅ እንዲሸሽ ነገረው፡፡ ዮሴፍ የታዘዘውን ፈጸመ፡፡

ሄሮድስም ሰብዓ ሰገል ***የአይሁድ ንጉሥ*** ማቴ. ፪ ፥ ፩ - ፪ ያሉትን በሰማ ግዜ መንግሥቱን የሚቀማው መስሎት ከእነዚህ አንዱ ክርስቶስ ነው ብሎ አስቧልና - ***ሕፃኑን ኢየሱስን*** ያገኘ መስሎት

ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን አስፈጀ ፣ የክርስቶስ መንግሥት ግን ከምድር አልነበረችም ሰማያዊት ነበረች እንጂ። ዮሐ. ፲፰ ፥ ፴፮።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተገደሉት ሕፃናት መካከል እንደሌለ ሄሮድስ ሲያወቅ፤ ተከትለው እንዲይዟቸው ወታደሮች ላከ።

በቤተ ክርስትያናችን ይህን ታሪክ የሚያብራሩልን መጻሕፍት አሉ፤ ከነኚህ መጻሐፍት እንደምንናነበው ፡-

በአንድ ወቅት የሄሮድስ ወታደሮች የሄዱበትን አቅጣጫ ተከትለው ሊይዝዋቸው ሲቀርቡ፤ በዋሻ እና በዛፍ ውስጥ በመከለል አለፏቸው። የእግዚአብሔርመልአክም ሊረዳቸው ከእነርሱ ጋር ነበር። ምግብ፤ መጠለያ እና ውኃ ፍለጋ በጣም መንከራተታቸውንም በዚሁ መጽሐፍ እናነባለን። ከዚያም በበረሐ የሚኖሩ ሽፍቶች አጋጥመዋቸው ልጅዋን እንዳይገድሉባት እመቤታችን ያዘነችውን መሪር ሐዘን ስናስብ አረጋዊው ስምዖን ይህ ስደት ከመነሳቱ ከሁለት ዓመት በፊት የተነበየውን ያስታውሰናል፡- ***‹‹እናቱን ማርያምንም፡- እነሆ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፤ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት››*** ሉቃ. ፪ ፥ ፴፬ - ፴፭።

ወንጌላዊው ዮሐንስ የግብፁን ስደት በራእይ መጽሐፉ እንደሚከተለው ጽፏል።***“ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክበት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። እርስ ዋም ፀንሳ ነበር፣ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች። ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶችም ነበሩት....ዘንዶውም ሴቲቱ በወለድች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። ሴቲቱም ሺሕ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።”*** ራእ. ፲፪ ፥ ፩ - ፮።

www.zeorthodox.org

ሐዋርያው ሴቲቱ ብሎ የገለፃት ድንግል ማርያም ስትሆን፣ ልጅዋ የተባለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ያሳደዳት ዘንዶም ሄሮድስ ሲሆን በእግዚአብሔር የተዘጋጀው ሥፍራ ግብፅ ነበር። 1260 ቀናቱም 3 ዓመት ከመንፈቅ ሲሆን፤ ይህም ሄሮድስ እስኪሞት በግብፅ የቆዩበት ጊዜ ነበር። ይህን የስደት ወቅት ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ባሉት ፵ ቀናት በየዓመቱ በቤተ ክርስቲያናችን እናስበዋለን።

## ማጠቃለያ

### ደጋጎች ይሰደዳሉ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰማያዊውን ንጉሥ ክርስቶስን ወልዳ ወደ ግብፅ ተሰዳለች። ይህም ሆኖ አላማረረችም። አንድ ሰው እውነተኛ ስለሆነ ብዙ መከራን ይቀበላል። የእውነት መጨረሻዋ ግን መልካም ነው። *"በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና። ኃጢአትን አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሱ፤ ምን ክብር አለበት? ነግር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሱ፤ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሎአልና።"* ፩ኛ.ጴጥ. ፪ ፥ ፲፱።

### ክፉ ምኞትን መግዛት ይገባል

ሄሮድስ ፍላጎቱ ሥልጣኑን ማስጠበቅ ብቻ ነበር። ለዚህም ነው ሌላ ንጉሥ ተወለደ ሲባል ዐሥራ አራት ሺሕ እልፍ ሕፃናትን ያስፈጀው።

ማናቸውም ምድራዊ እና ቁሳዊ ምኞቶች በአግባቡ ካልተያዙ አደገኛ ናቸው። ክፉ ቁሳዊ ምኞት የሚያዳብሩ ሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት ሲሉ ጨካኝ ይሆናሉ። ብዙ ወንጀሎች የሚፈጽሙት ለቁስ፣ ለገንዘብ፣ ለአልኮልና ለመጠጥ.... ካለ ጠንካራ ምኞት የተነሳ ነው። ለዚህም ነው ያዕቆብ ‹‹*ነገር ግን እንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኃላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኂላ ሞትን ትወልዳለች* ›› ያዕ. ፩ ፥ ፲፩ ያለን።

እኛም ‹‹*የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።*›› ተብሎ እንደተጻፈ ‹‹*በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ ፡*›› ገላ. ፫ ፥ ፳፬ - ፳፫።

| <u>*መዝሙር*</u> | <u>*ትርጉም*</u> |
| --- | --- |
| እስከ ማዕዜኑ እግዝእትየ | እስከ መቼ ድረስ እመቤቴ |
| ውስተ ምድረ ነኪር ትኄልዊ | ባዕድ ሀገር ትኖርያለሽ |
| ገሊላ እትዊ (4) ሀገርኪ ገሊላ እትዊ | ገሊላ ግቢ (4) ሀገርሽ ገሊላ ግቢ |

www.zeorthodox.org

# የምሥራቹ መልአክ - ቅዱስ ገብርኤል

## ዐሥራ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ቅዱሳን መላእክት መገንዘብ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"መልአኩም መልሶ፦ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥"*

*ሉቃ. ፩ ፥ ፲፱።*

**ምንባብ፡-** ሉቃ. ፩ ፥ ፳ እስከ ፍጻሜ፣ ትንቢተ ዳንኤል ፫ ፥ ፩ እስከ ፍጻሜ።

## መግቢያ

የእግዚአብሔር መልእክተኞች መላእክት ስለኛ ይጸልያሉ፣ ይረዱናልም። ዛሬ ለሰው ልጆች መልካም ዜና ያበሰረውን የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት እና ሠለስቱ ደቂቅን ማዳኑን እንማራለን፡-

## የሳምንቱ ትምህርት

የሰው ልጆች ድኅነት ሲታወጅ የተላከው መልአክ **ቅዱስ ገብርኤል** ነው።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ በተገለጠለት በ6ኛው ወር ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትጸንስና እንደምትወልደው አበሠራት፤ *"ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።"* እርስዋም *ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ብላ አሰበች።* መልአኩም *ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።* ማርያምም *ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው።* መልአኩም *መንፈስቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።እነሆ.. ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ወራት ወንድ ልጅ ፀንሳለች ይህ ስድስተኛ ወር ነው።ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። እርስዋም እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች።" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርስዋ ተጸነሰ።*

www.zeorthodox.org

ሦስቱ ወጣቶች የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነጾር ላቆመው ጣዖት *አንሰግድም* በማለታቸው ወደ ሚነደው እቶን ሲጣሉ፤ እሳቱን ሊያበርድላቸው የተላከው ***ቅዱስ ገብርኤል*** ነበር። መላእክት

ለተልእኮ ሲላኩ ቁጥራቸው ብዙም አንድም ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ክፍልም በታሪኩ ጎልቶ የወጣው የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት ነው፡፡ ታሪኩም እንዲህ ነበር፦

ናቡከደነፆር ዱራ ሜዳ በተባለ ቦታ ትልቅ ጣዖት አቆመ፤ ከዚያም ላቆመው ምስል ሁሉም እንዲሰግዱ አዋጅ አስነገረ ሁሉም ለምስሉ ሲሰግዱ አንሰግድም ያሉ ሦስቱ ወጣቶችን ከለዳውያን ከሰው በንጉሡ ፊት አቆሟቸው ንጉሡም በታላቅ ቁጣ ካልሰገዱ በሚነድ እቶን ውስጥ እንደሚጣሉ አስጠነቀቃቸው፡፡

እነርሱም ‹‹***ንጉሥ ሆይ እኛ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም፡፡ የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፤ ንጉሥ ሆይ ነገር ግን እርሱ ባያድነን፤አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት፡፡***››

ናቡከደነፆር ተቆጥቶ ሲድራቅ ሚሳቅ እና አብደናጎም ታስረው በሚነድ የእሳት እቶን እንዲጣሉ አደረገ የጣሉዋቸውንም ሰዎች የነበልባሉ ወላፈን ገደላቸው፡፡ በዚያን ጊዜም ንጉሡ ባየው ተደነቀ ‹‹***ሦስቱ ሰዎች አስረን በእሳቱ ውስጥ ጥለን አልነበረም... እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ ምንም አላቆሰላቸውም የአራኛውም መልክ የአማልክትን መልክ ይመስላል አለ፡፡***››

ወጣቶችንም ኑ ውጡ ብሎ ጠራቸው የራሳቸው ጠጉር ሳይቃጠል ሰናፊላቸውም(ልብሳቸውም) የጢስ ሽታ ሳይኖረው ወጡ፤ ናቡከደነፆርም ‹‹***መልአኩን የላከ... በእርሱ የታመኑትን ባርያዎቹን ያዳነ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎንም አምላክ ይባረክ፡፡***›› አለ፡፡ ዳን ፫ ፥ ፩ - ፴፡፡ ያም መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነበረ፡፡

| ***መዝሙር*** | ***ትርጉም*** |
|---|---|
| ገብርኤል ይቤላ ለድንግል በቃሉ | ቅዱስ ገብርኤል ማርያምን አላት |
| ትወልዲ ፍስሐ ለኩሉ(2) | ለሁሉ ደስታ የሚሆነውን ትወልጃለሽ |

www.zeorthodox.org

***መዝሙር***

እንደ አናንያ እንደ አዛርያ እንደ ሚሳኤል አጽናን እኛን

አጽናን እኛን (3) አጽናን በእምነታችን

# ቅዱስ ኒቆላዎስ - ሊቀ ጳጳስ

## ዐሥራ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቅዱሳንን በሚገባ አውቀን እንድናከብራቸው እና እኛም እግዚኣብሔርን እንዴት ደስ እንደምናሰኘው መግለጽ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።" ራእ ፪ ፥ ፲ - ፲፩

**ምንባብ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ (የተሰጡትን ጥቅሶች በሚገባ አንብብዋቸው)፤ መጽሐፈ ስንክሳር የታኅሣስ 10 ።

## መግቢያ

በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ የተከተለውን የቅዱስ ኒቆላዎስን መንፈሳዊ ሕይወት ተመርኩዘን እንማራለን።

ወደ ዋናው ትምህርት ከመግባታችን በፊት ስለ ሳንታ ክላውስ (Santa claus) የምታውቁትን ለመምህር አስረዱ።

## ልደትና እድገቱ

ኒቆላዎስ - የሕዝብ አሸናፊ ማለት ነው።ሀገሩ ሜራ ሲባል በጥንትዋ ሊቅያ (Lycia) በዛሬዋ ቱርክ የምትገኝ ታሪካዊት ከተማ ናት። ኒቆላዎስ አባቱ ኤጲፋንዮስ እናቱ ዮና ይባላሉ። እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባዕለጸጎች ነበሩ። ልጅ ግን አልነበራቸውም።

እግዚአብሔር ልጅ እንዲሠጣቸው ሲለምኑ ኖረው መውለጃቸው ሲያልፍ መለመን ተዉ። ሥራው ድንቅ የሆነ ፈጣሪያችን ልዑል እግዚአብሔር ግን ጊዜውን ጠብቆ ልጅ ሠጣቸው። ስሙንም ኒቆላዎስ አሉት።

www.zeorthodox.org

ሲወለድ በታየው በሕጻንነቱ በነበረው መንፈሳው ሥራ ሁሉም ይደነቁ ነበር። ትኩረቱም የሕይወት ምንጭ የሆነው መንፈሳዊው ምግብ ቃል እግዚአብሔርን መመገብ ነበር። እድሜው ለትምህርት ሲደርስም ወላጆቹ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት እንዲማር ላኩት።

## መንፈሳዊ አገልግሎት

ትምህርቱን በሚገባ አጠናቀም፣ መንፈሳዊ ሥራን በየቀኑ የሚጨምር ሆነ። የአጎቱ ልጅ

በአበምኔትነት ወዳለበት ቦታም ሄዶ በድንግልና መኖር ጀመረ፡፡ በፍጹም ተጋድሎ እየኖረም በ19ዓመቱ ቅስና ተቀበለ፡፡ እግዚአብሔርም ድንቅ ተአምር መፈጸምንና ድውያንን የመፈወስም ጸጋ ሰጠው፤ በተሠጠው ጸጋም፡- ከሰዎችና ከሚያመልኳቸው ዛፎች አጋንንት አወጣ፤ በርካታ በሽተኞችንም ፈወሠ፤ ትንሽ እንጀራ ባርኮም ብዙ ሕዝብ መገበ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ‹‹***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ፡፡***›› ዕብ.፲፫ ፥ ፫ ተብሎ እንደተጻፈም፤ አራት ሴት ልጆች የነበሩትንና ከሀብታምነት ወደ ፍጹም ድኅነት የተሸጋገረን ሰው ረድቷል፡፡

## ታሪኩም እንዲህ ነው

ይህ ሰው ሴቶች ልጆችን መዳርና መመገብ ስላቃተው፡፡ በዝሙት እንዲኖሩ ቤቱን የዝሙት ቤት ሊያደርግ ሲዘጋጅ አባ ኒቆላዎስ በእግዚኣብሔር ጸጋ ነገሩን አውቆ ወደዚህ ሰው ቤት በሌሊት ሄደ፡፡ ወንጌል ‹‹***ስጡ ይሠጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና***› ሉቃ. ፮ ፥ ፴፰ እንዳለ በመጀመሪያ ፪ ዲናር ወርቅ በበሩ ሥር አስቀምጦለት ተሰወረ፡፡

በዚህም ጌታችን ‹‹***አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል፡፡***›› ማቴ. ፮ ፥ ፫ - ፬ ያለውን ቃል ፈጸመ፡፡ ሰውየው ጠዋት ሲነሣ የወርቅ ዲናሩን አገኘና ፈጣሪውን አመስግኖ የመጀመሪያይቱን ልጅ ዳራት፡፡

ለሁለተኛ እና ሦስተኛዋም አባ ኒቆላዎስ ተደብቆ ሰዉየዉን ረዳው ሰውየዉም እግዚኣብሔርን አመስግኖ ልጆቹን ዳረ፡፡ በመጨረሻም ሰዉየዉ ገንዘቡን የሚሰጠው ማን? መሆኑን ለማወቅ ነቅቶ ሲጠብቅ ቅዱሱ እንደተለመደው ወርቁን አስገብቶ ሲሄድ ደረሰበት፡፡ አባ ኒቆላዎስ መሆኑን ሲያውቅም እግሩ ላይ ወድቀው ከልጆቹ ጋር አመሠገኑት፡፡

ወንጌል በዚህ ምድር ብቻ ከሰው የሚመሰገኑ ‹‹***ዋጋቸውን ተቀብለዋል***›› እንዳለ ሰማያዊውን ዋጋ እንዳያስቀሩበት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ነግሮአቸው ሄደ፡፡

www.zoorthodox.org

**ጵጵስና፡-** ***"ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው፡፡"*** ፩ኛ ጢሞ. ፫፥፩ በሕልሙ ዙፋንና የከበረ የክህነት ልብስ ሲሠጠውና ልብሱን ለብሶ በዙፋኑ እንዲቀመጥ ሲያዘውም አየ፡፡ **ዳግመኛም** እመቤታችን የክህነት ልብስ ጌታችንም ወንጌል ሲሠጡት አየ፡፡ የሜራ ኤጲስቆጶስ ሲያርፍም፥ የእግዚአብሔር መልአክ ለሮሙ ሊቀ ጳጳሳት ተገልጦ በሜራ መንበር የሚተካው አባ ኒቆላዎስ መሆኑን ነገረው፡፡ ያም ሊቀ ጳጳሳት ለሕዝቡ ነገራቸው አምነውም አባ ኒቆላዎስን በሀገራቸው ኤጶስቆጶስነት ሾሙት፡፡ ምዕመናንን በታማኝነት እያገለገለም ሳለ ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ ተነሳ፡፡

**ፈተና፡-** ***"ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው።... እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።" ራዕ. ፪ ፥ ፲ - ፲፩***

በዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ እና ጣዖት እንዲያመልኩ የሚያስገድድ አዋጅ ወጣ፤ ቅዱስ ኒቆላዎስም ምዕመናን እግዚኣብሔርን በማመን እንዲጸኑ ያስተምር ነበር። በራእየ ዮሐንስ **"ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው።... እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።"** *ራዕ. ፪ ፥ ፲ - ፲፩* ተብሎ እንደተነገረ። ዲዮቅልጥያኖስ ምንም ጥፋት ሳያገኝበት አቡነ ኒቆላዎስን በብዙ መከራ አሠቃየው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እንደ ቅዱስ ቃሉ አጸናው፤ *ሥቃዩም* አልጎዳውም።

ማሰቃየቱ ያልጠቀመው እና የሠለቸው ዲዮቅልጥያኖስም ቅዱሱን አሰረው። አቡነ ኒቆላዎስ በእስር እያለ፣ ለወዳጆቹ የሚፈርድላቸው እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ትዕግስት ተመልክቶ ዲዮቅልጥያኖስ ተሸኝፎ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በሮም መንበረ መንግሥት ተተካ። ***"ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ.በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና ስሜንም አልካድህምና።››*** *ራዕ ፫፥፰* ተብሎ እንደተጻፈም ቆስጠንጢኖስ ካሰፈታቸው ቅዱሳን አንዱ ይህ ቅዱስ አባት አቡነ ኒቆላዎስ ነበር። ከእስር ወጥቶ ወደ ሌላው የሕይወቱ ምዕራፍ፤ ጌታችን ወደ ከፈተለት የአገልግሎት በር ተሰማራ።

ወደ መንበረ ጵጵስናው ተመልሶም ምዕመናንን እና አምላኩን በብርቱ አገለገለ። አርዮስ ሲነሣም በኒቅያ ጉባዔ ከነበሩት 318ቱ ሊቃውንት አንዱ ይህ ቅዱስ ነው። ከዚያም ያማረ ተጋድሎውን ፈጽሞ በጵጵስናው ብቻ ከ40 ዓመት በላይ አገልግሎ አረፈ።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹***የጻደቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል - ለበረከትም ነው***።›› መዝ. ፻፲፩ (፻፲፪) ፥ ፮፣ ምሳ. ፲ ፥ ፯ እንዳለ። ቅዱስ ኒቆላዎስ - ሊቀጳጳስ በቤተ ክርስቲያናችን በሌሎች ኣኃት አብያተ ክርስቲያናትም በየ ዓመቱ ታኅሣስ 10 ቀን ይታሰባል።

የምዕራባውያኑ ሳንታ ክላውስ ትውፊትም ከዚህ ቅዱስ ታሪክ ይነሳል፤ ነገር ግን ከታሪኩ እንዳየነው ቅዱስ ኒቆላዎስ ድሆችን አጽናኝ ትርፍ ሳይሻም ሰዎችን ያስደሰተ እንጂ በዘመናችን እንደሚታየው ለንግድ እና ሥጋዊ ማታለያ የሠራ አልነበረም።

## ማጠቃለያ፡- ምን ተማርን?

የቅዱስ ኒቆላዎስ ወላጆች እስከ መጨረሻው በመተማመን ኖሩ፤ በእነሱ እውቀት አብቅቶለታል ያሉትን የልባቸውን ፍላጎት የሚፈጸምበት ጊዜ በእግዚኣብሔር የታሰበ ነበር፡፡ በእውነትም እርሱ ስጦታውን የሚሰጥበት ጊዜ አለው ***ለሁሉም ዘመን አለው*** መክ. ፫፥፩ ብሎናልና፡፡ ተስፋ ባለመቁረጥ እንጠብቀው፡፡

ቅዱስ ኒቆላዎስ ፈጣሪዉን ከልጅነቱ ጀምሮ ተከተለው እግዚኣብሔርም በጸጋ ጎበኘው ከፍ ከፍም አደረገው፡፡ ‹‹***የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ደስ አያሰኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ፡፡***›› መክ. ፲፪፥፩ ተብለናልና እኛም እግዚኣብሔርን የምናገለግልበት ዘመን አሁን ነው፡፡

ለሰዎች በተለይም ለተቸገሩ መልካም እናድርግ፥ የልደት መልዕክትም ይሄው ነው፤ ሁሉም የእርሱ የሆነው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት የተወለደው የተቸገረውን የሰው ልጅ ባለጸጋ ለማድረግ ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹***የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ፡፡***›› ዕብ. ፲፫፥፫ ብሎ እንዳስተማረን አቡነ ኒቆላዎስ ከተቸገረው ቤተሰብ እኩል ተጨንቆ የሚችለውን እንዳደረገ እኛም የገና ሥጦታን ከቅዱሱ አባት በተማረነው መሠረት ማበርከት ይኖርብናል፡፡

‹‹***በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው ከተፈተነ በ/ላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና፡፡***›› ያዕ. ፩ ፥ ፲፪ እንዳለ ቅዱስ ኒቆላዎስ መመጽወት በሚችልበትና በሚመሰገንበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በግርፋት እና እስራትም ስለጸና እግዚኣብሔር አከበረው፡፡ እኛም በማንኛውም መከራ እግዚኣብሔር እንደማይተወን አውቀን መጽናትን ከአባታችን እንማራለን፡፡

የቅዱሳንን ታሪክና መልካም ተጋድሎ በተገቢው መንገድ ብናከብረው ከጻድቁ በረከት እናገኝበታለንና የቅዱሳንን በዓላት በመንፈሳዊ መንገድ ማሰብ አለበን፡፡ ምክንያቱም እግዚኣብሔር ቅዱሳንን የሰጠንና ቤተ ክርስቲያንም የዘገበችልንና የምታስባቸው፡፡ ‹‹**እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፤እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን.የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፡፡**›› ዕብ. ፲፪ ፥ ፩ - ፪ ስትለን ነው፡፡ቅዱሳን ክርስቶስን መስለውታልና ፩ኛ.ቆሮ. ፲፩ ፥ ፩ በተግባር ብንከተላቸው ክርስቶስን እናገኘዋለን፡፡

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ኒቆላዎስ (Santa Claus) የእምነት፤ የልግስናና የእውነት ፍሬ፣ ለእግዚአብሔር እና ለቤተሰብ የመታዘዝ ሕይወትን ያሳየ የመንፈሳዊው ተጋድሎም አርኣያችን ነው፡፡

## ተግባር

በገና በዓላችን የቅዱስ ኒቆላዎስን ተግባር በትክክለኛው መንገድ ፈጽሙ፡፡

# እግዚአብሔርን መፍራት

## ዐሥራ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የጥበባት ሁሉ መጀመሪያ ስለሆነው እግዚአብሔርን ስለ መፍራት መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ልብህ በኃጢአተኞች አይቅና ነገር ግን ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር "*** ምሳ. ፳፫ ፥ ፲፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ዕብ. ፲፪፥፳፰-፳፱፣ ምሳ. ፰፥፲፫፣ ምሳ. ፲፮ ፥ ፮፣ ዘዳ. ፲ ፥ ፲፪ - ፲፫፡፡

## መግቢያ

በምድራችን ብዙ ዕውቀት አለ፡፡ ጥበብ እንደሚበዛም አስቀድሞ ተነግሮናል፡፡ ‹‹***እውቀትም ይበዛል፡፡›››*** ዳን. ፲፪፥፬ በተባለበት ዘመን ላይ ስለሆንንም እውቀት በዝቷል፡፡ በተለያየ ሙያና ደረጃ ሰዎች እውቀት ሊኖራቸው፣ በጣም ጠቢብም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጥበባት ምንጭና መሠረት ግን እግዚአብሔርን መፍራት መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት እውቀት ከፍተኛ ጥፋት ያስከትላል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔርን ስለ መፍራት እንማራለን፡፡

***የሚከተሉትን ጥቂዎች ተወያዩባቸው***

እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው?

እንዴት እናዳብረዋለን?

እግዚአብሔርን በመፍራት አለመኖር ምን ያስከትላል?

## የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

አባታችን እግዚአብሔር የሚወደንና የሚንከባከበን አምላክ ነው፡፡ እርሱ ፈጥሮናል፡፡ ሲጠራንም ወደ እርሱ እንሄዳለን፡፡ ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሳ ስንሳሳትና የዘላለምን ሞት ስናመጣም እስከሞት ወዶናል፡፡ የምንወዳቸውን ቤተሰቦች፣ ሕይወታችንንና በጎዎችን ነገሮች ሁሉ የሰጠን እርሱ ነው፡፡ ለወደፊቱም ያሰበልንና ያዘጋጀልን መልካም ነገሮች አሉ፡፡ ይህንን አምላክ ማምለካችን ደስ ያሰኛል፤ እርሱን መውደድ እና ማመንም ታላቅ በረከት ነው፡፡ ታዲያ እርሱን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው?

## እግዚአብሔርን መፍራት ማለት፡-

### እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

እውነተኛ ክርስቲያን ደፋር አይደለም፤ የሚወደውን የሰማዩን አባቱን ያከብራል፡፡ *"ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሐት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ፤ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና፡፡"* ዕብ. ፲፪ ፥ ፳፰ - ፳፱፡፡ አባታችን ዮሴፍ ለቀረበለት የኃጢአት ግብዣ *"በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?"* ዘፍ. ፴፱ ፥ ፱ ያለው ለሚወደው አምላክ ካለው ክብር የተነሣ ነበር፡፡

### ክፋትንና ኃጢአትን እንደሚጠላ ማወቅ ነው።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ቅዱሳን እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ *"ዳሩ ግን። እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ"* ፩ኛ ጴጥ. ፩ ፥ ፲፭ - ፲፮ ኃጢአትና ርኩሰት በእርሱ ዘንድ የተጠላ ነው፡፡ *"እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል ትዕቢትንና እብሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ እጠላለሁ።"* ምሳ. ፰ ፥ ፫

### ለሁሉም እንደ ሥራው ዋጋውን እንደሚሰጠው (እንደሚፈርድ) ማመን ነው።

እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው፡፡ ለሰዎች ክፉና መልካም ሥራ ዋጋ ይሰጣል፡፡ *"እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።"* ራእ. ፳፪ ፥ ፲፪ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ስንፈራ እርሱ እንዳለ፣ እንደሚያየንና እንደሚሰማን፣ ለክፋትና ለበጎነትም ዋጋ እንደሚሰጥ ስለምናምን ነው፡፡ *"በምሕረትና በእውነት ኃጢአት ትሰረያለች፥ እግዚአብሔርንም በመፍራት ሰው ከክፋት ይመለሳል።"* ምሳ. ፲፮ ፥ ፮

እግዚአብሔርን መፍራት ታላቅ ጥበብ ነው፡፡ *"እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ትምህርት ነው ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች።"* ምሳ. ፲፭ ፥ ፴፫ ይህን ጥበብ መያዝ ታላቅ ያደርጋል፡፡ በዘላለም ቤቶች ለመግባትም እርሱን በመፍራት መኖር መልካም ነው፡፡ የሚፈሩት ክብርና ጸጋን ያገኛሉ፡፡

ይህንን ታላቅ ሀብት የሚገኝበትን ጥበብ በውስጣችን ለማዳበር ሁሌም ከቃሉ አንራቅ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለ እግዚአብሔር ይነግረናል፡፡ ከቃሉ አለመራቅ ጥበብንና ማስተዋልን እንድናገኝ አምላካችንንም እንድንወደውና እንድንከተለው ይረዳናል፡፡ *"እስራኤል ሆይ፥ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ፥ በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ፥ አምላክህንም እግዚአብሔርን ትወድድ*

www.zeorthodox.org

*ዘንድ፥ በፍጹምም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ፥ መልካምም እንዲሆንልህ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሥርዓት ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው"* ዘዳ. ፲ ፥ ፲፪ - ፲፫።

ዳዊትም ፡-*"ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል። እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማ ይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።"* መዝ. ፩ ፥ ፪ - ፫ እንዳለ እግዚአብሔር አለማወቅ እና አለመፍራት በምድር እና በሰማይ የምንጎዳበት ስህተት ውስጥ ይከተናልና፤ ልጆች እናንተም እንደ ልበ አምላክ ዳዊት የጥበብ ሁሉ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን መፍራት በውስጣችሁ ይኑር።

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔርን መውደዳችንን በተግባር መገለጥ አለበት። የምንወደው ከሆነም እናከብረዋለን፣ ቃሉን በመፈጸምም ደስ እናሰኘዋለን።

እግዚአብሔርን መፍራታችን የሚታወቀው እርሱን በማክበር፣ የማይወደውን ባለመፈጸምና ፈቃዱን በመፈጸም ነው። ለዚህ የሚረዳንም ቃሉን ማንበብ፣ መማርና መፈጸም መቻል ነው።

## ተግባር

ጥበበኞችና አስተዋዮች እንድትሆኑ እግዚአብሔርን መፍራትን በውስጣችሁ አሳድሩ፣ የነገሮችን ምስጢር የምታውቁበት ጥበብም እንዲሰጣችሁ ዘወትር በጸሎት ጠይቁት።

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ጊዮርጊስ

## ሃያኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ጽናትና እምነትን ከቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪክ ተነስተን መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***‹‹አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱ ትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ፡፡ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፡፡ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ፡፡››*** ራእ. ፮፥፱-፲

**ምንባብ፡-** ገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ዕብ. ፲፩ ፥ ፩ - ፍጻሜም

### መግቢያ

ዛሬ ጊዮርጊስ ስለተባለ ቅዱስ እንማራለን፡፡ ***ቅዱሳን*** ሕይወታቸውን በቅድስና የመሩ፣ ዓላማዊ ምኞትን ክደው (ትተው) ራሳቸውን በጸሎት፣ ሌሎችን በመርዳት እና በሌሎችም መንፈሳዊ ሥራዎች የተሠማሩ ናቸው፡፡

### ሳምንታዊው ትምህርት

ቅዱስ ጊዮርጊስ ልዳ በተባለ ቦታ ተወልደ፡፡ሃያ ዓመት ሲሆነው ቤሩት ወደምትባል ከተማ ሄደ፡፡ በዚያም የቤሩት ሕዝቦች የሚያመልኩት ዘንዶ ነበር፡፡ ወደ ከተማው ከመግባቱ በፊትም በዛፍ ላይ የታሰረች ሴት ልጅ አየ፡፡

ምን እንደሆነች ሲጠይቃትም ለሚያመልኩት ዘንዶ በመሥዋዕትነት መቅረብዋንና እርሱም ፈጥኖ ካልሄደ ዘንዶው ከመጣ እርሱንም እንደሚበላው ነገረችው፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም ይሄን ክፉ ነገር እንደማይፈራ ነገራት፡፡

www.zeorthodox.org

ዘንዶው ቅዱስ ጊዮርጊስን ሲያየው ሊገድለው አንገቱን ቀና አደረገ፡፡ ቅዱሱ ግን ***"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ"*** ብሎ በመስቀል ምልክት አማተበበት፡፡ ዘንዶውም ደካማ ሆኖ መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ከዚያም ቅዱስ ጊዮርጊስ ፈረሱን አምጥቶ፣ የታሰረችውን የገዘውን ልጅ ጫናት፣ ዘንዶውንም በገመድ አሥረው እየጎተቱ ወደ ከተማ አስገቡት፡፡

የቤሩት ሰዎች ይሄንን ሲያዩ፣ ደንግጠው ቅዱስ ጊዮርጊስን ለምን ወደ ከተማው አመጣህብን አሉት፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም ዘንዶው አምላክ እንዳልሆነና ምንም ኃይል እንደሌለው ነገራቸው በክርስቶስ እንዲያምኑም አስተማራቸው፡፡ ሲያመልኩት የኖሩትን ዘንዶም ገደለው፡፡

ስለ ክርስቶስ የሰበከላቸውን ከሰሙ በኋላም÷ክ ርስትናን አምነው ተቀበሉ። የመጀመሪያው ትዕዛዝ እግዚአብሔር በፍጹም ልብ መውደድና ከርሱ ሌላ አለማምለክ ቢሆንም የቤሩት ሰዎች ዘንዶውን ያመልኩ ነበር። ሰማዕቱ ግን ዘንዶውን ገድሎ ክርስቶስን እንዲያመልኩ አደረገ።

ከዚያም ጊዮርጊስ የሀገረ ገዢ ልጅ ነበርና ለሹመት ወደ ንጉሡ ከተማ ሲገባ፤ ሰዎች ሁሉ የጌታችንን የኢየሱስን ክርስቶስን ስም መጥራት ሲፈሩ አየ። እርሱም በታላቅ ድምጽ ስለ ክርስቶስ አስተማረ።

በዚህም ታሰረ፤ ዝም እንዲል ታዘዘ፤ አባበሉትም እርሱ ግን አገልግሎቱን ቀጠለበት። በመጨረሻም ገድለው ሥጋውን በተኑት ነገር ግን ክርስቶስ ላመኑበት ድንቅን ያደርጋልና ቅዱስ ጊዮርጊስን ከሙታን አስነስቶት ሥጋውን የበተኑት ወታደሮች ሳይደርሱ እርሱ ወደ ከተማው ደርሶ ወንጌልን አስተማረ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ የቅዱስ ጊዮርጊስ አጽም ይድራስ ከተባለው ተራራ የሰበሰበበት እና ቅዱሱን ከሞት ያዳነው ቀን ጥር 18 ቀን ነበር።

***የሰማዕቱ ጸሎት ከክፉ ይጠብቀን ይርዳንም አሜን!!***

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ጊዮርጊስ እውነተኛ ሰው በጠፋበት (ባልነበረበት) ዘመን ተነሥቶ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረ ነው። በሕይወቱ ብዙ መከራን ተቀብሎ አልፏል። በመጨረሻ የሕይወትን አክሊል ተቀብሏል።

## ተግባር

እናንተም ስለ ክርስቶስ የተማራችሁት ለሌሎች አስተምሩ።

www.zeorthodox.org

| <u>መዝሙር</u> | <u>ትርጉም</u> |
|---|---|
| አክሊሎሙ አንተ ለሰማዕት | የሰማዕታት አክሊላቸው አንተ ነህ |
| ወአስተርአየ ገሃደ ከመ ሰብእ | እንደ ሰው በግልጥ ታየ |

# ሐዋርያት ተከተሉት

## ሃያ አንደኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ክርስቶስ ኃጥኣንን ለንስሐ ለመጥራት እንደመጣ፣ ስለ ሐዋርያት ጥሪ እና ጌታችንንም ስለ መከተላቸው መገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እነሆ የእግዚኣብሔር በግ አለ፡፡... ደቀመዛሙርቱም ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት"*** ዮሐ ፩ ፥ ፴፮ - ፴፰፡፡

**ምንባባት፡-** ማቴ. ፱ ፥ ፩ - ፲፫፤ ማር.፪ እና ፫፣ ሉቃ.፭ እና ፮፤ ማቴ. ፬፣ ማር. ፩፣ ሉቃ. ፭፣ እና ዮሐ. ፩፡፡

### መግቢያ፡-

በዛሬው ትምህርታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የመጀመሪያ ደቀ መዛሙርት (የአባቶቻችን ሐዋርያትን) አጠራር እናያለን፡፡

### ትምህርቱ

መጥምቁ ዮሐንስ ከእርሱ በኋላ ስለሚመጣውና ከእርሱ ስለሚልቀው ያስተምር ነበር፡፡ ክርስቶስ ወደእርሱ ሲመጣም እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ አስቀድሞ የነገራቸው ስለርሱ እንደነበረም ነገራቸው፡፡

በቀጣዩ ቀንም ጌታችንን አይቶ ‹‹***እነሆ የእግዚያብሐየር በግ***›› አለ፡፡ ከዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሁለቱም ይሄንኑ ምስክርነት ሰምተው ተከተሉት፡፡ ጌታም ሲከተሉት አይቶ ‹‹***ምን ትፈልጋላችሁ***›› ሲላቸው ‹‹***ወዴት ትኖራለህ?***›› አሉት፡፡ ‹‹***ወጥታችሁ እዩ***›› አላቸው ተከተሉት ከርሱም ጋር ዋሉ፤ እነርሱም እንድርያስና ዮሐንስ ነበሩ እንድርያስም መሲሕን አግኝተናል ብሎ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን ጠራው፡፡

www.zeorthodox.org

በሚቀጥለውም ቀን እንድርያስ እና ስምዖን ዓሳ ሲያጠምዱ ዋሉ ግን ምንም አላገኙም፡፡ ጌታችን በታንኳ አስተምሮ ወደ መሐል ገብተው መረባቸውን እንዲጥሉ አዘዘ፡፡ ለረጅም ሰዓታት ሞክረው ባይሳካላቸውም ለጌታ በመታዘዝ መረባቸውን ጣሉ፤ ብዙ ዓሳ ያዙ መረባቸው እስኪቀደድና ያዕቆብና ዮሐንስ እስኪጠሩም በሁለት ታንኳ ሞሉ፡፡ ሉቃ ፭ ፥ ፲፩፡፡

ጌታችንም ሰውን ወደ መንግስት ሰማያት የምታጠምዱ አድርጋችኋለሁ አላቸው፡፡ ተከተ ሉትም ስለዚህ የመጀመሪያዎች ደቀመዛሙርት ወንድማማቾቹ ዓሳ አጥማጆች እንድርያስና ጴጥሮስ እንዲሁም ዮሐንስና ያዕቆብ ሆኑ፡፡

በነጋታውም ጌታ ፊልጶስን «*ተከተለኝ*» አለው ተከተለው ፊልጶስም ናትናኤልን ጠራው እንዲህም አለው «*ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለእርሱ የፃፉለትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል፡፡*» አለው፡፡ ናትናኤልም ከሐዋርያት አንዱ ሆኖ ጌታን ተከተለ፡፡

ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ማቴዎስ ግብር ሰብሳቢ ነበር። ቀራጭ ይባሉም ነበር። ጉቦ የሚቀበሉ ሙሰኞች ስለነበሩ እምነት አጉዳይ ሲባሉ÷ አብዝተው ሕዝቡን ይበዘብዙና ግብር እየጫኑ ለራሳቸው ያተርፉ፣ ከሕዝቡም ጉቦ ይቀበሉ ነበር። ሕዝቡ እንደኃጢአተኛ ያያቸውና ይጠላቸውም ነበር። ማቴዎስም ግብር ሰብሳቢ (ቀራጭ) ነበርና ግብር ለመሰብሰብ በተቀመጠበት ጌታ ሲያልፍ አይቶት። *"ተከተለኝ"* አለው። ማቴዎስም ተነስቶ ተከተለው። በዚያው ቀንም ቀራጭና ኃጢአተኞችን ስብስቦ ጌታችንን በቤቱ እራት ጋበዘው።

አይሁድ ይሄን አይተው ደቀመዛሙርቱን *«መምህራችሁ ለምን ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል?»* አሉት ጌታም *«ሕመምተኞች እንጂ ጤነኞች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ ነገር ግን ሄዳችሁ፦ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ፤ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና አላቸው።»* ማቴዎስም ቀራጭነቱንና ኃጢአቱን ትቶ ተከተለው። የጌታ ደቀመዝሙር (ሐዋርያም) ተባለ።

## ማጠቃለያ

ጌታችን አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ሲመርጥ ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው። እነርሱም ከላይ የተጠቀሱት እና የታዴዎስ ወንድም ያዕቆብ ፣ ታዴዎስ፣ ስምዖን፣ ቶማስና የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው። በኋላም ይሁዳ ጌታን ስለ ካደው በማትያስ ተተክቷል።

## ተግባር

የአሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት ስም በቃላችሁ አጥንታችሁ ያዙ፡፡

አባቶቻችንን ሐዋርያትን በግብር እና በተግባር ለመምሰል እንጣጣር፡፡

www.zeorthodox.org

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዮሐንስ ደቀመዛሙርት የነበሩት ሐዋርያት ማንና ማን ናቸው?
2. በዚህ ትምህርት ጌታችንን የተከተሉት ዓሳ አጥማጆች ስንት ናቸው?
3. ናትናኤልን የጠራው ማነው? ዮሐንስ መጥምቅ ጌታችንን ሲያየው ምን አለ?
4. ማቴዎስ ምን እየሠራ ተጠራ?

# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

## ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክና ክብር መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ትውልድ ሁሉ ብፅእት ይሉኛል፡፡"*** ሉቃ ፩ ፥ ፵፰

**ምንባባት፡-** ሕዝ. ፵፬ እና ሉቃ ፩

## መግቢያ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም፤ ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከችና እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናትነት የመረጣት ናት፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንማራለን፡፡

ስለ እመቤታችን የምታውቁትን አስረዱ… መቼና የት ተወለደች? ወላጆችዋ ማን ይባላሉ? በዚህ ምድር ስንት ዓመት ኖረች? ምን ያህን በዓላቶችዋን ታውቃላችሁ? የምታውቁትን አስረዱ፡፡

## ትምህርቱ

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላጆች ኢያቄም እና ሐና ይባላሉ፡፡ ልጅ በማጣት ለብዙ ዘመን ሲኖሩ ያዝኑ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ልጅ ከሰጣቸው ለቤተ መቅደስ እንደሚሰጡ ስዕለት ተሳሉ፡፡ እግዚአብሔር ልመናቸውን ሰምቶ ጎበኛቸው፡፡ ሐና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ግንቦት 1 ቀን ወለደች፡፡ በተሳሉት መሠረትም በሦስት ዓመትዋ ታኅሣስ 3 ቀን ለቤተ መቅደስ ሰጧት፤ በ15 ዓመትዋ ለዘመድዋ እና ሽማግሌው ዮሴፍ እንዲጠብቃት አደራ ተሰጠው፡፡ በዚያን ወቅት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጌታን እንደምትወልድ አበሰራት፡፡ እርስዋም ***"እንደቃልህ ይሁንልኝ"*** አለችው፡፡

www.zeorthodox.org

ከብሥራቱ በኂላም እመቤታችን ድንግል ማርያም ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ልትጠይቅ ሄደች፡፡ የእመቤታችንን ድምፅ ስትሰማም በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፤ ፅንሱ /ዮሐንስ መጥምቅ/ በእናቱ ማኅፀን ውስጥ በደስታ ዘለለ፡፡ ኤልሳቤጥም እንዲህ አለች ‹‹***ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፣ የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ የጌታዬ እናት ወደእኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል፡፡***›› ሉቃ .፩ ፥ ፵፩ - ፵፪፡፡

ጌታችንን በቤተልሔም በከብቶች በረት ወለደችው፡፡ በሁለተኛው ዓመት ሄሮድስ እንዳይገድለው ልጇን ጌታችን ኢየሱስን ይዛ ወደ ግብፅ ተሰደደች፡፡ በግብፅ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ቆይተው

ናዝሬት ገቡ፡፡ ጌታችንን እያሳደገች በዚያው ኖረች፡፡ ክርስቶስ በ30 ዓመቱ ለማስተማር ሲወጣ የመጀመሪያውን ተአምራት ያዳረገው በእርስዋ ልመና ነበር፡፡ ዮሐ. ፪ ÷ ፩ - ፲፩ ከልመናዋ (ከምልጃዋ) በኋላ ስለ ክርስቶስ ***“የሚላችሁን አድርጉ”*** ብላ መጀመሪያ የመሰከረችው እርስዋ ናት፡፡ በሚያስተ ምርበትም ሁሉ ትገኝ ነበር፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ሲሰቀል፤ ከመስቀሉ ሥር ነበረች፡፡ ***“ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን። እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።”*** ዮሐ. ፲፱ ÷ ፳፯፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በማርቆስ እናት ቤት መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ በዚያ ነበረች፡፡ ከጌታችን ዕርገት በኋላ 15 ዓመታት በጠቅላላው 64 ዓመታት ኖራ ጥር 21 ቀን 50 ዓ.ም ዐረፈች፡፡ ነሐሴ 16 ቀን እንደ ልጅዋ ተነስታ ዐረገች፡፡

ልጆች ለእመቤታችን ምስጋና ይገባታል፡፡ እርስዋም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ***“ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል፡፡”*** ሉቃ.1፡46 እንዳለችን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ‹‹***ጸጋ የተሞላሽ ደስ ይበልሽ፡፡***›› እንዳላት እኛም ብጽዕት፣ ቅድስት፣ ውድስት፣... እያልን እናመሰግናታለን፡፡

ታማልዳለችና በጸሎትዋ ለመጠቀም ወደ እርስዋ እንማለላለን፡፡መዝ. ፹፬(፹፫)÷፲፪፣ ዮሐ. ፪÷፩-፲፩

ወላዲተ አምላክ ናትና ከሌሎች ቅዱሳን በተለየ ክብር እናከብራታለን፡፡ የዓለሙን መድኅን ኢየሱስ ክርስቶስ መውለድ አጋጣሚ አይደለም፡፡ የተለየ ምርጫ ነው፡፡ በእዚህ መጠን የተከበረች ሴትም የለችም፡፡ ይህም ለሌሎች ያልተሰጠ ለእርስዋ ብቻ የተሰጠ ክብር ነው፡፡

## ማጠቃለያ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም 64 ዓመታትን ስትኖር ለራስዋ አልኖረችም፤ የዓለሙን መድኅን ለዓለም ስትገልጥ፣ በእርሱ ምክንያት መሪር ሐዘኖች ሲያጋጥምዋት ኖራለች፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ከዚህ ታሪክዋ እና ሕያው እግዚአብሔር እርስዋን ያከበረበትን ክብር አውቃ ታከብራታለች፡፡ ከእግዚአብሔር በተሰጣት ጸጋ እንዲጠቀሙም ምእመናንን ታስተምራለች፡፡

www.zeorthodox.org

## ተግባር

ልጆች ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት ለቅድስት ድንግል ማርያም ያላችሁን ክብርና ፍቅር አጥብቃችሁ በመያዝ እደጉ፡፡

# ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው

## ሃያ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ጥምቀት ታሪክና ወደ ኢየሩሳሌም ስላደረገው ጉዞ መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣"*** የሐዋ.ሥራ ፰ ፥ ፴፪

**ምንባብ፤-** የሐዋ.ሥራ ፰ ፥ ፳፮ - ፵

## መግቢያ

ከአይሁድ ምድር ቀጥሎ ክርስትናን የተቀበሉ ሕዝቦች የሚኖሩባት ምድር ኢትዮጵያ ናት፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም የንግሥት ሕንደኬ ባለ ሙሉ ሥልጣን የነበረውና የመጀመሪያው ክርስቲያን፤ እንዴት እንዳመነና እንደተጠመቀ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኢትዮጵያውያን ከክርስትና በፊትም አምልኮታቸውን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር፡፡ ክርስቶስ በዐረገ በዓመቱም የንግሥት ህንደኬ (የዚያን ጊዜዋ የኢትዮጵያ ንግሥት) ሹመኛ፤ በሀብትዋ ሁሉ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን የነበረ ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡

ያነብ የነበረው የመጽሐፍ ክፍልም ጌታ ከመሰቀሉ ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በፊት ነቢዩ ስለ ጌታችን የመስቀል መከራ የተናገረውን ትንቢት ነበር፡፡ የጌታም መልአክ ፊልጶስ ጃንደረባው በሚሄድበት መንገድ ሄዶ ወንጌልን እንዲሰብክለት ነገረው፡፡

ፊልጶስ የሚሄድበትን አልመረጠም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ነጥቆ ጃንደረባው ጋር አደረሰው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ መከራ መስቀል ***"እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም፡፡"*** ሲል የተነበየውን ጃንገረባው ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነብ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

ፊልጶስም ቀርቦ ***"የምታነበውን ታስተውለዋለህ"*** አለው፡፡ ጃንደረባውም ***"የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው፡፡"*** ወደ ሰረገላውም ገብቶ እንዲያስተምረውም ጠየቀው፡፡ ፊልጶስም ከነቢዩ የትንቢት ቃል ጀምሮ ስለ ክርስቶስ ከእመቤታችን መወለድ፣ ማስተማር፣ መሰቀል፣ ትንሳኤና ዕርገቱንም አስተማረው፡፡

በመንገድ ሲሄዱም ውሃ ካለበት ቦታ ደረሱ በዚህ ግዜ ጃንደረባው ***"እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድርነው?*** አለው፡፡ ፊልጶስም መልሶ ***"በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል"*** አለው፡፡ ጃንደረባውም ***"ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ"*** አለ፡፡

ሁለቱም ከሰረገላው ወረዱ፣ ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው፣ የመጀመሪያው እስራኤላዊ ያልሆነ ተጠማቂም ሆነ፡፡ ከውኃው ሲወጡም ፊልጶስ ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ ተወሰደ፤ ኢትዮጵያዊውም ደስ እያለው ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

## ማጠቃለያ

- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የኢትዮጵያ ሰው ነው፡፡ በሕንደኬ ዘመን ባለሙሉ ሥልጣን ነበር፡፡ ሆኖም እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን በኦሪት ሕግ እግዚአብሔርን የሚያምን ነበር፡፡ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሄደውም ለዚህ ነበር፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ በምሥጢር የተሞላ ነው፡፡ ያልገባንን መጠየቅ አለብን፡፡ ኢትዮጵያዊው ***"የሚረዳኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል"*** በማለቱ፡፡ ፊልጶስ መጽሐፉን ተርጉሞለት አመነ፡፡
- ነቢዩ ኢሳይያስ የተነበየውና ኢትዮጵያዊው ያነበው የነበረው የመጽሐፍ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በትኅትና ባዶ አድርጎ በሚሰድቡት እንዳልዛተ ይነግረናል፡፡ እኛም ለሌሎቹ እንዲህ ማድረግ አለብን ልንጸልይላቸው  የሚገባን መልካም ለሚያደርጉልን ብቻ ሳይሆን ክፉ ለሚያደርጉብንም ነው፡፡
- ጸሎታችን መልካም እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፤ ባይመለሱም እግዚአብሔር ለፍቅራችን እና ለመልካምነታችን ይከፍለናል፡፡

## ተግባር

- ቅዱሳት መጻሕፍትን ስታነቡ ያልተረዳችሁን መጠየቅ አትርሱ፡፡
- መምህር የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለተማሪዎች በመስጠት እንዲያነቡና ትርጉሙን ከመምህራኑ ቤተ ክርስቲያን ጠይቀው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡

www.zoorthodox.org

# የሳውል መመለስ

## ሃያ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ሳውል ወደ ክርስትና መመለስ መገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው..."*** የሐዋ.ሥ ፱ ፥ ፲፭

**ምንባብ፡-** የሐዋ. ሥራ. ፱ ፥ ፩ - ፴፩

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ያጠመቀው ማነው?
2. እንዲያጠምቀው የላከውስ ማነው?
3. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምን ይሰራ ነበር? ምን ተማረ ለመምህር አስረዱ፡፡

### መግቢያ

ዛሬ ጌታን በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ከተከተሉትና ቤተክርስቲያንን ካገለገሉት አንዱ ስለሆነው ቅዱስ ጳውሎስ እንማራለን፡፡ ይህ ሐዋርያ ቁጥሩ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ባይሆንም ሐዋርያ ተብሎአል፤ አሥራ አራት መጻሕፍትንም ጽፏል፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

የክርስቶስን ደቀመዛሙርት የሚያሳድድ ሳውል የተባለ ቀናኢ አይሁድ ነበር፡፡ ክርስቶስ የእግዚ አብሔር ልጅ መሆኑንም አያምንምና አንድ ቀንም ክርስቲያኖችን አስሮ ለማምጣት የሚያስችለው ማዘዣ ከአይሁድ የካህናት አለቆች ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ተጓዘ፡፡

www.zeorthodox.org

ወደ ደማስቆ ሲቃረብም ኃይለኛ ብርሃን በዙሪያው ሆነ፤ እጅግ ደንግጦም መሬት ላይ ወደቀ፡፡ ‹‹***ሳውል ሳውል ስለምን ታሣድደኛለህ?"***›› የሚል ድምፅም ሰማ፡፡ ሳውል ***"አንተ ማነህ?"*** አለ፡፡ ጌታም ***"እኔ የምታሣድደኝ ኢየሱስ ነኝ"*** አለው፡፡ ሳውልም ደንግጦ ***"ጌታ ሆይ ምን ላደርግ ትፈልጋለህ?"*** አለው፡፡ ወደ ከተማ እንዲገባና ማድረግ የሚገባውንም እንደሚነግሩት ገለጠለት፡፡

ከተቀመጠበት ተነሣ ማየት ግን አልቻለም፡፡ አብረውት የነበሩትም ሰዎች እየመሩ ከተማ አደረሱት፡፡ ሳውልም ሳይበላና ሳይጠጣ ሦስት ቀን በጸሎት ኖረ፡፡ ሐናንያ የሚሉት ሰው መጥቶ እንዲያይ እንደሚያስችለውም በራዕይ አወቀ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐናንያ ለተባለ ደቀመዝሙር ተገልጦ ወደ አይሁድ ቤት ሄዶ ሳውል የሚሉት የጠርሴስ ሰው ፈልጎ እጁን ጭኖ እንዲጸልይለት ነገረው፡፡ ሐናንያ ሳውል ብዙ ክፉት እንዳደረገና ከካህናት አለቆች ክርስቲያኖችን የማሠር ሥልጣን እንደተሠጠውም ገለጠ፡፡ ጌታችንም ***"ስሜን የሚሸከም ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ"*** አለው፡፡

ሐናንያም ሳውል ወዳለበት ቤት ሄዶ ሳውልን ተገናኘው እጁን ጭኖበት ከጸለየ በኃላ እንዲህ አለው ***"ወንድሜ ሳውል ሆይ፡-ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፣ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ "*** አለ፡፡

ወዲያውም ቅርፊት ከዓይኑ ወደቀ፣ አየም ተጠመቀም በልትቶም በረታ፡፡ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቆጥሮም ስለ ክርስቶስ ማስተማር ጀመረ፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝን አላወቀም፡፡ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነቱን እንዲያይ ዓይኖቹን ከከፈተለት በኂላ አመነና እንደሌሎቹ ደቀማዛሙርት የጌታ ምስክር ለመሆን በቃ፡፡ ብዙ መልእክቶችንም ጽፎአል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖርንም ለብዙ ሰዎች አስተምሮአል፡፡ ከመልእክቱም እግዚአብሔርን እንዴት እንደምንከተለው እንማራለን፡፡

ሳውል ማየት ሲያቅተው ሦስት ቀንና ሌሊት እየጾመ ጸልዮአል፡፡ ጌታም ተገልጦና ሐናንያን ልኮ ዓይኑን አብርቶለታል፡፡ ከዚህ እኛም በመከራ ጊዜ ልንጾምና ልንጸልይ እንደሚገባንና እግዚአብሔር መፍትሔ እንደሚሰጠን እንማራለን፡፡

## ተግባር

በጸብና በኃይል ከመፈጸም ይልቅ በትሕትና ነገሮችን ለመረዳት ለማስረዳት ሞክሩ፡፡

www.zeorthodox.org

# ፍቅር - የሕግ ፍጻሜ

## ሃያ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፦** ስለ ፍቅር መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፦***"ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።"* ሮሜ ፲፫፥፲፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፦** ሕግጋተ እግዚአብሔር መጽሐፍ በአባ ኃብተ ማርያም፣ በቀሲስ እሸቱ ታደሰ፡፡

### *መግቢያ*

እግዚአብሔር ክብሩን ሊያወርሰን ስለወደደ ፈጥሮናል፡፡ በነጻ ፈቃድ እንድናመልከውም ፈቀደ፡፡ በነጻ ፈቃዳችን እንዳንሞትም ሞት የምታመጣዋን ፍሬ አትብሉ ሲል ሕግ ሠራልን፡፡ ይህችም ሕግ የመጀመሪያዋ ሕግ ናት፡፡ ሌሎቹን ሕግጋትም በኋላ ሠጠን፡፡ እነርሱም አሠርቱ ትእዛዛት እና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው፡፡ ቀጥሎ ባሉት ሳጥኖች ውስጥ አሠርቱን ሕግጋትና ስድስቱን ቃላት ሙሉ፡፡

| | |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |

www.zeorthodox.org

የወንጌል ሕግጋት..........

| | |
|---|---|
| | |
| | |

በዛሬው ትምህርታችንም የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ስለሆነው ስለ ፍቅር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው ማለት፡-

### የሁሉም ሕጎች መድረሻ ፍቅር ነው፡፡

በሕጎች ውስጥ የምናገኘው ዋና ሃሳብ እግዚአብሔርንና ሰውን በመውደድ እንድንኖር ነው፡፡ የምንወደውን ሰው አንዋሽውም፣ አንሰርቀውም፡፡ ***"ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።"*** ሮሜ ፲፫ ፥ ፲

እግዚአብሔርን ከወደድነውም ሌላ አምላክ አናመልክም፣ ስሙንም በከንቱና በሐሰት አንጠራም፣ ራሳችንን ለእርሱ እንቀድሳለን፡፡ ፈቃዱንም እንፈጽማለን፡፡ ***"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።"*** ዮሐ. ፲፬ ፥ ፲፭

### የመጨረሻዎቹ ሕግጋት የፍቅር ሕጎች ናቸው

አዳምን አትብላ ሲለው ምክንያት የጠቀሰው እንዳትሞት ብሎ ነው፡፡ ይህም ጥልቅ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ የ፲ቱ ትእዛዛት መጨረሻ ባልጀራህን ውደድ የሚል የፍቅር ሕግ ነው፡፡ ***"አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል፡፡"*** ሮሜ. ፲፫ ፥ ፺

### የሕግ ፍጻሜ ክርስቶስ ነው፡፡

ነቢያት የተናገሩት ትንቢት እና ምሳሌ ፍጻሜውን ያገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በክርስቶስ ማመን በፍቅር መኖር ነው፡፡ በክርስቶስ ማመን የሕግን ሁሉ ፍጻሜ ማግኘት ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ ፍቅርን በተግባር እስከሞትም ድረስ አሳይቶናልና፡፡ ለዚህ ፍቅር የሚኖረን መልስ በእርሱ በማመን መኖር ነው፡፡ ***"የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።"*** ሮሜ. ፲ ፥ ፬፡

www.zeorthodox.org

### ፍቅር ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ሕግ ነው።

ሁሉም ሕግጋት መድረሻ አላቸው። የሚጠበቁትና የሚያዙትም በዚህ ምድር ነው። ምክንያቱም በሰማይ ሀገር ኃጢአትን መፈጸም አይቻልምና መስረቅ ወይም ማመንዘር… አይቻልም።

እምነት የእግዚአብሔር መኖርና መገለጥ ማመን ነው። ሰማያዊ ዋጋ እንዳለ መቀበል ማመን ነው። እምነት በልብ የሚያዝ ነው። በቃል በመመስከር በተግባር ይገለጣል። እነኚህን እያደረግ ኖረን ክርስቶስ ሲመጣ ለማመናችን ዋጋ ይሰጣል።

ተስፋ የምናደርገው ነገር ተስፋውን ስናገኝ ተስፋነቱ ያበቃል። ሰማያዊትዋን ሀገርና ክርስቶስን ፊት ለፊት ሲመጣ እናገኘዋለን። በመሆኑም ሁሉም ፍጻሜ አላቸው። ፍጻሜያቸውም ፍቅር ነው።***"ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል።።"*** ፩ኛ ቆሮ. ፲፫ ፥ ፰።

ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖርበት ሕግም ፍቅር ነው። ***"እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።"*** 1ኛ ቆሮን.13፥13

## ማጠቃለያ

ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ እርሱንና ፍጥረታቱን መውደድ ነው።

## ተግባር

ከወንድምና እህት እንዲሁም ከማንኛውም ሰው ጋር በፍቅር ተመላለሱ።

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ፓሊካርፐስ

## ሃያ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ** ፦ ከፖሊካርፐስ ሕይወት በእድሜና በአገልግሎት ማደግን ማስገንዘብ።

**የሚጠና ጥቅስ፦** *"እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።"* ፩ኛ ዮሐ. ፩ ፥ ፫

**ተጨማሪ ምንባብ፦** ቅዱስ ፖሊካርፐስ ሐዋርያዊ ጳጳስ ወሰማዕት ገጽ. 26 - 33 በዘውዴ ገብረ እግዚአብሔር

### መግቢያ

ልጆች ከጌታችን የተማሩትን ሐዋርያትን የተከተሉዋቸው ሐዋርያውያን አበው ይባላሉ። ቤተ ክርስቲያንን በብዙ መከራ ውስጥ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፤ ከጌታችን ለሐዋርያት የተላለፈውንና ሐዋርያት የጻፉትን መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ የጠበቁና ያስተላለፉ ናቸው። ከእነዚህ አባቶች አንዱ ከ፸ - ፻፶፮ ዓ.ም የኖረው ቅዱስ ፖሊካርፐስ ነው። ከሕፃንነቱ እስከ እውቀት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገለና ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ የኖረውን አባት ታሪክ በአጭሩ በዛሬው ትምህርታችን እናየለን።

### የሳምንቱ ትምህርት

ሰርምኔስ በዛሬዋ ቱርክ በጥንትዋ ታናሽ እስያ ከነበሩት ሰባት ጥንታዊ ከተሞች አንድዋ ናት። በዚህች ከተማ ከኢየሩሳሌም የተሰደዱ አይሁድ በብዛት ነበሩባት። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊውም አስተምሮ ፣ አሳምኖና አጥምቆ ክስቲያኖችን በማሰባሰብ ቤተ ክርስቲያንን መሥርቷል።

www.zeorthodox.org

በዚህች ከተማ ከነበሩት ክርስቲያኖች ሁለት ጠንካራ ባልና ሚስት ነበሩ። እነዚህ ባለትዳሮች ከሐዋርያት በእውነት የተማሩና በቅድስና የሚኖሩ ነበሩ። ፖሊካርፐስ ከእነኚህ መልካም ቤተ ሰቦች ተወለደ። ሆኖም በልጅነቱ ሁለቱም ሞቱበት።

በከተማው ካሊቶስ የተባለች ደግና ባለጸጋ ሴት ነበረች። ይህች ሴት በሕልምዋ ፖሊካርፐስን እንድታሳድገው ተነገራት። እርስዋም የታዘዘችውን ፈጸመች። ቤተሰቡን አጥቶ በብቸኝነት የነበረው ፖሊካርፐስ በባጸጋዋ ካሊቶስ ቤት ማደግ ጀመረ።

እንደ ቤተሰቡ ይህችም ሴት ፖሊካርፐስን ሃይማኖት ማስተማርዋን ቀጠለች፡፡ ልጁ ከፍ ሲልም የቤትዋን ሓላፊነት ሰጠችው፡፡ ታማኙ ፖሊካርፐስ እንደእርስዋ ሆኖ ቤትዋን በመጠበቅና በመላላክ አገለገላት፡፡

አንድ ቀን ካሊቶስ ቤት ባልነበረችበት ወቅት በቤት ያለውን ለነዳያንና ሰጠ፡፡ ካሊቶስ ስትመለስ፤ ቤት ሳትደርስም አንድ ልጅ ሮጦ የሆነውን ነገራት፡፡ በጣም የተበሳጨችው እናት ፖሊካርፐስን ልትቆጣ ወደ ውስጥ ስትገባ የተባለው እቃ በሙሉ በቦታው ተገኘ፤ ያውም የጎደለው ሁሉ ሞልቶ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ የነገራት ልጅ የዋሸ መስሏት ልትመክረውና ልትገስጸው ስትመለስ፡፡ ፖሊካርፐስ ***ተይው አልዋሸም*** አላት፡፡ እርስዋም በጌታችን ተአምራት ሁሉ መሞላቱን አስተዋለች፡፡

ካሊቶስ ንብረትዋን  በሙሉ ለፖሊካርፐስ አወረሰችው፡፡ ብዙም ሳትቀይ ሞተች፡፡ እርሱ ግን በቅድስናና በመንፈሳዊ ሥራዎች ጠንክሮ መመራት ቀጠለ፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙርና የሰርምኔስ ጳጳስ ቡኩሎስ ሃይማትናት በሚገባ አስተማረው፡፡ ከሐዋርያት በተለይም ከቅዱስ ዮሐንስም በሚገባ ተማረ፡፡

ትጋቱንና ታማኝነቱን ያየው ሊቀ ጳጳስ ቡኩሎስ ፖሊካርፐስን ዲቁና ሾመው፡፡ ቀጥሎም ትጋቱን ዐይቶ ቅስና ሾሞ ተክቶት እንዲያስተምር አደረገ፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ የቅርብ ወዳጅና ደቀ መዝሙር በመሆንም በሐዋርያዊ ጉዞዎች ይራዳው ነበር፡፡

ቅዱስ ዮሐንስንና ሌሎችን ሐዋርያት በማየት ያገኘውን ልምድ በሚገባ ተጠቅሞ በሕይወቱ መተግበር በመቻሉ ለብዙዎች አርዓያ ለመሆን በቃ፡፡ በሐዋርያዊ ተልእኮው በመበርታትም በአይሁድ በመናፍቃንና በአሕዛብ መካከል ይሰብክ ነበር፡፡

ፖሊካርፐስ አሁን ፴ ዓመት እየሆነው ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ የሚመሰክሩለት ክርስቲያናዊ ኑሮም አለው፡፡  በእድሜና በጤና እየደከመ የመጣው ሊቀ ጳጳስ ቡሉኮስም እንዲተካው የሚመኘው ፖሊካርፐስ መሆኑን በተደጋጋሚ እየተናገረ ነው፡፡

ቅዱስ ዮሐንስም ፖሊካርፐስን የሰርምኔስ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾመው፣ በዚህ ወቅት ሊቀ ጳጳስ ቡሉኮስ ዐረፈ፡፡ እርሱም በትጋት በጎቹን መምራትና መጠበቅ ቀጠለ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተገለጠለት፡፡ ታላላቅ አባቶች ለመሆን የበቁ ደቀ መዛሙርትም አፈራ፡፡

ሁሉም አባቶችም ይመሰክሩለት ነበር፡፡ በተለይም ቅዱስ አግናጥዮስ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ***"ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ይህ የአሁኑ ወቅት አንተን በእጅጉ ይፈልግሃል፡፡ በአንተ እርዳታ ወደ እግዚአብሔር እንደርሳለን"***

በዚህ ሁኔታ ያገለገለው ቅዱስ ፖሊካርፐስ የካቲት ፳፫ ቀን በ፻፶፮ ዓ.ም በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- ቅዱስ ፖሊካርፐስ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደና በአባቶቹ እየተማረ ያደገ ክርስቲያን ነው፡፡
- በክህነት አገልግሎቱ እስከ ጵጵስና ደርሶ የተሾመበትን በአግባቡ የፈጸመ ታላቅ አባት ነው፡፡
- በሐዋርያትና በተከታዮቻቸው ዘመን መሐል እንደመኖሩ በክርስትና ጠብቆ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

## ተግባር

- የተማራችሁትን የምትተገብሩ ሁኑ፡፡ ይህን ብታደርጉ እግዚአብሔር ያሳድጋችኋል፡፡
- ከአባቶች ትምህርትና ልምድ መውሰድ ለወደፊት ሕይወታችሁ የማይጠፋ ስንቅ ማግኘት መሆኑን እወቁ፡፡
- ታማኝነታችሁ ዘወትር ዘበሰው እና በእግዚአብሔር ፊት ይሁን፡፡
- የቅዱስ ፖሊካርፐስን ሥራዎች ጠይቃችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1 ሰርምኔስ የት ትገኛለች? በሰርምኔስ መጀመሪያ ያስተማረውስ ማነው?

2. ቅዱስ ፖሊካርፐስን ያሳደገችው ሴት ማን ትባላለች? ለምን ከእርስዋ ዘንድ አደገ?

3. ፖሊካርፐስን ክህነትና ዲቁና የሰጠው ማነው? ጵጵስናውንስ ከማን ተቀበለ?

4. ቅዱስ ፖሊካርፐስ ምን ያህል ዘመን ኖረ?

www.zeorthodox.org

# ታማኝ አገልጋይ

## ሃያ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ተሰጥዎቻችንን ስለመጠቀም ማስታወስ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** "ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ።" 2ኛ ጢሞ 2÷1

**ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፭ ፥ ፲፬ - ፴

### መግቢያ፡-

ጌታችን ስለ ዳግም ምጽአቱ በተለያዩ ምሳሌዎች አስተምሯል። ከነዚህ ምሳሌዎች ስለታማኞች እና ሰነፍ ባሪያዎች መስሎ ያስተማረው ይገኝበታል። ማቴ. ማቴ. ፳፭ ፥ ፲፬ - ፴። ይህ አንቀጽ በቤተክርስቲያን ***"ገብርኄር"*** ተብሎ ሲታወቅ የዐቢይ ጾም ፯ኛ ሳምንት በዚህ የጌታችን ትምህርት ተሰይሞአል። ገብርኄር - ታማኝ አገልጋይ ማለት ሲሆን፤ እግዚአብሔርን በመታመን ስለማገልገል በተሠጠን ተሰጥኦ ተጠቅመን ውጤታማ መሆንና ዋጋውንም እንማርበታለን።

### የትምህርቱ መገለጫ፡-

ጌታችን ስለ አንድ ባለጠጋና ባሮቹ ምሳሌ አስተማረ። ወደ ሌላ አገር የሚሄድ አንድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዱ እንደየአቅሙ ለአንዱ አምስት ለአንዱም ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ሄደ። ባለ አምስቱ  ሄዶ ነገደና አምስት፣ ባለ ሁሉቱም ሁለት አተረፈ። ባለአንዱ ግን ቆፍሮ ቀበረው። ከብዙ ዘመንም በኂላ የእነዚያ ባሮች ጌታ የሠጣቸውን ሊቆጣጠር መጣ። ባለአምስቱና ባለ ሁለቱ ያተረፉትን ይዘው ሲቀርቡ ባለ አንዱ ግን ጌታዬ ጨካኝ ብሎ እንደፈራና እንደቀበረውም ነገረው።

ጌታቸውም ያተረፉትን እያንዳንዳቸውን ***"መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** አላቸው። የቀበረውንም ***"አንተ ክፉና ሃኬተኛ እኔ ካልዘራሁበት እንደማጭድ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሠጠው በተገባህ ነበር፣ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት"*** አለ። ወደ ውጪ አውጥተው እንዲጥሉትም አዘዘ። ‹‹***በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል***።››

www.zeorthodox.org

ይህ ምሳሌ ጌታችን ስለዳግም ምጽአቱ ሲያስተምር የተናገረው ነው። ምሳሌነቱም ባለጠጋው የክርስቶስ፤ ባሮችም ጌታችን በሠጣቸው ጸጋ፣ ዕውቀት፣ ሀብት፣ መንፈሳዊ በረከቶች የተጠቀሙና

ያልተጠቀሙ ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡ ጌታችን ሲመጣ እያንዳንዳችን የሰጠንን እንደሚቀበለንና እንዲሚጠይቀን መዘጋጀት እንደሚገባን እንማራለን፡፡

## ማጠቃለያ

ማድረግ የሚገባንን በጠቅላላው እንዲህ ከተገነዘብን የምንፈጽምባቸውን መንገዶች እንይ ፡-

**እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ሰጥቶናል፡፡** በተፈጥሮ የተሰጠን ዕውቀት፣ በጥምቀትና ሜሮን የተቀበልነው ጸጋ፣ የምንቆርብባትና የምንማርባት ቤተክርስቲያን፣ካህናትና መምህራን፣ የሚወዱንና የሚንከባከቡን ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችንን በአግባቡ ከተጠቀምንባቸውና ከሰማናቸው ከእግዚአብሔር የተሠጡን ስጦታዎች (መክሊቶችም) ናቸው፡፡በመጽሐፍ ***"ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፡፡" ፪ኛ*** ጢሞ ፪ ፥ ፩ እንዳለ፡፡

**ተስጥዎቻችንን እንጠቀምበት፡፡** ከላይ በጠቀስናቸውና እውቀታችንን፣ ተስጥዖአችንንና፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወታችን በቀና መንገድ ብንመራና ብናሳድግ እግዚአብሔር ***"አንተ ታማኝ በሰላም ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** ይለናል፡፡ በበለጠውም ይሾመናል፥ያከብረናልም፡፡

**ጌታችን ሥራችንን ሊመዝን የሚመጣበት ጊዜ አለ፡፡** ***"ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው፡፡"*** ማቴ. ፳፭፥፲፱ ተብሎ እንደተመሰለ ሁሉንም ስለሥራው ዋጋ ሊሠጥ ጌታችን ይመጣል ***"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡"*** ራዕ. ፳፪፥፲፰ እንዲል፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የሚታይ፣ የሚመሠገንም ሥራ ልንሠራና ዋጋችንን ጌታችን እንደሚከፍለን አምነን ልንሠማራ ይገባል፡፡

በዕድሜአችንም በአግባቡ ከተማርን ፣ ቤተሰብ ከታዘዝና ከተመረቅን በእግዚአብሔር ፊትም በእውነትና በትጋት ካገለገልን በነገው ሕይወታችን ***"በጥቂት ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ፡፡"*** ማቴ. ፳፭ ፥ ፳፩ እና ፳፫ እንደሚለን ታላቅ ሰው እንደሚያደርገንም እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

***ታዛዥነት*** ሌላው ከዚህ ምሳሌ የምንማረው መታዘዝን ነው፡፡ሁለቱ ሰዎች በተሠጣቸው ታዘው ሲያተርፉ ሦስተኛው ግን ቀብሮ ከመቆየቱም በላይ ለስንፍናው ጌታውን የወቀሰ ነው፡፡ ይሄም የማይታዘዙ እንቢተኛ ልጆችን ይመስላል፡፡ ካለመታዘዝ በትሕትና የተባልነውንና የተማርነውን ወደ መፈጸም እንድንመለስ ያስተምረናል፡፡

## ተግባር

1. የሰንፍና ምክንያቶችን ከእናንተ ቁርጣችሁ አስወግዱ።
2. ታዛዦች ሁኑ።
3. የተሠጣችሁና ያላችሁን በረከት እወቁ! እግዚአብሔርን አመስግኑበት! አድንቁ! ተጠቀሙበትም።

<u>*መዝሙር*</u>

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል
በዕረፍት ውሃ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል።

***ጥያቄዎች፡-***

1. ሰባተኛው ሳምንት በቤተ ክርስቲያን ምን ተብሎ ይጠራል? ለምን?
2. ገብርኄር ማለት ምን ማለት ነው?
3. ባለጠጋው ለባሮቹ ምን ሠጣቸው?
4. እነርሱስ በተሰጣቸው ምን ሠሩ?
5. ጌታቸው የሠጣቸውን ሲቆጠራቸው ምን አሉት?

www.zeorthodox.org

# ኒቆዲሞስ

## ሃያ ስምንተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ኒቆዲሞስ እና ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፡፡"*** ዮሐ. ፫ ፥ ፭

**ምንባብ፡-** ዮሐ. ፫ ፥ ፩ - ፲፭

## መግቢያ

በዛሬው ትምህርታችን፤ በዐቢይ ጾም ሰባተኛ ሳምንት የሚታሰበውን መነሻ በማድረግ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ለመማር በሌሊት የሚመጣ ኒቆዲሞስ የተባለ ምሁር ነበር፡፡ የታወቀ ምሁር ሆኖ ሳለ ስለ ጌታችን ለማወቅና ከእርሱም ለመማር አይሁድን ተሸሽጎና ፈርቶ በሌሊትም ይመጣ ነበር፡፡ አንድ ምሽትም ጌታችን ስለ ጥምቀት አስተማራቸው፡፡ ታዲያ ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ ***"መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳመጣህ እናውቃለን፡፡"*** አለው፡፡

ጌታችንም ***"እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይም"*** አለው፡፡ ኒቆዲሞስም ተደንቆ ***"ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?"*** አለ፡፡

ጌታችንም ***"ዳግመኛ መወለድ"*** ምን ማለት እንደሆነ አብራራለት፡፡ ***"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፡፡ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፡፡"*** አለው፡፡ በዚህ ትምህርት መሠረትም ቤተክርስቲያን ልጆችንና አዲስ አማንያንን ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ ታጠምቃለች፡፡

www.zeorthodox.org

እናት ልጇን ታቅፋ ስትቀመጥ፤ ካህናትና ዲያቆኑ ቆመው በማጥመቂያ ዙሪያ ይጸልያሉ፡፡ የክርስትና አባትና እናትም ጸሎተ ሃይማኖት ደግመው ስለ እግዚአብሔር ሊያስተምሩ ቃል ይገባሉ፡፡ ካህኑም የክርስትና ስም ይሠጣሉ፡፡ ***የክርስትና ስም ምንድነው?*** ተወያዩበት፡፡

ከጥምቀት በኋላ ሜሮን ይቀባሉ፤ መንፈስ ቅዱስም ያድርባቸዋል፤ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ ማለትም ይህ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ እንዳስተማረውም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡

አዲስ ምስጢር እንደ ኒቆዲሞስ እንዲገልጥልንም፤ ከእግዚአብሔር ለመማር ያለን ፍላጎት ሁሌም በጉጉት መሆን አለበት። ኒቆዲሞስ ምሁር እንኳን ሆኖ ሳይኮራና ይበቃኛል ሳይል ይማር ነበር። በዚህም ስለ ሰማያዊ ምሥጢር ተማረ።

## ማጠቃለያ

- ኒቆዲሞስ ሊቅም ሆኖ ለመማርና ለመጠየቅ የሚጥር ነበር። ይህ ትጋቱም ከራሱ አልፎ ለዓለም የሚጠቅም ትምህርት እንዲያገኝ አስችሎታል።
- ጥምቀት የመዳን መግቢያ በር ነው። የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኘት የምንችለው በጥምቀት ነው። ይህን ያልፈጸመ ወይም ተሰብኮለት ያልሰማና ያላመነ አይድንም።

## ተግባር

- ለመጠየቅ እና ለመማር ምክንያት አትስጡ።
- እንደ ኒቆዲሞስ የመማር ፍላጎት አላችሁ? ካልሆነ ለምን? ከመምህር እና ከቤተሰብ ጋር ተወያዩ። ምክርም ተቀበሉ።
- ሕፃናት ሲጠመቁ በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ ተመልከቱ።

### ጥያቄዎች

1. ኒቆዲሞስ ወደ ጌታችን ይሄድ የነበረው ለምንድነው?
2. መድኃኒታችንስ ስለ ምን አስተማረው?
3. ጥምቀት ምንድነው?
4. የተጠመቁ ሰዎች የሚወጣላቸው ስም ምን ይባላል?

www.zeorthodox.org

# ሆሣዕና

# ሣያ ዘጠነኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን አዘጋጀሁ›* ማቴ ፳፩ ፥ ፲፮

**ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፩ ፥ ፩ - ፲፮

## መግቢያ

ሆሣዕና መድኃኒት ማለት ሲሆን የዛሬው ትምህርታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱና ትንሣኤው በፊት ባለው እሁድ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ማየት እንመለከታለን፤ በክብር መግባት ስንልም ሞትን በሞቱ እና ትንሣኤው አጥፍቶ፣ ለሕያዋንና ለሙታን ድኅነትን ያውጅ ዘንድ ስለገባ ነው፡፡ሕዝቡ የያዘው የዘንባባ ዝንጠፊም የክብሩ መገለጫ እና ምሳሌ ነበር፡፡

በዘሌዋ. ፳፫ ፥ ፵ እንደተገለጠውም ዘንባባ የክብርና ምሥጋና ምሳሌ ነበር፡፡ ሕጻናትና አዋቂዎች ዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ደስታቸውንና ክብራቸውን ለክርስቶስ የገለጡት ከዚህ ተነስተው ነው፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ በዓለ ፋሲካ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፤ በኢየሩሳሌም በዓል ለማክበር የተሰበሰበው ሕዝብ አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱን ስለሰሙ ብዙ ሕዝብ ሊቀበለው ወጣ፡፡

ወደ ኢየሩሳሌም ከመውጣቱ በፊትም ሁለት ደቀመዛሙርቱን *«በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ፡፡ ማንም እንዳች ቢላችሁ፡- ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል፡፡››* ማቴ. ፳፩ ፥ ፪ - ፫

www.zeorthodox.org

ደቀመዛሙርቱ እንደታዘዙት ሄደው አገኙ፡፡ ፈትተው ሲመጡም የአህዮቹ ጌታ ጠየቃቸው ጌታ መፈለጉን ሲነግሩትም ሰደዳቸው፡፡

ጌታችን በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሕዝቡ ልብሳቸውን የዘንባባ ዝንጣፊና የሌሎች ዛፎች ጫፍ እየቆረጡ መንገድ ላይ በማንጠፍ ተቀበሉት፡፡

ብዙ ሕጻናትም *‹‹ሆሣዕና በአርያም በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፡፡›* እያሉ ዘመሩ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው በመጀመሪያ የሆነውን አላስተዋሉም ነበር፡፡ በኂላ ግን ነቢያት ቀድመው ተንብየው እንደነበርና ያም መፈጸሙን አስተዋሉ፡፡

ነቢይና መዝሙረኛው ዳዊት «*ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጅህ*» መዝ. ፰ ፥ ፪ ሲል ቀድሞ ተንብዮ ነበር፡፡ በነቢዩ ዘካርያስም «***ለጽዮን ልጅ፦እነሆ÷ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉኣት***» ዘካ. ፱ ፥ ፱ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፡፡

ነገር ግን የአይሁድና የካህናት አለቆች ቀንተው ‹‹***እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን?***›› በማለት ዝም ለማሰኘት ሞከሩ፡፡ ጌታችንም‹‹***እሰማለሁ***›› ብሎ በነቢያት የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን አስታወሳቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ የገባበት ሰንበት ከመስቀሉ በፊት ያለችው ሰንበት ናት፡፡ የአይሁድ ካህናትና አለቆች ክርስቶስን ብዙ ሕዝብ ሲከተለው ስላዩ ቀኑ፡፡ ይኸ ቅናትም ሊያድናቸው የመጣውን ለመስቀል አሳልፎ ለመስጠት አበቃቸው፡፡ የካህናት አለቆችና ፈረሳውንያን ምንም እንኳ መጻሕፍት አዋቂዎች ቢሆኑና ስለክርስቶስ የተባለውን ቢውቁም ለክብራቸው ሲሉና ቅንዓት ዓይናቸውን አሳውሮት ጌታችንን መቀበልና ማመን አልቻሉም ነበር፡፡

በዚህም የሐሰት ክስ በክርስቶስ ላይ በማቅረብ ዓርብ እለት ሰቀሉት፡፡ ጌታችን ግን ክሳቸውንና ተንኮላቸውን አውቆ በሞቱና በትንሣኤው ሞትን ይሽር ዘንድ ለሞት ራሱን አሳልፎ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡ ከሆሣዕና እሑድ በኋላ ያለው ሳምንት ዕለታት ‹‹***ሰሙነ ሕማማት***›› የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራና የስቅለቱ መታሰቢያ ቀናት ናቸው፡፡

## ተግባር

የሆሣዕናን ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ ተሳተፉ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትሄዱ ነጭ ወይም የታጠበ ልብስ ለብሳችሁ እና ዘንባባ ይዛችሁ ሂዱ፡፡

***<u>መዝሙር</u>***

www.zeorthodox.org

ሆሣዕና በአርያም

እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም

# የክርስቶስ ትንሣኤ

## ሠላሳኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ መማር።

**ምንባብ፡-** ማቴ. ፳፰ ፥ ፩ - ፰፣ ማር. ፲፮ ፥ ፩ - ፰፣ ዮሐ. ፳፩ ፥ ፩ - ፲፬

**መግቢያ፡-** ጌታችን ከተነሣ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ለ፵ ቀናት ለደቀ መዛሙርቱ ይገለጥላቸው ነበር። በዛሬው ትምህርታችንም ለደቀ መዛሙርቱ መገለጡን እንማራለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

### ክርስቶስ በሐሰት ክስ ሞት ተፈረደበት

ጌታችንን እየተከተሉ የሚያመስግኑትን ሕፃናትንና ሕዝቡን የተመለከቱት አይሁድ በጌታችን ላይ በቅናት ተነሱበት። ሊገድሉትም ወሰኑ፣ የሐሰት ምስክር አቁመውም ከሠሱት።

አርብ ዕለትም ተሰቀለ፣ ሞተም። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉት ሁለት ሰዎችም ከመስቀል አውርደው፣ ቀበሩት። ኒቆዲሞስን ታስታውሳላችሁ?... ከመምህር ጋር ተወያዩ

### ከዓርብ ሠርክ እስከ ቀዳሚት ሰንበት

በሥጋ ወደ መቃብር በነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ። በሲኦል ለነበሩት ለአዳም ለሔዋንና ለልጆቻቸው በሙሉ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ብሎ ነጻነትን ሰበከላቸው፤ ከሲኦል ባርነት ወደ ገነት አገባቸው።

***“ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤”*** ፩ኛ ጴጥ. ፫ ፥ ፲፰ - ፲፱

በመንፈሳዊው ዓለም ይህ እየተደረገ፤ አይሁድ በሥጋ አሳብ ወደ ጲላጦስ ቀርበው እነሳለሁ ብሏልና፤ ደቀ መዛሙርቱ ሥጋውን ወስደው ተነሳ እንዳይሉ መቃብሩ ይጠበቅ አሉ። ጲላጦስ ጠባቂዎች አሉአችሁ ሄዳችሁ አስጠብቁ አላቸው። እነርሱም ከጠባቂዎች ጋር ድንጋዩን አትመው በብርቱ የሮም ወታደሮች አስጠበቁት። ማቴ. ፳፯ ፥ ፷፪ - ፷፮

ወታደሮቹ በተጠንቀቅ የክርስቶስን መቃብር እየጠበቁ ነው። በጌታችንና መድኃኒታችን ሞት ያዘኑት ሐዋርያትም በዝግ ቤት ተሰብስበው እያዘኑ ነው። ቅዱሳት አንስትም በአይሁድ ልማድ

www.zeorthodox.org

በሣልስቱ መቃብር ሽቶ ስለሚቀባ የመቃብር ሽቶ አዘጋጁ፡፡ በዚህ ሁኔታ የአይሁድ ሰንበት ቅዳሜ አለፈች፡፡

## ትንሣኤ

እሁድ ከሌሊቱ በ፮ ሰዓት ጌታችን የተነገዘበትን ጨርቅ የሚፈታለት ሳያስፈልገው፣ ታላቁን ድንጋይ የሚያንከባልልለት ሳይሻ ከሙታን ተነሣ፡፡ አዎን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ተነሣ፡፡ ሙስና መቃብርን(በመቃብር በስብሶ መቅረትን) አጥፍቶ ተነሣ፡፡ የትንሳኤችን በኩር ሆኖ ተነሣ፡፡

ብርቱዎቹ ጠባቂዎች ሊያስቀሩት አልቻሉም፡፡ ሌሊቱን ካለ እንቅልፍ ያሳለፉት ቅዱሳት አንስት ያዘጋጁትን የመቃብር ሽቱ ይዘው ወደ ጌታ መቃብር መጡ፡፡ ፍርሐታቸው ድንጋዩን ማን ያንከባል ልልናል የሚል ነበር፡፡ ሆኖም እዚያ ሲደርሱ መልአክ ተገለጠላቸው፡፡ ታላቅ የምድር መናወጥም ሆነ፡፡ መልአኩም የመቃብሩን ድንጋይ አንከባሎ ተቀመጠ፡፡ ክርስቶስ በመቃብር አለመኖሩንና መነሣቱን በተግባር አሳየ፡፡ ወታደሮቹም እንደሞተ ሰው ሆነው ወደቁ፡፡ ኃይላቸውና ትምክህታቸው ምንም ሆነ፡፡

ከዚህ በኂላ ኃያሉ የጌታ መልአክ ለሴቶቹ እንዲህ አላቸው፡- *“እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ፡፡ ፈጥናችሁም ሂዱና፡፡ ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፡፡ እነሆም፥ ነገርኋችሁ፡፡ በፍርሐትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ፡፡”* ማቴ. ፳፰፥፩ - ፯

ሴቶችም ወደ መቃብሩ ሥፍራ ተመለከቱ መልአኩ እንደነገራቸውም ጌታችን በዚያ አልነበረም፡፡ ይህን በመስማታቸው እጅግ ተደስተው ሄዱ፡፡ መልካሙን የትንሣኤ ዜናም ለደቀ መዛሙርቱ አበሰሩ፡፡

ከዚሀ በኂላ ክርስቶስ ለመግደላዊት ማርያም ፣ ለሌሎቹ ቅዱሳት አንስት ፣ ለሐዋርያት በግልና በማኅበር ትንሣኤውን እያስረዳ ተገለጠላቸው፡፡ ከእነዚህም የሚከተለው ይገኝበታል፡-

ከጥቂት ቀናት በኂላም ደቀመዛሙርቱ በማታ ዓሣ ሊያጠምዱ ወጡ፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ምንም አላገኙም፡፡

www.zeorthodox.org

በጠዋትም ክርስቶስ በሚያጠምዱበት ዳርቻ ቆሞ ተገለጠላቸው፡፡ እርሱ መሆኑን ግን አላወቁም፡፡ ጌታችንም *"ልጆች ሆይ አንዳች የሚበላ አላችሁን?"* ሲል *"የለንም"* ብለው መለሱለት፡፡ እርሱም *"መረቡን በታንኳይቱ በስተቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ"* አላቸው፡፡ ሙሉ ሌሊቱን ሞክረው ባያገኙም፣ መረባቸውን እንደታዘዙት ጣሉ፡፡ ብዙ ዓሣ አጠመዱ ለመጎተት እስኪያቅታቸውም ተጨነቁ፣ መረቡ ሳይቀደድም ጎትተው አወጡት፤ ፍምና ዓሣም ሞልቶበት ነበር፡፡

ዮሐንስም ጌታ መሆኑን አውቆ ለጴጥሮስ ነገረው፡፡ ጴጥሮስ ነበርና ደንግጦ ልብሱን ይዞ ወደ ባሕር ገብቶ ወደ ጌታ መጣ፤ ተባብረውም መረቡን ካወጡ በኂላ ጌታችን ***"ኑ ብሉ"*** አላቸው፡፡ ሊጠይቀው የደፈረም አልነበረም፡፡ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና፡፡ ባርኮም ሊበሉ ሠጣቸው፣ በሉም፡፡ ከተነሣ በኂላ ሲገለጥላቸው ይህሦስተኛው ጊዜ ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

ጌታችን ሞቶ በሞቱ ሞትን ሽሮ ተነሥቷል፡፡ ይህ ትንሣኤም በደቀ መዛሙርቱ በኩል ለዓለም በሙሉ ተሰበከ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንም በታላቅ ክብር ታስበዋለች፡፡

## ተግባር

ትንሣኤውን ለሌሎች አስተምሩ፡፡ ከሌሎችም ጋር ስለ ትንሣኤው ተወያዩ፡፡

***መዝሙር***

አማን በአማን (4)

ተንሥአ እምነ ሙታን(4)

www.zeorthodox.org

# ሊቁ ቅዱስ ያሬድ

## ሠላሳ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ ቅዱስ ያሬድ ሕይወት ማስገንዘብ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ። እንዲህ ያለውንም ሰው አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ።"* ፪ኛ ቆሮ. ፲፪ ፥ ፪ - ፫

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ቅዱስ ያሬድና ዜማው፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻ ዓ.ም. ገጽ 97 - 102 መጻሕፍት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ።

### መግቢያ

በዛሬው ትምህርታችን ስለ ቅዱስ ያሬድ ታሪክ እንማራለን። ቅዱስ ያሬድ ማነው? ምን ሠራ? መቼ እንደነበረስ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ለመምህር አስረዱ።

ዜማን እግዚአብሔር ከሰማይ መላእክት እንዲሰማና እንዲማር ያደረገው ቅዱስ ያሬድ ለቤተ ክስቲያን ዜማን አዘጋጅቷል። በዛሬው ክፍለ ትምህርታችን የቅዱስ ያሬድን ታሪክ እንማራለን።

### የሳምንቱ ትምህርት

#### ትውልዱና እድገቱ

www.zeorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ከዛሬ 1500 ዓመታት በፊት ከአባቱ ከአብዩድና ከእናቱ ከክርስቲና በ፭፻፭ ዓ.ም. ሚያዚያ ፭ ቀን በአክሱም ተወለደ። አባቱ በልጅነቱ ሞተ። እናቱ እስከ ሰባት ዓመቱ አሳደገችው። ወንድምዋ ጌዴዎን የአክሱም ገበዝ ነበረ። እናቱም ልጅዋን እንዲያሳድገውና እንዲያስተምረው ለመምህር ጌዴዎን ሰጠችው። እርሱም መማርና ማገልገል ጀመረ።

ሆኖም በትምህርቱ ስለደከመባቸው አጎቱ ቁጣና አለንጋ አበዙበት። በዚህ የተማረረው ያሬድ አንድ ቀን ለመጥፋት ተነሳ። ከከተማውም ርቆ በእግር መጓዝ ጀመረ። ሲጓዝ ውሎ የቀዳማዊ ምንሊክ መቃብር በሆነችውና ማይኪራህ በምትባለው ቦታ ደረሰ።

ደክሞት ከአንዲት ዛፍ ሥር አረፍ ሲል ከዛፉ ስር አንዲት ትል አየ፡፡ በዛፉ ላይ እወጣለሁ እያለች ስትወድቅ፣ ይህንንም በተደጋጋሚ ሞክራ በሰባተኛው ከዛፉ ላይ ወጥታ የዛፉን ፍሬ ስትበላ አየ፡፡ ቅዱስ ያሬድ ትዕግሥትን፣ ተስፋ አለመቁረጥንም እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ትል አስተዋለ፤ ወደ ልቡ ተመልሶ፣ አጎቱን ይቅርታ ጠየቀና ትምህርቱን ቀጠለ፡፡

ትላልቅ ሰዎች ከምንም ይማራሉ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በዶሮ ጩኸት ንስሓ ገባ፡፡ ማቴ. ፳፮፥፸፬-፸፭፣ አባ እንጦንስ ከከተማው አቅራቢያ ርቆ ገዳማዊ ሕይወትን ለመጀመሩ ትምህርት የሆነችው አንዲት ተራ ሴት ነበረች፡፡ (ፊልክዩስ መግቢያ)፡፡ ቅዱስ ያሬድም ከትንሽዋ ፍጥረት ተምሮ እግዚአ ብሔርን በጸሎት ለመነ፤ እግዚአብሔርም ገልጦለት ብሉያትንና ሐዲሳትና ከመምህር ጌድዮን በአጭር ጊዜ ተምሮ አጠናቀቀ፡፡ ልጆች እናንተም አስተዋዮች ሁኑ፤ ብልህ ሰው በጥቂት ነገር ይማራልና፡፡

## ቅዱስ ያሬድ ዜማ ተገለጠለት

እግዚአብሔርም በቅዱስ ያሬድ መመስገንን በወደደ ጊዜ በአዕዋፋት ምሳሌ ሦስት መላእክትን በመላክ ወደ ሰማይ ጠራው፡፡ እርሱም ወደ ሰማይ ተነጥቆ የ፳፬ቱን ካህናተ ሰማይ ምሥጋና አይቶ ተመለሰ፡፡

ከጧቱ በ፫ ሰዓት በአክሱም ቤተክርስቲያን በታቦተ ጽዮን ፊት ቆሞ «***ሃሌ ሉያ ለአብ፣ ሃሌ ሉያ ለወልድ፣ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ***» ብሎ በልሣነ ግእዝ ዘመረ፤ የዜማውም ስልት አራራይ ነበር፡፡ ትርጓሜውም ***«ለአብ ምሥጋና ይገባል፣ ለወልድም ምስጋና ይገባል፤ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል ከጽዮን አስቀድሞ እግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ ዳግመኛም ለሙሴ የድንኳኑን ሥራ አሳየ፡፡»*** ማለት ነው፡፡ ይህችን በአርያም ከሚያመሰግኑ መላእክት የተገኘች ለማለት ***«አርያም»*** አላት፡፡

ከዚያም የተለያዩ ዜማዎችን ደርሷል፡፡ ድጓ ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት፣ ምዕራፍ፤ አንቀጸ ብርሃን የቅዱሱ የዜማ መጻሕፍት ናቸው፡፡ የቅዳሴ ዜማም በእርሱ የተዘጋጀ ነው፡፡

የቅዱስ ያሬድ ዜማ ግእዝ፣ እዝል እና አራራይ ተብለው በሦስት ይመደባሉ፡፡ በእርሱ የተዘጋጁ ፰ ምልክቶችና ፳፪ የዜማ አርእስቶች አሉ፡፡

www.zeorthodox.org

## ሦስቱ ቅዱሳን

ቅዱስ ያሬድ አቡነ አረጋዊና አፄ ገብረ መስቀል በአንድ ዘመን የነበሩ አባቶች ናቸው፡፡ ቅዱስ ያሬድ በዜማ፣ አቡነ አረጋዊ በቡራኬና በስብከት፣ አፄ ገብረ መስቀልም በንጉሥነትና አብያተ ክርስቲያንን በማስፋፋት ያገለግሉ ነበር፡፡ አቡነ አረጋዊ ደብረ ዳሞን ገዳም ሲያደርጉ፣ ንጉሡ ቤተ ክርስቲያኑን አሠራላቸው፡፡ ቅዱስ ያሬድም ቤተ ክርስቲያኑን ዞሮ ካየ በኋላ ዘመረ፡፡

በሌላ ጊዜ ሦስቱም ወደ ጣና ሐይቅ መጡ፡፡ በዚያም አቡነ አረጋዊ በእግዚአብሔር መሪነት ዛሬ ዙር አምባ የተባለውን ቦታ ባረኩት፤ ንጉሡም እንደተለመደው በሦስት ዓመት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሠራበት፤ ቅዱስ ያሬድም ዜማ እያስተማረ ሦስት ዓመት ኖሮ ወደ አክሱም ተመለሱ፡፡

አቡነ አረጋዊ ወደ አምላካቸው ከተወሰዱ በኋላ ቅዱስ ያሬድ በአክሱም ሲዘምር፥ ንጉሡና ሕዝቡ ሁሉ ተነስተው ተመስጠው በፊቱ እንደከበቡ ንጉሡ ሳይታወቃቸው የቅዱሱን እግር በዘንጋቸው ጫፍ ወግተው ተደግፈውት ቆመዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ቅዱስ ያሬድም እርሳቸውም አልታወቃቸውም፡፡ ዜማውን ሲፈጽም ሁሉም ታወቃቸው የቅዱሱም ደም እንደ ውኃ ፈሰሰ፡፡ ንጉሡም አዝነው ለደምህ ካሳ ምን ላድርግልህ አሉት፡፡ ቅዱስ ያሬድም በብሕትውና ለመኖር ስለሚፈልግ ብቻውን እንዲኖር ንጉሡ እንዲፈቅድለት ጠየቀ፡፡ ንጉሡም በጥያቄው ቢያዝኑም ቃል ስለገቡ ፈቅደው ሸኙት፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ያሬድ በሰሜን ተራሮች በብሕትውናና በማስተማር ኖሮ ግንቦት ፲፩ ቀን ፭፻፷፩ ዓ.ም. ወደ አምላኩ ተወሰደ፡፡

## ማጠቃለያ

ቅዱስ ያሬድ ከ፭፻፭ — ፭፻፷፩ ዓ.ም. በዚህ ምድር የነበረ ሲሆን ሰማያዊውን ዜማ ለኢትዮጵያ እና ለመላው ዓለም ያስተላለፈ ነው፡፡

## ተግባር

በየክፍለ ጊዜው በዝማሬ፣ በቅዳሴ ተሰጥዖ፣ ወዘተ የሚሰጣችሁን የቅዱስ ያሬድን የዜማ ትምህርት በአግባብ ተከታትላችሁ ከምታውቁት ክፍል አስታውሳችሁ ለወላጆቻችሁ አሰሟቸው፡፡

www.zeorthodox.org

# ኅብስተ ሕይወት

## ሠላሳ ሁለተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** የክርስቶስ *ሥጋና* ደም የመቀበልን አስፈላጊነት መግለጽ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም "* ዮሐ. ፮ ፥ ፶፫

**ምንባብ፡-** ዮሐ. ፮ ፥ ፴፭- ፍም

### መግቢያ

ክርስቶስ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በቅፍርናሆም ስለ ኅብስተ ሕይወት አስተማረ። በዚህ ትምርታችንም ኅብስተ ሕይወት ምን እንደሆነ ጥቅሙንና ሳይቀበሉት የመኖርን ውጤትም እናያለን።

### የሳምንቱ ትምህርት

ብዙ ሰዎች ክርስቶስ የሚሠራቸውን ድንቅና ተአምራት በማየት ብቻ ይከተሉት ነበር። አንድ ቀንም የገሊላ ባሕር ወደሚባለው ሲጓዝ ብዙ ሕዝብ እንደተለመደው ተከትሎት መጣ። በዚያ ቀንም ሁለት ዓሣ እና አምስት እንጀራ አበርክቶ አምስት አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ።

ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም በጀልባ ሄደ ሕዝቡም መሄዱን ሲያውቁ በሚቀጥለው ቀን በንጋት ተከትለው ወደ ቅፍርናሆም መጡ።

ጌታችንን ሲያገኙትም መቼ እንደመጣ ጠየቁት እርሱም *"የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።"* አላቸው። ሕዝቡም *"የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ?"* አሉት። ጌታችንም *‹‹የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው።››* አላቸው።

*‹‹እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው... የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሠጥ ነውና።››* አላቸው። ሕዝቡም ጌታሆይ *"ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን"።* አሉት። ጌታም መልሦ *"የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።"* አላቸው።

www.zeorthodox.org

‹‹በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፡፡***የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ*** አባቶቻችሁ በበረሃ መና በሉ ሞቱም፡፡ ከሠማይ የወረደ ኅብስት ይህ ነው ከርሱ የሚበላም አይሞትም፡፡ ***ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፡፡*** ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘላለም አይራብም ለዘላለም ይኖራል እንጂ፤ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የምሠጠው ኅብስት *ሥጋዬን* ነው፡፡

የሰውን ልጅ *ሥጋውን* ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡ *ሥጋዬን* የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፡፡ *ሥጋዬን* የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡ አባቴ እንደላከኝ፣ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል፡፡ ከሠማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፡፡***"ከዚህ የሚበላም ለዘለላም ይኖራል፡፡***›› አላቸው፡፡

የተከተሉት ሕዝብም እንዴት *ሥጋውን* ልንበላ ይሰጠናል ብለው አጉረመረሙ፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ይህ ለመቀበል ከባድ ነው አሉት፡፡ ብዙ ሕዝብም  ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ ስለዚህ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ***"እናንተስ መመለስ ትፈልጋላችሁ?"*** አላቸው፡፡

ስምዖንም መልሶ ***"ወዴት እንሄዳለን፣ አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፣ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም"*** ብሎ መለሰለት፡፡ ደቀመዛሙርቱም ተከተሉት የክርስቶስን *ሥጋና* ደም ለመቀበልም(በጸሎተ ሐሙስ) የመጀመሪያዎቹ ሆኑ፡፡

## ማጠቃለያ

አንዳንዶች ክርስቶስን የሚፈልጉት አበርክቶ ስላበላቸው ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ ምክንያት ሊሆነን አይገባም፡፡ እርሱ እንደ አባት እንደ እናት የሚያስፈልገንን የሚያዘጋጅልን ቢሆንም የሚቀድመው ጽድቁና መንግሥን መፈለግ ነው፡፡ ***"ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል"*** ማቴ. ፮ ፥ ፴፫፡፡

በጌታችን ትምህርት መሠረት *ሥጋውንና* ደሙን ካልተቀበልን ሕይወት የለንም፡፡ ***"የሰውን ልጅ (የክርስቶስን) ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም፡፡"*** ዮሐ. ፮ ፥ ፶፫፡፡ የክርስቶስን ቅዱስ *ሥጋውንና* ክቡር ደሙን ለመቀበል መዘጋጀት አለብን፡፡ ምክንያቱም በ*ሥጋውና* ደሙ፡-

- የዘለላም ሕይወት እናገኛለን
- በእርሱ እንኖራለን እርሱም በእኛ ይኖራል፡፡

አንዳንዴ የመጻሕፍትን ትምህርትና መልእክት መረዳት ሊያቅተን ይችላል፡፡ ነገር ግን በእምነት ሆነን፤ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ***"ጌታ ሆይ ወዴት እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ"*** ብለን በትሐትና ስንቀርብ፣ ወደ እውነተኛው መረዳትና መገለጥ እንደርሳለን፡፡

www.zeorthodox.org

ደቀ መዛሙርቱ ከመለኮታዊ ምሥጢር ለመካፈል የበቁት በትሕትና ተከትለውት ነውና፡፡

## ተግባር

ዘወትር በሰንበት ቅዱስ ቁርባን ተቀበሉ (ቁረቡ)፡፡

*የሙከራ ጥያቄዎች፡*

1. ክርስቶስ በገሊላ ባሕር የፈጸመው ተአምር ምን ነበር? ሕዝቡስ ለምን ተከተሉት?
2. እውነተኛው የሕይወት መብል /ኅብስተ ሕይወት/ ምንድነው?
3. ክርስቶስ በፍቅርናሆም ላስተማረው ትምህርት ደቀመዛሙርቱ ምን አሉ?
4. የጌታችንን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በመጀመሪያ የተቀበሉት እነማን ናቸው?
5. ቅዱስ ቁርባን ትቀበላላችሁ? ከቅዱስ ቁርባን ውጪ መኖር ምን ያስከትላል?

www.zeorthodox.org

# ልደታ ለማርያም

## ሠላሳ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ድንግል ማርያም የተነገረ ትንቢት፣የታየ ሕልምና የልደትዋንም ታሪክ መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ"*** ሉቃስ ፩ ፥ ፳፰፡፡

**ምንባብ፡-** የግንቦት ፩ ስንክሣር እና ነገረ ማርያም፡፡

## መግቢያ

ዛሬ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ እንማራለን፡፡ እግዚአብሔር በቅድስናና ንጽሕናዋ እናቱ እንድትሆን መረጣት፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

በኢየሩሳሌም ባለ ጸጋ የሆኑ ነገር ግን ንብረታቸውን የሚወርስ ልጅ ያልነበራቸው ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነበሩና ልጅ እንዲሠጣቸው ዘወትር ይጸልዩ ነበር፡፡ አንድ ቀን ላም ልጅ ስትወልድ የተወለደችዋም ሌላ እየወለደች ስድስት ትውልድ ከደረሰ በኋላ ስድስተኛዋ ጨረቃ ስትወልድ፣ ጨረቃዋም ፀሐይ ስትወልድ በሕልም አዩ፡፡

እንደ ዮሴፍ ሕልም ወደሚተርጉም ሰው ሄደው ያዩትን ሕልም ነገሩት፡፡ ልጅ እንደሚያገኙ እና እስከ ስድስት ትውልድ እንደሚሄድ ከዚያም፣ በስድስተኛው ትውልዳቸውም የምትወለድ ታላቅ ልጅ እንዳለች የጨረቃዋን ምሳሌ ከተረጎመላቸው በኋላ ፀሐይ ምን እንደሆነ መተርጎም እንዳልቻለ ነገራቸው፡፡

ጥንዶቹም ሕልም ተርጓሚው እንደነገራቸው እስከ ስድስት ትውልድ ልጆችና ቤተሰቦች ተወለዱላቸው፡፡ ስድስተኛዋም ትውልድ ሐና ትባላለች፡፡ ቤተሰቦችዋም ኢያቄም ለተባለ መልካም ሰው አጭዋት፡፡ ኢያቄም እና ሐና አብረው ለረጅም ጊዜ ኖሩ፡፡ ልጅ ሳይወልዱም አረጁ፡፡

www.zeorthodox.org

ሐና እና ኢያቄም ድሆችን የሚረዱና ለእግዚአብሔር ትዕዛዝም ታማኞች ነበሩ፡፡ ተስፋ ሳይቆርጡ በመጸለያቸው እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ መልአኩን ወደ ኢያቄም ላከ፡፡ የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄም ተገልጾ ውድ ልጅ እንደሚሰጣቸው አበሠረው፤ ኢያቄምም ለሐና ነገራት ሐናም ይህንኑ በእምነት ተቀብላ ልጅ ቢሰጣቸው መልሰው እንደሚሰጡት ተስለው ኖሩ፡፡

ሁለቱም በሕልም ተረድተውም ሐና ጸነሰች፡፡ የመውለጃዋ ጊዜዋ አልፎ ስለ ጸነሰችም ዘመዶችዋ ተደነቁ፡፡ ሐና አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት፡፡ አንድ ቀን ሐና መጽነስዋን ስምታ ሆድዋን

በእጅዋ ዳስሳ ካረጋገጠች በኋላ ዓይኗን በዚያው እጅዋ ስትነካው ዓይንዋ በራላት፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና፡፡ ሉቃ ፩ ፥ ፴፯፡፡

ሌሎች ሰዎች ይህን ተአምር ሰምተው በመምጣት ከተለያዩ ነገሮች ተፈወሱ፡፡ ነገር ግን አይሁድ ቀንተው ሐና እና ኢያቄም እንዲሰደዱ አደረጉ፡፡ ሐና እና ኢያቄምም ወደ ሊባኖስ ተራራ ተሰደዱ፡፡ በዚያም ግንቦት ፩ ቀን ሐና ተወዳጅዋን ልጅ ወለደች ስምዋንም ማርያም አለቻት፡፡ እንደ ስለታቸውም ድንግል ማርያም እስከ 15 ዓመትዋ በቤተመቅደስ እያገለገለች ኖረች፡፡

እግዚአብሔርም በቅድስና ኖረው በንጽሕና ከወለድዋት ልጃቸው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ለማዳን ፈቃዱ ሆኖ መረጣት፡፡

## ማጠቃለያ

የጌታችን እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሐና እና ኢያቄም ከሚባሉ ቅዱሳን ቤተሰቦችዋ ግንቦት ፩ ቀን ተወለደች፡፡ በስዕለት የተገኘችዋ ድንግል ማርያም ለእናትዋ አንዲት ናት፡፡

ኢያቄምና ሐና በትዕግሥት በመጠበቃቸው ልጅ አገኙ፡፡ እግዚአብሔርን በእምነት ሆነን ከጠየቅነው የለመነውንና የጠበቅነውን ሁሉ እንቀበላለን፡፡

## ተግባር

ይህንን የተማራችሁትን ትምህርት ወደቤታችሁ ስትመለሱ ለወላጆቻችሁና ለሌሎች ሰዎች ተርኩላቸው፡፡

**መዝሙር**

ምሥራቀ ምሥራቃት ሙፃዓ ፀሐይ እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ
ዘመና ሙዳይ (4) ማርያም ዘመና ሙዳይ

www.zeorthodox.org

# ዕርገት

## ሠላሳ አራተኛ ሳምንት

**ዓላማ** ፡- ስለክርስቶስ ዕርገትና ከማረጉ በፊት ያስተማረውን ትምህርት መማር

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *"እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* የሐዋ.ሥ. ፩ ፥ ፰

**ምንባባት፡-** ማር. ፲፮ ፥ ፲፱ - ፳፣ ሉቃ. ፳፬፥፶፣ የሐ.ሥ. ፩ ፥ ፮ - ፲፩፡፡

### መግቢያ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለ፴፫ ዓመታት ከሦስት ወራት በምድር ኖሯል፡፡ በ፴ ዓመቱ ተጠመቀ ለ፫ ዓመታት አስተማረ፣ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ቤዛ ሆነልን፡፡ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ተገለጠላቸው፡፡

ዛሬም ጌታችን ኢየሱስ ከዕርገቱ በፊት ከተነሣ በኋላ ስላስተማራቸው ትምህርቶች፣ ደቀ መዛሙርቱን ስላዘዛቸው ትዕዛዝና ስለ ዕርገቱ እንማራለን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

ጌታችን ከተነሣ በኋላ ባሉት ፵ ቀናት በተለያዩ ጊዜያት ለደቀመዛሙርቱ ተገልጾ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምራቸው ነበር፡፡ ስለ ክርስቶስ የተነገረውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት ከዚያ በፊት አላስተዋሉም ነበር፡፡ ጌታችንም ስለ እርሱ የተጻፉትን ተረጎመላቸው፣ አዕምሮአ ቸውንም ከፈተላቸው መጻሕፍትንም አስተዋሉ፤ እምነታቸውን አጸናላቸው፡፡ ስለ ትንሣኤው የነበራቸውን ጥርጣሬም ከልቦናቸው አጸዳላቸው፡፡

**የሚከተሉትን ትዕዛዛት እና ኃላፊነቶችም ሰጣቸው፡-**

www.zeorthodox.org

- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፡፡ ማር ፲፮ ፥ ፲፭
- ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ፡፡ የሐዋ ፩ ፥ ፭
- እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ... አስተምሯቸው፡፡ ማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱ - ፳
- እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡፡ የሐዋ.ሥ ፩ ፥ ፰

በወንጌል ለመስበክ እና በስሙ ለማጥመቅ ወደ ዓለም ሲወጡ፣ እንደሚገረፉ ወደ ነገሥታት የፍርድ አደባባይም እንደሚያወጧቸው ነገሯቸዋል። እስከመጨረሻም የጸና ግን ይድናል በማለት እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ኃይልን እንደሚያገኙም ቃል ገብቶላቸዋል። ከሙታን በተነሣ በ፵ ኛው ቀን ደቀመዛሙርቱን ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸውና ባረካቸው። ተሰብስበው ትምህርቱን እየሰሙም ***ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ። ወደ ሰማይም ዐረገ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው።***

ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው ***"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው።"*** ደቀ መዛሙርቱም ጌታ ካረገበት ከደብረ ዘይት እግዚአብሔርን እያከበሩ ተመለሱ። እንደታዘዙት መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉም በኢየሩሳሌም ቆዩ ።

## ማጠቃለያ

ጌታ ከተነሣ በኋላ ፵ውን ቀናት እያስተማረ እና ሐዋርያትን እያዘዘ ከቆየ በኋላ የሚያገኛቸውን መከራ ነገራቸው፤ የሚጸና ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚያገኝም ቃል ገባላቸው።

በደብረ ዘይት ሰብስቦ አስተምሮ ባርኳቸው ዐረገ። እንደ ክርስቲያን ምስክሮች ልንሆን ተጠርተናል። ምስክርነትም መናገር ብቻ ሳይሆን ትዕዛዛቱን መጠበቅ ነው። ***"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"*** ማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱ - ፳

በዕርገት ሐዋርያት የታዘዙት ለእኛም የሚሆን ቃል ነው። ኢየሩሳሌም የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎትና ለአገልግሎት መሄድ መተው የለብንም።

www.zeorthodox.org

## ተግባር

የተማራችሁትን ለሌሎች አስረዱ።

# ለሌሎች መልካም አርአያ መሆን

## ሠላሳ አምስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ለሌሎች መልካም አርኣያ የመሆንን ኃላፊነትን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ፡፡"*** ዮሐ ፲፫ ፥ ፲፫

## መግቢያ

ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዴት መኖር እንዳለብን አስተምሮናል፤ በመልካም *ሥራዎቹም* ምን ማድረግ እንዳለብን ምሳሌ ሰጥቶናል፡፡ ዛሬም በቃልና በተግባር ማስተማሩን እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ***"ጠላቶቻችሁን ወደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤"*** ማቴ ፭ ፥ ፵፬ - ፵፭ ሲል አስተምሮዋል፡፡ ለሚሰድቡትና ለሰቀሉት ምሕረትን በመለመንም ተግባራዊ ምሳሌውን ተቶልናል፡፡ የክርስቶስ ሰቃዮች ከሥር ሆነው እየተሳደቡ እርሱ በመስቀል ላይ ሆኖ ***" አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ"*** ሉቃ ፳፫ ፥ ፴፬፡፡ ጌታችን ራስን ለሌሎች አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር የለም ብሎ ነበርና፡፡ ዮሐ ፲፭ ፥ ፲፫ ራሱን ለመስቀል በመስጠትም ምሳሌውን ተቶልናል፡፡

***"ሰው ከውኃ እና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት አይገባም፡፡"*** ዮሐ ፫ ፥ ፭ ብሎ እንዳስተማረ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ አርኣያ ሆኖናል፡፡

www.zeorthodox.org

በመጨረሻም ከመሰቀሉ በፊት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቧል፡፡ እንዲህም ብሎዋቸዋል፡፡ ***" እንግዲህ እኔ ጌታ እና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡"*** ዮሐ ፲፫ ፥ ፲፬ - ፲፭

ቅዱሳን ሐዋርያት ክርስቶስ እንዳዘዛቸው ፈጽመዋል፡፡ በፍቅር ወንጌልን ሰብከዋል፣ ለሌሎች አርአያ ሆነዋል፤ ሌሎቹም በሕይወታቸው አርአያ እንዲሆኑ አስተምረዋል፡፡

ለዚህ አብነት የሚሆነን የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ነው፡፡ ***"በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን፡፡"*** 1ኛ ጢሞ ፬ ፥ ፲፪

## የዚህ ትምህርት ጠቃሚ መልእክቶች

በሕይወታችን ለሌሎች መልካም አርኣያ መሆን ያስፈልገናል፡፡ ወጣት ወንድሞች፣ እህቶችና ልጆች ከታላላቆቻቸው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም መማር አለባቸው፡፡ ክርስቶስ ምሳሌ እንደሆነን እኛም ስለሌሎች ምሳሌ መሆን አለብን፡፡

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ የተወልን ምሳሌዎች ፍቅር፣ ትሕትናና ሌሎች መልካም ሥነ ምግባሮች ናቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዛሙሩ ጢሞቲዎስ እንደጻፈለት፤ እኛም በሚከተሉት መንገዶች ለሌሎች አርአያ መሆን ያለብን፦

***በቃላቶቻችንና በንግግራችን፦*** ከሌሎች ጋር በመልካም ቃል ተነጋገሩ፤ ስትነጋገሩም አስቀያሚና ክፉ ቃላትን ሳትጠቀሙ ይሁን፡፡

***በልግስና፦*** የቸገረውን እርዱ፣ለሌሎች ይህንኑ አስተምሩ፡፡

***በመንፈሳዊነት፦*** የመንፈስ ፍሬ የሆኑትን ፍቅርን፣ ሰላምን፣ ትዕግስትን፣ መልካምነትን…ወዘተ ፈጽሙ፡፡

***በእምነት፦*** በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት ጠብቁ እንደ ትዕዛዙም ኑሩ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ መሳተፍ አለብን፡፡ የጸሎትና ጾም ሕይወትም የመንፈሳዊነት መገለጫና የእምነት ተግባራት ናቸውና እነዚህን አዳብሩ፡፡

***ንጽህና፦*** በሥጋና በነፍስ ንጹሐን ሁኑ፡፡ በሥጋ ንጹሕ መሆን ማለትም አካላዊ ዝግጅቶችን ለምሳሌ መታጠብ፣ በሥርዓት መልበስ ወዘተ… ፈጽማችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ እንደም ትመጡት ሁሉ ከጋብቻ በፊት ተገቢ ካልሆነ ግንኙነት ተጠበቁ፡፡ መንፈሳዊ ዝግጅቶች ማለትም መጸለይና ግብረገብነት የጎደላቸውን ነገሮች ከማድረግ ይልቅ መንፈሳዊ ነገሮችን ለማሰብና ለመለማመድ መዘጋጀት ነው፡፡

www.zoorthodox.org

## ጥያቄና መልመጃዎች

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አርአያ እንደሆነን ምሳሌ (ዎችን) ጥቀሱ።

_______________________________________________

2. ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዛሙሩን ጢሞቲዎስን የመከረው ምንድን ነው?

_______________________________________________

3. በተግባርና በቃል ማስተማር ለምን ይጠቅማል?

_______________________________________________

4. ሌሎች በተግባር ያስተማሩአችሁን መልካም ነገር አብራሩ።

_______________________________________________

5. ታናናሾቻችሁ የምትሠሩትን ይከተላሉ? እንዴት?

_______________________________________________

www.zeorthodox.org

# ቅዱስ ላሊበላ

## ሠላሳ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በክርስትና መጽናት እና ማደግን ከቅዱሳን ሕይወት በመነሣት ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ፤ የማይጠፋም የዘለዓለም ስም እሰጣቸዋለሁ፡፡... በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፡፡"*** ኢሳ. ፶፮ ፥ ፬ - ፯

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ገድለ ቅዱስ ላሊበላ

### *መግቢያ*

ቅዱስ ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕረግ ከሠጠቻቸው ኢትዮጵያውያን ነገሥታት አንዱ ነው፡፡ ከዓለማችን ድንቅ ቅርሶች መካከል አንዱን ያነጸውና በቅድስና ኑሮው የሚታወቀውን የቅዱስ ላሊበላን ታሪክ በዛሬው ትምህርታችን እንማራለን፡፡ የቅዱሳን አምላክ ከሁላችንም ጋር ይሁን፡፡ አሜን!!!

## የሳምንቱ ትምህርት

### ከልደት እስከ ንግሥና

በጥንትዋ ሮሃ በዛሬዋ ቡግና የሚገኙትን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ያነፀው ቅዱስ ንጉሥ ላሊበላ አባቱ ሥዩም እናቱ ኪረወይና ይባላሉ፡፡

ከሁለቱ የተገኘው ሕፃን ታኅሣስ ፳፱ ቀን ሲወለድ ንብ ከቦት ነበርና - እናቱ በአገውኛ ላሊበላ ብላ ጠራችው፡፡ ***"ላሊበላ ብሂል ንህብ አእመረ ጸጋሁ - ላሊበላ ማለት ንብ ጸጋውን አወቀ ማለት ነው"*** ይላል ገድሉ፡፡ ይህም ወደፊትም ንጉሥ ይሆናል ተብሎ ተተረጉመ፡፡ ይህም ለመንገሥ ያስብ የነበረውን ወንድሙን ሐርቤን ቅር አሰኝቶል፡፡ በኋላም ሐርቤ ነገሰ ላሊበላም በሞገስ አደገ፡፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ተወዳጅ የነበረው የሮሃው ልዑል - ላሊበላ ፤ በመልካም ስብእናው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እና በበጎ ተግባሩ የሚከበርና እና ለንግሥና የሚናፈቅ ልዑል ሆነ፡፡

ላሊበላ የመጀመሪያውን ትምህርት በቤተሰቡ አካባቢ ከተማረ በኋላ ወደ ጎጃም መርጡለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመጓዝ ትምህርቱን አስፋፍቷል፡፡ በነበረው ቀለም የመቀበል ችሎታ

www.zeorthodox.org

የቀኑበት ሌሎች ተማሪዎች ችግር ስለፈጠሩበት ትምህርቱን አቋርጦ ወደ ላስታ ተመልሶ፤ መስቀል ክብራን አገባ፡፡

ከወንድሙ የሚያጣሉት ነገር ሠሪዎች እና በአባት ብቻ የምትወለደው እኅቱ /ዮዲት/ በንጉሡ ላይ ይነግሳል ብለው በክፋት ተነሡበት፡፡ በአንድ ወቅትም እኅቱ በአባት እና በእናት ለሚወለዳት ወንድም የተቀረቀረች መስሏት መርዝ ቀላቅላ ሠጠችው፡፡ ጌታችን ‹‹***በእኔ የሚያምኑ... የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፡፡***›› ማር. ፲፮ ፥ ፲፰ እንዳለ ለሦስት ቀናት ራሱን ከሣተ በኋላ ተነሣ፤ አብያተ ክርስቲያናቱን ያነጸበትን ራእይ በዚህ ጊዜ  እንዳየም ገድሉ ይገልጣል፡፡

በዚህ ያልበቃቸው ክፋ አሳቢዎች በድጋሚ ነገር ሠርተው ከወንድሙ ጋር አጣሉት፤ በዚህ ምክንያትም ታስሮ ተገረፈ፡፡ ከዚያም ከክፉ ሰዎች ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻላል ብሎ ትግራይ ውስጥ መደባይ ታብር በተባለ ቦታ ሚስቱን አስቀምጧት፤ ወደ በረሐ ተሰዶ በምሥራቅ ኢትዮጵያ ለዓመታት ኖረ፤ በዚያም ከእግዚአብሔር በተሠጠው ጥበብ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ሠራ፡፡ አንዳንድ ምንጮች በስደቱ ወቅት ኢየሩሳሌም እንደሄደ ያትታሉ፡፡

ከዚያም ወንድሙ ተጸጽቶ ስላስጠራው ወደ ቤተመንግሥት ተመለሰ፡፡ ንጉሥ የነበረው ወንድሙም ሥልጣኑን ለላሊበላ አስረከበው፡፡ በቅድስና ኑሮው በአስተዳደር ብቃቱ እና በሕንጻ ጥበቡ ቅዱስ ላሊበላ የነበረውን ክርስቲያናዊ ዝና በመስማት ከአምስት ሺህ በላይ ግብፃውያን ክርስቲያኖች ወደ ሮሐ መጥተው ነበር፡፡

## የዓለት ላይ አብያተ ክርስቲያናት ሥራ

የዛጉዌ ነገሥታት ከሚታወቁባቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው ዋሻ ውስጥ በመገንባትና ከዓለት ላይ በመፈልፈል አብያተ ክርስቲያናትን ማነፃቸው ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ የተጀመረው በ፬ ኛው መቶ ክ/ዘመን በአጤ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ቢሆንም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የላቀ ደረጃ የደረሰው ግን በዛጉዌ ነገሥታት ነው፡፡ ይህም በዘፈቀደ ሳይሆን ራሱን የቻለ ሃይማኖታዊ ትርጉምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንድምታ አለው፡፡

www.zeorthodox.org

የላሊበላን ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚያስታውስበት ሌላው ምክንያት ጻድቁ ንጉሥ ከአንድ ቋጥኝ አስፈልፍሎ የሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ከእነዚህም ዛሬ በላሊበላ የሚገኙት ፲፩ ውቅር አብያተክርስቲያናት ፡-

1. ቤተ ደናግል
2. ቤተ ማርያም
3. ቤተ መድኃኔዓለም
4. ቤተ መስቀል
5. ቤተ ጎልጎታ
6. ቤተ ቅዱስ ሚካኤል
7. ቤተ ገብርኤል
8. ቤተ አባ ሊባኖስ
9. ቤተ መርቆሬዎስ
10. ቤተ አማኑኤል
11. ቤተ ጊዮርጊስ ናቸው

ተመራመሪው አል ቫሬስ ስለ ቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በ፲፮ኛው መ/ክ/ዘመን የሚከተለውን ብሎ ነበር ፡-*"ስለእነዚህ ሕንፃዎች መፃፍ ደከመኝ። ምክንያቱም የማየውን ማመን አቃተኝ። ከዚህ ተጨማሪ ብፅፍ ማንም አያምነኝም፤ ሐሰተኛ እባላለሁና። ስለዚህ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ የፃፍኩት ሁሉ እውነት ነው። ምንም ከራሴ የጨመርኩት የለም። እንዲያውም ያልፃፍኩት እና የተውኩት ብዙ ነው፤ ውሸታም ተብዬ እንዳልወቀስ። ዓለም ይህን ድንቅ ሥራ እንዲያውቅልኝ እመኛለሁ።"* ምንጭ ፡- ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ መጽሐፍ (the sign and the seal)

ላሊበላ በሮሐ ካነፃቸው በተጨማሪ በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር እስከ ሰባ (ሃያ ሦስት የሚሉም አሉ) አብያተ ክርስቲያናትን አንጿል።

## የሰላማዊነት እና መልካም ግንኙነት ፍሬዎች

ቅዱስ ላሊበላ በዘመኑ ከግብጻውያን ጋር የነበረው ግንኙነት በመልካም ጎኑ የሚጠቀስና በአብዛኛው በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ነበር። ንጉሡ መልእክተኞቹን ከብዙ ገጸ በረከት ጋር ልኮ አባ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ከእስክንድርያ አስመጥቶ የደመቀ አቀባበል እንደተደረገላቸው ተዘግቧል።

ቅዱስ ላሊበላ በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ወቅት ድል ከቀናው ሳላአዲን ከተባለ ግብፃዊ ሡልጣን ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው ቅዱሳት መካናት በኢየሩሳሌም በስጦታ ተበርክቶለታል። ከእነዚህም መካናት መካከል በጎልጎታ የጌታ መቃብር አጠገብ ያለው እሌኒ ንግሥት መስቀሉን ያስወጣችበት ዋሻና፣ በቤተልሔም ጌታ የተወለደበት በረት ይገኙበታል።

www.zoorthodox.org

በመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክ ውስጥ ምዕራባውያኑ(የሮም) ካቶሊኮች ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት በሚል ሰበብ ከእስላሞች ጋር ያደረጉት ስምንት የመስቀል ጦርነቶች ነበሩ። ጦርነቱ ፍትሐዊ አለመሆኑና በካቶሊካውያኑ ብቻ የተያዘ ስለነበር አርቶዶክሳውያኑ አልተሳተፉበትም ውጤቱም መልካም አልነበረም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቅዱስ ላሊበላ ከሳላአዲን (ከሙስሊሞቹ መሪ) በኢየሩሳሌም ያሉ ቦታዎችን በስጦታ ያገኘው ኢትዮጵያ በመስቀል ጦርነት ጊዜ ገለልተኛ ሁና በሰላማዊነት በመቆየቷ

ነው፤ ይህም ከኢትየጵያውያን በተጨማሪ ግብጻውያን እና ካቶሊካውያን መነኮሳት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት መጠጊያ እንዲያገኙ አስችሎል፡፡

## ቅዱሱ እና ቅዱሳኑ

በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት ታላቁ አባት ጻድቅ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ  መጥተዋል፡፡ ንጉሡ ቤተክርስትያኑን ሠርቶ እንደፈጸመ በጸሎት ቦታው ሆኖ ሲጸልይ በእግዚአብሔር ጸጋ ፊታቸው የሚያበራ፤ በጣም ረጅም የሆነና የሚያምር ጢም ያላቸው አባት በአናብርት እና አናብስት ተከበው መጡ፤ ቤተ ክርስቲያኑንም በመደነቅ ይመለከቱ ነበር - እኒህ አባት አቡነ ገብረ መንፈስቅዱስ ናቸው፡፡ ንጉሡ ጸሎቱን ጨርሶ ወደ እርሳቸው ቀርቦ ***ሰማያዊ ኖት ወይስ ምድራዊ*** ሲላቸው እርሳቸውም ***ይህ ሕንጻ የምድር ነው የሰማይ*** አሉት፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ተነጋገሩ፡፡

ወደ ቤቱ ወስዶ ለተወሰኑ ቀናት አስተናገዳቸው፤ በጻድቁ ገድል እንደተመለከተው ቅዱስ ላሊበላ የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን መንፈሳዊነት ወዶ የተለየ የክብር ቦታ ሰጣቸው፡፡ እርሳቸውም ጥቂት ቀናት እያስተማሩ በሮሃ ቤተ መንግሥት ሰነበቱ፡፡

በመቀጠልም ቅዱስ ላሊበላ ቦታ ልስጠዎትና በዚህ እየጸለዩ እየባረኩ፣ ወንጌልንም እያስተማሩ ይቀመጡ አላቸው፡፡እሳቸው ግን እኔ እንዳስተምር እና እንድጸልይ የታዘዝኩት በዚህ አይደለም በደብረ ታቦር አምሳል በሆነች በዝቋላ ተራራ ስለሆነ ወደዚያው እሔዳለሁ የአንተ ግን ከተማህ የተባረከ ነው፤ አንተም የተባረክህ ነህ ብለው ወደ ዝቋላ  ለመሔድ ሲነሡ ዝቋላ ድረስ ሸኟቷቸው እንደተመለስ ተጽፏል፡፡ ሸኝቶ ሲመለስም የአዳዲ ማርያምን ቤተ ክርስቲያንን አነፃት ፡፡

ላሊበላ ከሚታወስባቸው ነገሮች መካከል ሌላው የግል ኑሮውን እንደ መንግሥት በሚሰበስበው ግብር ላይ ሳይመሰርት ለመንግሥት ሥራ ብቻ ማዋሉ ሲሆን፤ ለኑሮው የሚሆነውን ገንዘብ ያገኝ የነበረው በእጁ ተግባረ እድ እየሠራና ያንን እየሸጠ ነበር፡፡

ከዚህም በላይ ራሱ እየሠራ የሚያሠራ ንጉሥም ነበር፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ልብሰ መንግሥቱን አውልቆ ተራ ልብስ በመልበስ ለሥራ ይሰለፍ ነበር፡፡

www.zeorthodox.org

የንጉሥ ላሊበላ ሚስት አባ ሊባኖስ የተባሉትን ቅዱስ ታከብር እና ትወዳቸው ነበር፤ ንጉሡም እንዲሁ ያከብራቸው ነበር፡፡ (አባ ሊባኖስ /አባ መጣዕ/) በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩ ብዙ ተአምራት የፈጸሙ ቅዱስ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ከ፲፩ዱ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ቤተ ሊባኖስ የሆነው ከአዲግራት በስተ ምዕራብ የሚገኘውን ደብረ ሊባኖስ ዘሺምዛና ገዳምም በጣም ይወድ ነበር፡፡ ላሊበላ ለዚህ ገዳም ብዙ ርስት ሰጥቶ ነበር፡፡ በኋላም በሚስቱ በቅድስት መስቀል ክብራ ስም እንደገና ጉልት ሰጥቷል፡፡

## ማጠቃለያ

ዐፄ ላሊበላ ኢትዮጵያን ለ፵ ዓመታት ከገዛ በኋላ በ፲፻፪፻ ዓ.ም / በ፲፻፩፻፸፫ ዓ.ም ነው የሚሉም አሉ፡፡/ ሰኔ ፲፪ ቀን አርፎ በቤተ ጎልጎታ ተቀበረ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ቅድስናውን አረጋግጣ ቅዱስ ብላ ታቦት በስሙ ቀርፃ ገድሉን ጽፋ ታከብረዋለች፡፡

የተወለደበት ቀን ታኅሣስ ፳፱ እና ያረፈበት ሰኔ ፲፪ መታሰቢያ በዓሉ በየዓመቱ ይከበራል፡፡ አምላካችን እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሱ በረከት ያካፍለን፡፡አሜን!!!

## ተግባር

የቅዱስ ላሊበላን ታሪክ ለሌሎች ደግማችሁ አስረዱ፡፡

www.zeorthodox.org

# ማመስገን

## ሠላሳ ሰባተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ሁልጊዜ ስለ ሁሉም እግዚአብሔርን ስለማመስገን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"እግዚአብሔርንም እያመሰገነ እያከበረም ተመለሰ" ሉቃ.፲፯ ፥ ፲፮***

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ሉቃ. ፲፯ ፥ ፲፩ - ፲፱፣ የምሥጋና ሕይወት (The Life of Thanks Giving) በአቡነ ሲኖዳ

## መግቢያ

ልጆች እግዚአብሔርን መቼ ታመሰግኑታላችሁ? አንዳንድ ጎበዝ ልጆች ሁሌም እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ግዴለሾች ናቸው፡፡ ማመስገን እንዳለባቸውም አያውቁም፡፡ መምህር ልጆች መቼ ተመስገን እና እግዚአብሔር ይስጥልኝ ማለት እንዳለባቸውያስረዷቸው ፡፡

አንድ ቀን ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መንደር ሲገባ፤ ቆዳቸው በበሽታ የተጎዳ (በለምጽ) ዐሥር ሰዎች መጥተው ሰገዱለት፤ እነዚህ ሰዎች ከማንኛውም ሰውጋር እንዳይገኙ ተከልክለው ነበር፡፡ ወደ ጌታ ቀርበውም ጌታ ሆይ ማረን ብለው ጮሁ፡፡ ጌታችንም ወደ ቤተ መቅደስ ሄደው ራሳቸውን ለካህናት እንዲያሳዩ ነገራቸው፡፡

ካህናት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንደምናያቸው የሰዎችን ኃጢአት የማስተሥረይ ሥልጣን የተሰጣቸው ናቸው፡፡ አሥሩም ሰዎች ወደ ካህናት ሄደው ራሳቸውን አሳዩ ከበሽታቸውም ተፈወሱ፡፡ ከአሥሩ ሰዎች ግን አንዱ ብቻ ጌታችንን ሊያመሰግን ተመልሶ መጣ ጌታችንም በዚህ ሰው ተደሰተ፡፡ በሌሎቹ በቀሩት አዝኖም ***ዘጠኙ የት ቀሩ?*** አለ፡፡ ብቻውን የመጣውንም ***ተነሣና ሂድ*** አለው፡፡

እኛም ማመስገን አለብን፡፡ የሚያመሰግን የተደረገለትን መልካም ነገር የማይረሳ ነው፡፡ መጽሐፍ ***"ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ፡፡"*** ኤፌ. ፭ ፥ ፳ እንዳለን በዛሬው ትምህርታችን ሁሌም ስለ ሁሉም ማመስገንንና የምሥጋናን ደረጃዎች እንማራለን፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

ሰውና መላእክት ለዘላለማዊ የማይቋረጥ ምስጋና ተፈጥረዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን የማያቋርጥ ምሥጋና የሚገኘውም ለዚህ ነው፡፡ እኛም እግዚአብሔርን፡-

## ሁልጊዜ ማመስገን አለብን፡-

*“ሁልጊዜ……አመስግኑ”* ኤፌ. ፭ ፥ ፳ እንደተባለ ለሰማያዊው አባታችን የምናቀርበው ምሥጋና በጊዜ ተገድቦ ወይም አንዳንዴ ብቻ መሆን የለበትም። ጠዋት ስንነሳ ፣ በቀን ውሎኣችን ፣ ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነትም ሆነ ማታ ስንተኛ፣ ስንመገብም ምሥጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። እርሱን ለማመስገን የሚያጥረን ጊዜ የለም፤ ዳዊት አገር እየመራ በቀን ሰባት ጊዜ ያመሰግን ነበር። “*ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ።* ” መዝ. ፻፲፰(፻፲፱) ፥ ፻፷፬። ነብዩ ዳንኤል በባቢሎን ቤተ መንግሥት ኃላፊነት እያለበት “*በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጕልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም* ” ዳን. ፮ ፥ ፲። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን አባት ለ፳፬ ሰዓታት የሚጸለይ ጸሎት አዘጋጅተው ይተጉ ነበር።

በዚህ መሠረትም በቤተ ክርስቲያን የተዘጋጁ የጸሎት ሰዓታት ሁሉ በምስጋና የሚጀመሩና የሚፈጸሙ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ከምንሳተፈው የምስጋና ሕይወት በተጨማሪ በግላችን የማያቋርጥ የምሥጋና ሕይወት ሊኖረን ይገባል። እግዚአብሔርንም ስላሳለፈልንና ስለሠጠን ስለ እያንዳንዷ ሰዓት እናመሰግነዋለን።

## ስለ ሁሉ ማመስገን

ከላይ ባየነው ጥቅስ *“በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።”* ተብለናልና ስለ ሁሉም እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።እርሱ ነገሮችን ሁሉ ለእኛ መልካም እንዲሆኑልን ካለው በጎ ፈቃድ የተነሳ ያደርግልናል *“እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን* ” ሮሜ. ፰ ፥ ፳፰ ለዚህ የማይቋረጥ በጎነቱ ምሥጋና ማቅረብ ይገባናል።

ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር፡- ጤና፣ ቤተሰብ፣ የመማር እድል፣ ሀገር፣ በጎ ጓደኞች፣ ቤተ ክርስቲያንና ካህናት፣ መጽሐፍ ቅዱስ…ሰጥቶናልና ለእነዚህ ሁሉ ልናመሰግነው ይገባናል።

ሰዎች ተሳስተው ሰይጣንም ሊጎዳን ፈልጎ ክፉ ነገር ቢደርስብን እንኳን ለእግዚአብሔር የምናቀርበውን ምሥጋና ማቋረጥ የለብንም። ምክንያቱም የደረሰብንን ነገሮች ጌታችን ስለሚያውቅ ለበጎ ይለውጠዋልና። ዮሴፍ ወንድሞቹ ካደረጉበት ክፉ ነገር በላይ የአምላኩ ቸርነትና የተማረው ትምህርት ይበልጣል።

www.zoorthodox.org

ላላየናቸውና ላላወቅናቸው ነገሮችም ምሥጋና ማቅረብ አለብን። ምክንያቱም ከእኛ በላይ አዋቂ የሆነው ጌታ ያደረገልንና የሚያረግልን ብዙ ነገሮች አሉና።

## ማጠቃለያ

በሰላምታ ልውውጣችንም ሆነ ስንተኛ እና ስንነሳ ማመስገን አለብን፡፡

ስለሁሉም ሊመሰገን የሚገባውን እግዚአብሔርን ሁሌም አመስግኑት ፡፡

## ተግባር፡-

ዛሬ ማታና ዘወትር ጠዋት ከእንቅልፋችሁ ስትነሡ ማታ ወደ መኝታችሁ ስትሄዱ ከመኝታችሁ በፊት ጸልዩ፡፡

ቅዳሴ፣ ማኅሌት፣ ቅኔ... ማለት ምን ማለት ነው? ጠይቃችሁ ኑና በክፍል ውስጥ አስረዱ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ትርጉም

## ሠላሳ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ።

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው።"*** ፩ኛ ጢሞ. ፫ ፥ ፲፭

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

## መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ይህ ስያሜ ተሰጣት? የዛሬው ትምህርታችን የቤተ ክርስቲያንን ትርጉም ማወቅ ይሆናል። አስቀድማችሁ የምታውቁትን ተወያዩ። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በሁለት መንገድ ይተረጎማል፡- አንደኛው ዘይቤያዊ ሲሆን ሁለተኛው ምሥጢራዊ ፍቺ ነው። እነዚህን በዛሬው ትምህርታችን እንመለከታቸዋለን።

## የሳምንቱ ትምህርት

በቀጥተኛ ትርጉም ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ቤተ እና ክርስቲያን ከሚሉት ሁለት የግዕዝ ቃላት የተገኘ ሲሆን የክርስቶስ ቤት ማለት ነው። ይህም የክርስቶስ ቤት፣ የክርስቲያኖች መሰባሰቢያ ቤት የሚል ትጉም አለው።

በግሪክ አቅሌስያ ትባላለች፤ የምርጦች ጉባኤ ማለት ነው። ይህች የምርጦች ጉባኤ የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩት ጉባዔ እስራኤልን ያመለክታል።

በምስጠራዊ ፍቺም ቤተ ክርስቲያን ስንል ሦስት ትርጉም አለው።

1. **ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል።**

www.zeorthodox.org

ተሰባስበን የምናስቀድስባት፣ የምንማርባትና ሌሎችን ምሥጢራት የምንፈጽምባት ናት። ይኽችን ቤት ጌታችን ኢየሱስ ቤቴ ስላላት የክርስቶስ ቤት እንላታለን። ***"ወደ መቅደስም ገብቶ በእርሱ የሚሸጡትን የሚገዙትንም ያወጣ ጀመር፤ እርሱም፡- ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው።"*** ሉቃ. ፲፱ ፥ ፯

በዘመነ ሐዲስ የማርቆስ እናት የማርያም ቤት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በዚያች ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው ይጸልዩ ነበር። ***"ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።"*** የሐዋ.፲፪ ፥ ፭

### 2. የክርስቲያኖችን ስብስብ ያመለክታል፡፡

ክርስቲያኖች ከሁለት ሰው ጀምረው በእውነተኛ ሃይማኖተ ክርስቶስ ጸንተው የሚኖራቸው ስብስብ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡ ምክንያቱም በዚያ የእምነት አንድነት ውስጥ እግዚአብሔር አለና፡፡ ***“ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።”*** ማቴ. ፲፰ ፥ ፳

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበደለንን መክረን አልሰማ ቢለን ***ለቤተ ክርስቲያን ንገራት*** ያለን ለዚህች የአባቶች ካህናት እና የምዕመናን ስብስብ ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ማቴ. ፲፰ ፥ ፲፯

ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን በተለይም በሐዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ ተጽፏል፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡ የሐዋ. ፲፩፥፳፪፣፲፫፥፩፣ሮሜ. ፲፮፥፩፣ ፩ኛ.ቆሮ. ፲፮፥፲፱፣ፊልሞ. ፩፥፪፣ ፩ኛ.ጴጥ. ፭፥፲፫

### 3. እያንዳንዱ ክርስቲያንም ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡

ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች፣ የክርስቶስ አካላት ናቸውና ቤተ መቅደስ ይባላሉ፡፡ ***“የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?”*** ፩ኛ.ቆሮ. ፫፥ ፲፮ እንዲሁም ***“ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፦ በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።”*** ፪ኛ ቆሮ. ፮ ፥ ፲፮ እንደተባለ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ማደሪያ ነንና ቤተ ክርስቲያን ተብለን እንጠራለን፡፡

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን በቀጥተኛና በዘይቤያዊ ትርጉም የክርስቲኖች ቤት ማለት ነው፡፡ ***“ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት ፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው።”*** ፩ኛ ጢሞ.፫፥ ፲፭

በምሥጢር እያንዳንዱ ክርስቲያን፣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ጉባዔ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡ ***“ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን ? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።”*** ፩ኛ.ቆሮ. ፮ ፥ ፲፱ - ፳

www.zoorthodox.org

## ተግባር

ወደ ቤታችሁ ተመልሳችሁ የተማራችሁትንና በተጨማሪ ምንባብነት የተሰጣችሁን ከልሱ፡፡

# የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት

## ሠላሳ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ባሕርያት ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-*"እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።"*** ኤፌ. ፭ ፥ ፳፯

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

### *መግቢያ*

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የቤተ ክርስቲያንን ትርጉም አይተናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ከዚያው በመቀጠል የቤተ ክርስቲያንን ባሕርያት እንማራለን፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
2. በምስጢራዊ ፍቺ ሦስቱ የቤተ ክርስቲያን ትርጉሞች ምን ምን ናቸው?

እያንዳንዱ ነገር መሠረታዊ ባሕርይ አለው፡፡ ለምሳሌ ሰው አራት ባሕርያተ ሥጋና ሦስት ባሕርያተ ነፍስ አሉት፡፡ ሌሎችም ነገሮች በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁ ራሳቸውን የሚገልጥ ባሕርያት አሉዋቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም የራስዋ ባሕርያት አሉዋት፤ እነዚያን መሠረታዊ ባሕርያት ካላሟለችም ቤተ ክርስቲያን አትባልም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት ምንድናቸው? የምታውቁትን ከመምህር ጋር ተነጋገሩ፡፡

www.zeorthodox.org

## የሳምንቱ ትምህርት

ቤተ ክርስቲያን አራት ባሕርያት ወይም መገለጫዎች አሉዋት፡፡ እነዚህንም ዘወትር በምትጸልዩት የሃማኖት ጸሎት ታገኙታላችሁ *"ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላእለ ኵሉ ጉባዔ ዘሐዋርያት - **ሐዋርያት በሰበሰብዋት ከሁሉም በላይ በምትሆን በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡"*** ዘርዝረን ስንመለከተውም የሚከተሉት አራት ትርጉሞች(ባሕርያት) አሉት፡-

## 3. ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፡፡

*"ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ....፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡"* ኤፌ. ፭ ፥ ፳፭ - ፳፯ ተብሎ እንደተጻፈ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፡፡ ለቤተ ክርስቲያን የኃጢአትና የክህደት ርኩሰት አይስማማትም፣ የለባትምም፡፡ በተጨማሪም በሚከተሉት ምክንያቶች ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፡-

ቤተ ክርስቲያን በጌታችን ክቡርና ቅዱስ ደም የተቀደሰች ስለሆነች ቅድስት ናት፤

ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ቀዳስያን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆነች ቅድስት ናት፤

ቤተ ክርስቲያን አምነው የመጡት ለቅድስና የሚበቁባት ስለሆነች ቅድስት ናት፤

በዚህ *መሠረት* በጌታችን የተቀደሰችው ቤተ ክርስቲያን፤ *መንፈስቅዱስን* ከተቀበለችበት በቅድስና የምትመራበትን ኃይል ካገኘችበት ከበዓለ ሃምሳ ዕለት አንስቶ በእምነት የሚቀርቡትን ሁሉ ስትቀድስ ትኖራለች፡፡ የሐዋ ፪ ፥ ፩ - ፬

## 4. ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፡፡

በተለያየ የዓለማችን ክፍል ያሉ አማንያንና አብያተ ክርስቲያናት፡- በእውነተኛው ትምህርት፣ አምልኮት እና ሃይማኖት እስካሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ፡፡ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚመሩ አንድ ቤተሰብም ናቸው፡፡ በወንጌል *"አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ።"* ዮሐ. ፲ ፥ ፲፮ እንደተባለውም የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አካላት ናቸው፡፡ በተለያየ ሀገርና ቦታ ያለችን ቤተ ክርስቲያን አንድ የሚያደርጋት፡-

- በመሠረተ እምነት አንድ መሆንዋ
- በምሥጢራት እና ክብራቸው ላይ ተመሳሳይ እምነት በመኖሩ
- በቅዱስ ቁርባን ባላቸው አምልኮትና እምነት መመሳሰል ሲችሉ... የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡
- ከዚህ በተጨማሪም በገጠርም ሆነ በከተማ ያለች ቤተ ክርስቲያን ክብር አንድ ነው፤ በወርቅም ትሰራ በሣር በመንፈስ ቅዱስ እስከከበረች አንዲት ናት፡፡

www.zeorthodox.org

- በአንዲት ጥምቀት ክርስትናን የተቀበሉም እንዲሁ በክርስቶስ አንድ ናቸው፡፡ *"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤"* ኤፌ. ፬ ፥ ፬፣ *"ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ"* ይሁ. ፩ ፥ ፫

## 5. ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት፡፡

ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊት የሚያሰኟት ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከጌታችን የተማሩትና በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠላቸውን የሐዋርያትን ትውፊት መጠበቅዋ፡፡
- የሐዋርያትን ሥልጣነ ክህነት መያዝዋ፡፡
- ሐዋርያዊ አገልግሎት መስጠትዋ (በስብከት ማሳመንዋ) ናቸው፡፡

እነዚህ የተገኙት ከጌታችን ነው፡፡ እርሱ በቃሉ በመናገርና በንፍሐት (እፍ በማለት) ክህነትን ሰጥቷቸዋል፡፡ ማቴ. ፲፮፥፲፮፣ ዮሐ. ፳፥፳፪-፳፫፡፡ ሲያርግም እስከ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን እንዲሰብኩ አዟቸዋል፡፡ የሐዋ. ፩፥፰ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሐዋርያዊ ማንነት ጠብቃ ኖራለች፡፡ ዛሬም ከጌታችን የተላለፈው ጽሑፋዊና ቃላዊ ትውፊት አለ፡፡ የክህነት ሥልጣኑም ተላልፎልን ካህናት አሉን፡፡ ሐዋርያዊ አገልግሎቱም በስብከትና በተግባራዊ ትምህርቶች ተጠብቆ ይፈጸማል፡፡

## 6. ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም በላይ (ዓለም አቀፋዊት) ናት፡፡

**ይህ ማለትም፡-**

ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም በላይ የሆነች ጉባዔ ናት፡፡ ይህች ጉባዔ በምድር ብቻ ያለች ሳትሆን በሰማይም ካለችዋ የቅዱሳን ጉባዔ ጋር አንድ (Universal) ናት፡፡ ***"ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።"*** ዕብ. ፲፪፥፳፪-፳፬፡፡ ለዚህ ነው ከቅዱሳን ጋር በጸሎት የምንነጋገረውና፤ በምልጃቸው እንጠቀማለን ብለንም የምናምነው፡፡

www.zeorthodox.org

በተጨማሪም ዓለም አቀፋዊት ናት ስንል በነገድ በቋንቋና በወገን ልዩነት የሌለባት የሁሉም ናት ማለታችን ነው፡፡ ***"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡"*** ገላ. ፫ ፥ ፳፰፡፡ ይህ በክርስቶስ የተገኘው የሰው ልጆች አንድነት በሰማይም ጸንቶ ይቀጥላል ***"ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና***

*በበጉ ፊት ቆሙ።"* ራእ. ፯ ፥ ፱። መላእክትም በዚህ ተደስተው እንዲህ ሲሉ አመስግነዋል፡- *"መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችንዎጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ፡፡"* ራእ. ፭ ፥ ፱ - ፲፡፡

## ማጠቃለያ

- ቤተ ክርስቲያን አራት ዋና ዋና ባሕርያት አሏት እነርሱም፡- ቅድስና፣ አንዲት መሆን፣ ሐዋርያዊትነትና፣ የሁሉም (ዓለም አቀፋዊት) መሆንዋ ነው። እነዚህን ባሕርያት ካላሟላች ቤተ ክርስቲያን አትባልም።
- ልጆች እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሁሉ ታሟላልናለችና እኛ ግን እግዚአ ብሔር ይህችን ታላቅ ሥጦታ እንድናገኝ አድሎናል።

## ተግባር

- በበዓላት የሚለበሰውን ነጭ ልብስ፣ የክህነት ሥርዓቱን፣ በሆሳዕና የሚያዘውን ዘንባባ፣ እንዲሁም በሀገራችንና በውጭ ያሉትንን አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ከተማራችሁት አንጻርና ከመምህራን ጠይቃችሁ ለምን እንደሚደረጉና እንዴት እንደሚደረጉ በመጻፍ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

www.zeorthodox.org

# በዓለ ጰራቅሊጦስ - የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን

## ዐርባኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበላቸውና በአንድ ልብ ስለ መሰብሰብ ጥቅም መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፤ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡፡"*** የሐዋ.ሥ. ፪ ፥ ፩

**ምንባብ፡-** የሐዋ.ሥራ 2

## መግቢያ

ጰንጠቆስጤ ፶ኛው ቀን ማለት ነው፡፡ ፻፳ው የክርስቶስ ቤተሰቦች (፲፪ቱ ሐዋርያት ፣ ፸፪ቱ አርድዕትና ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስት) እመቤታችን ባለችበት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ዕለት ጰንጠ ቆስጤ ይባላል፡፡ ለዕለቱ ይህ ስያሜ የተሰጠበት ምክንያትም ክርስቶስ በተነሣ በ፶ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ ነው፡፡ በዛሬው ትምህርታችን የጰንጠቆስጤ ቀንን ታሪክ እና የሐዋርያትን አገልግሎት አጀማመር እናያለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ክርስቶስ በተነሣ በ፶ኛው ቀን ባረገም በ10ኛው ቀን ደቀ መዛሙርቱ በማርቆስ እናት ቤት ተሰብስበው ነበር፡፡ እመቤታችንና ሌሎችም ከእነርሱ ጋር ነበሩ፡፡ ፻፳ ያህሉም በአንድ ልብ ይጸልዩ ነበር፡፡ በድንገትም እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ የመጣ ድምፅ የነበሩበትን ቤት ሞላው፡፡

በእያንዳንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት ለንቃ አምሳያ ወረዳባቸው፡፡ በተለያየ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፡፡ የአይሁድን በዓለ ፋሲካ ለማክበር የተሰበሰቡና ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ሰዎችም ነበሩ፤ ሐዋርያትም በየራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው ተደነቁ፡፡

www.zeorthodox.org

አንዳንዶቹ ግን የወይን ጠጅ ጠጥተዋል ብለው አጉረመረሙ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ከ፲፩ዱ ደቀ መዛሙርት ጋር ተነስቶ የተሰበሰቡትን አስተማረ፡፡ አሁን የሚያዩትና ከዚህ በፊት የተመለከቱት በሙሉ በነቢያት የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑንም አስረዳቸው፡፡ ከዳዊት መዝሙርም ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት የተተነበየውን ጠቅሶ አስተማረ፤ ምን እናድርግ ሲሉትም ***"ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም***

***ስጦታ ትቀበላላችሁ።"*** አላቸው። በዚህ ቀን ፴፻ (3000) ሕዝብ አምኖ ተጠመቀ።

ሁሉም በወንድማማችነት፣ በኅብረትና በጸሎት አንድ ልብ ሆነው መኖር ጀመሩ። ይህም ክርስቶስ ቀደም ሲል የነገራቸው ቃል ፍጻሜ ነበር። ***"ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉኣቸዋል ፣ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ።"*** ማር. ፲፮ ፥ ፲፯ - ፲፰። ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ፣ ወንጌልን ሰበኩ፣ ስለ ክርስቶስም መሠከሩ።

ዓለም አልተገባቸውምና - ታሠሩ፣ አፌዙባቸው፣ ተገረፉ፤ እነርሱ ግን በስሙ መከራ በመቀበላቸው ደስተኞች ነበሩ። እስከ ሞትም ታምነው መሰከሩለት።

## ማጠቃለያ

ጌታችን ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ *‹‹እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።››* ሉቃ. ፳፬፥፵፱ እና *"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ እና በመንፈስቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጉዋቸው።››* ማቴ.፳፰፥፲፱-፳ ጠቃሚ ትእዛዞችን ስጥቶአቸዋል፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳዘዛቸው ደቀ መዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ቆዩ። የተሰበሰቡት በአንድ ቤት ሲሆን በአንድ ልብ ሆነው እየጸለዩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ተስፋ ይጠባበቁ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ጌታ ባረገ በ፲ኛው ቀን ተላከላቸው። በአንድ ቤት ተሰብስበውም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ በተለያየ ቋንቋ መናገርም ጀመሩ፤ ይህም ሰው የሚናገረው ቋንቋ - ልሳን ይባላል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ምሥክሩ እንደሚሆኑ ነግሮአቸው ነበር። የተሰጣቸውን ተስፋ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልና ጸጋ ከተቀበሉ በኋላ ሐዋርያት አገልግሎታቸውን በኢየሩሳሌም ጀመሩ በመጀመሪያው ቀንም ፴፻ (3000) ሕዝብ አጠመቁ። ጌታችን እንደነገራቸውም ታላላቅ ተአምራትና ድንቆች ይከተሉአቸው ነበር።

## ተግባር

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንዲፈጽምልን ታዛዦች እንሁን፤ በቤተሰብ እና በቤተ ክርስቲያን አንድ ልብ እንሁን።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጰንጠቆስጤ ምን ማለት ነው? በዚያን ጊዜ ምን ተከሰተ? ሐዋርያት ከጌታችን ዕርገት በኋላ የት ተሰበሰቡ? ስንትስ ነበሩ?
2. ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ጌታችን ካረገ ከስንት ቀናት በኋላ ነው? ያመኑበትን ምን ዓይነት ምልክቶች ተከተሏቸው?

# ዘመነ ሐዋርያት

## ዐርባ አንደኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ ዘመነ ሐዋርያት መንፈሳዊ ታሪክ መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨምሩለት ነበር፡፡"*** የሐዋ. ፭ ፥ ፲፬

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፩ እስከ ምዕራፍ ፲፪፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ዘመነ ሐዋርያት የምንለው ዘመን ከ፴፫ ዓ.ም. እስከ ፻ ዓ.ም. ድረስ ያለውን ዘመን ነው፡፡

### *በዚህ ዘመን የነበረው ዓለም*

በዚህ ዘመን ጌታችን ዓለምን ያዳነባትና ሐዋርያት ያስተማሩባት ሀገር - እስራኤል፤ በሮም ቅኝ ግዛት ሥር ነበረች፡፡ በምድረ እስራኤል የነበሩት አይሁድም በተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር፡፡

ቅኝ ገዥዎቹ ሮማውያንም ግዛታቸው ሰፍቶባቸው ለመቆጣጠር የተቸገሩበት ወቅት ነበር፤ የሚያመልኩትም በእጆቻቸው የተሰሩትን ጣዖታትን ሲሆን፤ የተሳሳቱ የግሪክ ፍልስፍናዎች በየጎዳናዎቹ ሲነገሩ ይውሉ ነበር፡፡

በዚህ ዘመን ጌታችን ተወልዶ ለዓለም ሕይወትን ሰጠ፤ በቅዱስ ቃሉና በኑሮ ዓለምን እንዲያጣፍጡት ሐዋርያትን ላካቸው፡፡ እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ዞረው አገለገሉ፡፡

ሆኖም ዓለሙ በጎውን መምረጥና ሐዋርያትን መቀበል አልቻለም፡፡ ብዙ መከራዎችን በማድረስም ተቃወማቸው፡፡ የመጀመሪያው ተቃዉሞ ከአይሁድ ነበር፤ ቢሆንም ይህንንም ፈተና ክርስትና በሰማዕትነት፣ በፍቅርና በተአምራት ድል አድርጎታል፡፡

www.zeorthodox.org

### ሐዋርያዊ አገልግሎት

የእግዚአብሔር መንፈስ በሐዋርያት ይሠራ ነበርና የአማኞች ቁጥር በየቀኑ ይጨምር ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ብቻ ከሦስት እስከ አምስት ሺህ ደረሰ፡፡ ***"ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፡፡ የወንዶችም ቁጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ፡፡"*** የሐዋ.ሥ. ፬ ፥ ፬፡፡

በሚፈጸሙት ተአምራት እና በፍቅርና በጽድቅ በተሞላው የክርስቲያኖች ሕይወት ምክንያት፡- *"ሕዝቡ ግን ያከብሩዋቸው ነበር። የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር።"* የሐዋ. ፭ ፥ ፲፬፣ የሐዋ. ፮ እና ፯፤ *‹‹እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።›* የሐዋ. ፪፥፵፯ በዚህ ምክንያትም አይሁድ በክርስቲያኖች ላይ በቅናት ተነሡ። እያሠሩ በመግረፍ፣ በድንጋይ ወግረው በመግደል፣ በሮማውያን ፍርድ ፊት በማስቆም ሞት እያስፈረዱባቸው በማስገደል በበብዙ መከራ አሳደዱአቸው። ቅዱስ ጳውሎስም አይሁድ በክርስቲያኖች ላይ ያደረሱትን መከራ *‹‹እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፥ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፥ ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፥ ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቍጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል።››* ፩ ተሰ ፪፥፲፭-፲፮። ሲል ገልጾታል።

ይህ እየሆነም መከራው ብዙ ፍሬዎች ነበሩት:- በቅዱስ እስጢፋኖስ መገድል በኢየሩሳሌም የነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን ስትሰደድ ክርስቲያኖች በተለያዩ ከተሞች የእግዚአብሔርን ቃል አደረሱ። *‹‹የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።››* የሐዋ. ፰፥፬። እናም መከራው ወንጌል በተለያዩ ከተሞች እንዲዳረስና ክርስትና ከጥንካሬ ጋር እንዲስፋፋ አደረገ ። ከእነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

***የሰማርያው ስብከተ ወንጌል***:-

በመጀመሪያ ወንጌልን በሰማርያ ከተሞች የሰበከው የቅዱስ እስጢፋኖስ ወዳጅ የነበረውና ከሰባቱ ዲቆናት አንዱ የሆነው ፊልጶስ ነው። *‹‹ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ። ርኵሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።››* የሐዋ. ፰ ፥ ፭ - ፰

www.zeorthodox.org

ፊልጶስን ተከትሎም ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ዮሐንስ በሰማርያ አስተማሩ። *‹‹እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ።››* የሐዋ ፰፥፲፭-፲፯፣ *‹‹እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ በሳምራውያን በብዙ መንደሮችም ወንጌልን ሰበኩ።››* የሐዋ ፰ ፥ ፳፭።

የመጀመሪያው እስራኤላዊ ያልሆነ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ያመነውም በዚህ ዘመን ነበር። የሐዋ.ሥ. ፰ ፥ ፳፮ - ፵።

***በባሕር ዳርቻዎች ባሉ ከተሞችና በገሊላም ክርስቶስ ተሰበከ:- ‹‹ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና። ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኙ፥ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተማዎች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።››*** የሐዋ.ሥ ፰ ፥ ፴፱ - ፵። ***‹‹በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።››*** የሐዋ ፱ ፥ ፴፩።

ቅዱስ ጳውሎስም በ37 ዓ.ም ክርስቲያን ሆነ። የሐዋ ፱ ፥ ፩ - ፲።

www.zeorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን የሆነው የጣዖት ቤት

## ዐርባ ሁለተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ምክንያት በማድረግ ከዘመናዊ ጣዖት መጠበቅን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ሌሎች አማልክት አይሁንላችሁ፡፡"*** ዘጸ. ፳ ፥ ፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ድርሳነ ሚካኤል

## መግቢያ

ሰኔ 12 የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል መከበር የጀመረው በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግብፅ ነበር፡፡ ክሊዮፓትራ በተባለች ንግሥት በተገነባ ቤተ ጣዖት ከዘመናት በፊት ሰኔ ፲፪ የሚከበር በዓል ነበር፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ይህ ቤተ ጣዖት እንዴት እንደተሠራና ከዚያም እንዴት ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለውጦ የቅዱስ ሚካኤል በዓል መከበር እንደጀመረ እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ንግሥት ክሊዮፓትራ በገነባችው ቤተ ጣዖት የእስክንድርያ ሰዎች ዙሐል የተባለ ጣዖት ያመልኩ ነበር፡፡ በየዓመቱም የእንስሳት መስዋዕት እያቀረቡ ያከብሩት ነበር፡፡ በ፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እለእስክንድሮስ የተባለ ሊቀጳጳስ ተነስቶ እነዚህኑ ጣዖት አምላኪዎች ወንጌል ሰበካቸው ጣዖቱ ዙሐል የማይሠማ፣ የማይናገር፣ምንም ማድረግ የማይችል በእነርሱ እጅ የተሠራ መሆኑን ነገራቸው፡፡ በነቢያትም የተነገረው ትንቢት በጌታችን መፈጸሙን ሰበከላቸው፡፡

ከዚያም በሮማው ንጉስ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን እለእስክንድሮስ የአሌክሳንደርያ (ግብፅ) ፓትሪያርክ ሆኖ ተሾመ፡፡ ከቆስጠንጢኖስ በፊት ያለው ዘመን የክርስትና የስደትና መከራ ዘመን ነበር፡፡ *ክርስቶስ ለስሙ ሲመሰክሩ በስሙ ምን መከራ እንደሚያገኛው የነገራቸውን ታስታውሳላችሁ?*

ታላቁ ንጉሥ ቆሰጠንጢኖስ ግን ለክርስቶያኖች ነፃነትን አወጀላቸው፡፡ በዚሁ ዓመትም እለእስክንድሮስ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ፡፡ እለእስክንድሮስ ፓትሪያርክ ከሆነ በኋላም የዙሐልን ቤተ ጣዖት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ቀደሰው የጣዖት ምስሎችንም አጠፋቸው፡፡ ጣዖት አምላኪዎችንም ክርስቲያን አደረጋቸው፡፡

www.zeorthodox.org

ለጣዖት በመሠዋት ፋንታም እግዚአብሔርን እንደያመልኩና ድሆችን እንዲረዱ አደረገ፡፡ ቀኑም የቅዱስ ሚካኤል ቀን ሆኖ ተከበረ፡፡ከዚያም በኋላ ሰኔ ፲፪ን ቅዱስ ሚካኤልን እያሰቡና ድሆችን እየረዱ እግዚአብሔርን የሚያከብሩበት በዓል ሆነ፡፡

## ማጠቃለያ

- ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በፊት ጣዖት አምልኮ በዓለም ላይ ተንሠራፍቶ ነበር፡፡ አሁንም እንደበፊቱም ባይሆን ጣዖት አምላኪዎች አሉ፡፡ ጥቅመኛነትና ግላዊነትም የዘመናችን ጣዖታት ናቸው፡፡
- እለእስክንድሮስ የዙሐል ቤተ እምነትን የጣዖት አምልኮ በአምልኮተ እግዚአብሔር ቀይሮታል፡፡ የታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን የክርስቲያኖችን መከራ አስቀርቶታል፡፡ ቤተ ጣዖታቱም ተዘግተዋል፡፡
- ሰኔ ፲፪ ቀን የምናከብረው ቤተ ክርስቲያን ጣዖተ አምልኮ ላይ ያገኘችውን ድል ነው፡፡

## ተግባር

- የምታከብሩትን በዓላት መንፈሳዊ ምክንያት ጠይቁ፡፡ ስለ ቆስጠንጢኖስ እናትም የምታዉቅትን ተወያዩ፡፡

### *ጥያቄዎች*

1. የዙሐል ቤተ ጣዖት ለምንና በማን ተገነባ?
2. የዙሐልን ቤተ ጣዖት ወደ ቤተ ክርስቲያንነት የቀየረው ማነው? ሕዝቡንስ ማን አጠመቃቸው?
3. የክርስቲያኖችን ስደት ያስቆመው የሮም ንጉሥ ማነው?
4. የዘመናችን ጣዖት አምልኮ ምን ይመስላል?
5. የምታከብሩት ብሎም እጅግ የምትወዱት ቅዱስ ማነው? ለምን?
6. በንግሥት እሌኒና በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ መካከል ያለው ዝምድና ምንድነው?

www.zeorthodox.org

# ሃይማኖት (መግቢያ)

## ዐርባ ሦስተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ስለ ሃይማኖት ምንነት በቅዱሳት መጻሕፍት ተመሥርተን ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹ዓለሞች በእግዚኣብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን፡፡››* ዕብ. ፲፩ ፥ ፫፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፡፡

## መግቢያ

የእግዚአብሔር እና የፍጥረቱ ግንኙነት ሃይማኖት ይባላል፡፡ ሃይማኖት እግዚአብሔር በመገለጡ የተጀመረ ሲሆን የሰው ልጆች በመጠበቅ ተስፋ እና ኃይል የሚሰጣቸውን እግዚአብሔርን ያገኙበታል፡፡ በዛሬው ትምህርታችን ስለ ሃይማኖት ምንነት እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### ሀ. ሃይማኖት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመገለጡ የተገኘ ነው፡፡

እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ለሰው ልጆች ተገልጧል፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ዋነኖቹ ናቸው ፡-

1. በፍጥረቱ፡-

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ካለመኖር ወደ መኖር በማምጣቱ ተገልጦል፡፡ ዘፍጥ. ፩፥፩-፳፰ *‹‹ዓለሞች በእግዚኣብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፤ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን፡፡››* ዕብ. ፩፥፫፡፡ ከዚያም ራሱን በመግለጥ አስገኛቸው እርሱ መሆኑን አሳውቋቸዋል፡፡ ዘፍጥ. ፩፥፳፱ - ፪፥፳፫

2. ሕግ እና ተስፋ በመስጠት

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት የሚተዳደርበትን፤ ክፉና ደግን የሚለይበትን እና በተፈጠረበት ዓላማ ለመኖር የሚያስችለውን **የተፈጥሮ እና ትዕዛዛዊ ሕጎችን** (ሕግ ጠባይዓዊ ሕግ መጽሐፋዊ) በመስጠት የርሱን ፈጣሪነት የእኛን ፍጥረትነት፣ የእርሱን አምላክነት የእኛን ተገዥነት፣ የእርሱን አባትነት የእኛን ልጅነት እንድናውቅ አድርጎናል፡፡

www.zeorthodox.org

የመጀመሪያው ትእዛዝም *‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካሙን እና ክፉን ለሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፡፡››* ዘፍ. ፪፥፲፯፡፡ ከዚያም ለኖኅ ለአብርሃም… ምስጢሩን እየገለጠ አባታዊ ትእዛዛትን ሲሰጣቸው እና እነርሱም ሲጠብቁት ኖረዋል፡፡ በመጨረሻም ለሙሴ ተገልጦ ፲ቱ ትእዛዛትን እና የቤተመቅደሱን ሕግ ሰጥቷቸዋል፡፡

የሰው ልጆች ሲሳሳቱም አባታችን እና አምላካችን እግዚአብሔር እንደወጡ ይቅሩ፤ በዘላለማዊው ሞት ይጥፉ ሳይል የማዳን ተስፋን በመስጠት ለደጋግ አባቶች እየተገለጠ ሃይማኖትን ያጸናላቸው ነበር፡፡ ዘፍ.፫፥፲፭፤ ፲፪፥፫፡፡ እነርሱም ተስፋ የሰጣቸው የታመነ መሆኑን በማወቅ አምነው ተስፋ በማድረግ ኖረዋል፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች በሚገባ አንብቡ፡- ገላ. ፫፥፮፡፳፱፣ ዕብ. ፲፩፥፫፣ ፩ኛ.ጴጥ. ፩፥፲-፲፪፡፡ በዚህ መሠረትም እግዚአብሔር በብዙ መንገድ በመገለጥ ተስፋ እየደለ ሃይማኖትን ለሰው ልጆች ሰጥቶል፡፡

### 3. በራዕይ ፣ በሕልም እና በብዙ ምሳሌዎች በመገለጥ፡-

እግዚአብሔር በባሕርይው ረቂቅ ስለሆነ በዐይን አይታይም አይዳሰስም፡፡ የሚገለጥላቸው፡- የሰው ልጆች በሚረዱት መንገድ እንደ ሰው፣ ድምጹን እያሰማ በማናገር ነበር፡፡ ለምሳሌ ለአብርሃም ድምጹን ሲያሰማው፣ ለሙሴ በዕፀ ጳጦስ (ከእሳት ነበልባል ጋር በተዋሐደች ቅጠል)፤ ለነቢዩ ኢሳይያስ በዙፋን በተቀመጠ ንጉሥ፣ ለዳንኤል በዘመናት በሸመገለ አባት… ተገልጦላቸው ነበር፡፡

### 4. በሥጋ ተገልጦ፡-

ለዘመናት ከላይ በገለጥናቸው መንገዶች ሲገለጥ የኖረው እግዚኣብሔር የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ አንድያ ልጁን ልኮ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በመዋሐድ ተወልዶ በሥጋ ተገለጠ፤ በመካከላችን ተመላልሶ በማስተማር ቤተ ክርስቲያንን መሠረተልን፣ ሕግም ሠራልን ሃያማኖትን እና በሃይማኖት መኖርን አስተማረን፡፡ *‹‹ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤››* ዕብ. ፩፥፩-፫፤ ሃይማኖት በእግዚአብሔር መገለጥ የተገኘ ነው፡፡

www.zeorthodox.org

### ለ. ሃይማኖት ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት መንገድ ነው፡፡

የሰው ልጆች ምንም በጎ ቢሠሩ እና በእውቀት ቢያድጉ ሃይማኖት ከሌላቸው እግዚአብሔርን አያገኙትም፥ ምክንያቱም ሃይማኖት ከሌለ እግዚአብሔር ደስ አይሰኝብንም (ያዝንብናልና)፤ ለልባችን እንዲረዳን ሆኖ አይገለጥልንም፡፡ ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ *‹‹ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ፡፡››* ዕብ. ፲፩፥፮ ያለው፡፡ ትክክለኛውን የሃይማኖት መንገድ የሚያገኟዋት እና የሚሄዱባትም ጥቂቶች ናቸው፡፡

የእውነት ሃይማኖትን መንገድ መሳትም መጨረሻው ጥፋት ነው፡፡ ‹‹*በጠበበው ደጅ ግቡ፣ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና፤ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፡፡ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና፤ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡፡*›› ማቴ. ፯ ፥ ፲፫ - ፲፬፡፡

ነቢዩ ኤርምያስ ይህችን መንገድ የቀደመቸው መንገድ ሲላት በዚህች መንገድ ላይ ጠይቀን እንድንሄድ እግዚአብሔር ማዘዙን በትንቢቱ ጽፎልናል፤ ለመሄድ ያልቻሉትንና እንቢተኝነታቸውንም ገልጦልናል፡፡ ‹‹*እግዚኣብሔር እንዲህ ይላል፡- በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርስዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ፡፡*›› ኤር. ፮ ፥ ፲፮፡፡

ወደ ሕይወት ምንጭ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ የሚመስሉ ፍጻሜያቸው ግን ሞት ከሆኑ መንገዶች እንድንጠበቅ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ‹‹*ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው፡፡*›› ምሳ. ፲፬ ፥ ፲፪፡፡

### ሐ. ሃይማኖት አንዲት ናት

ከአንዱ ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝባት ሃይማኖት አንዲት ናት፤ የተርሴሱ ሐዋርያ ‹‹*አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፡፡*›› ኤፌ. ፬፥፭ ሲል ያስተምረናል፡፡

የተሰጠችውም ከአንዱ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ብዙ ሃይማኖቶችን አልሰጠም፡፡ ከላይ እንዳየነው ለብዙ አባቶች የገለጠው አንዲትዋን ሃይማኖት የሚያጸኑ ትምህርቶች እና ቃል ኪዳን ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ለተገለጡትም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻፍ በኂላ ለተነሱት ቅዱሳን የተገለጠችው እና ያስተማሯት ሃይማኖት አንዲት ናት፡፡ መጽሐፍም ‹‹*ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት*›› ይሁ. ፫፡፡ ሲል ይህንኑ ትምህርት ያጸናልናል፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

- ፍጥረቱ ባዝኖ እንዳይቀር እግዚአብሔር በመገለጡ ሃይማኖትን ሰጠን፡፡ ክርስትናም የእግዚአብሔር መገለጥ የመጨረሻው እና ከፍተኛው ደረጃ ነው፡፡
- ሃይማኖት እግዚአብሔር እና ሰው የሚገናኙበት መንገድ እንደመሆኑ ይህን መንገድ ማጽናት አለብን፡፡ ይህች መንገድ አንዲት ናት፤ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሃይማኖቶች አሉ አላለንምም፡፡

## ተግባር

ስለ እግዚአብሔር መገለጥና ስለ አንዲቱ ሃይማኖት ተወያዩ፡፡

# ሃይማኖት (ሁለት)

## ዐርባ አራተኛ ሳምንት

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩኣችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮኣቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤››* ዕብ. ፲፫ ፥ ፯፡፡

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በዛሬው ትምህርታችን ስለ ሃይማኖት መጠበቂያ እና መተላለፊያ መንገዶች መማር መሠረታዊው ዓላማችን ነው፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን፡፡

### መግቢያ

ዛሬ በሃይማኖታችን ስላሉ ሦስት ነገሮች (ዶግማ ቀኖና እና ትውፊት) እንማራለን፡፡ እነዚህ ሦስቱ የሃይማኖታችን መሠረቶች ሲሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ሃይማኖት የሚጠበቅባቸው፣ የተመሠረተባቸው፣ የሚገለጥባቸው፣ የምናምነውን የምናውቅባቸው እና የሚተላለፍባቸው ናቸው፡፡ ሦስቱንም በሚገባ የተረዳ ሰው ሃይማኖቱን ያውቃል፡፡ እንዴት መኖር እንዳለበትም ይረዳል፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

*ዶግማ፡-* መሠረተ እምነት ማለት ሲሆን፤ የማይሻር እና የማይለወጥ ነው፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ላይ ያለን የማይለወጥ እምነት እና ትምህርት ነው፡፡ ይህን መሻርም ሆነ ማጉደል ክህደት እና ስህተት ነው፡፡ አምስቱ አዕማደ ምስጢራት፣ መጽሐፍቅዱስ፤... የመሳሰሉት ዶግማዎች ናቸው ፡፡

www.zeorthodox.org

ቀኖና፡- የግሪክ ቃል ሲሆን መለኪያ ማለት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ሥርዓት ያመለክታል፡፡‹ *‹ይህም የዘላለም ሥርዓት ይሁንላችሁ፤››* ዘሌዋ. ፲፮ ፥ ፳፱ ብሎ እግዚአብሔር የሰጠን ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ *‹‹ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን፡፡››* ፩ኛ.ቆሮ. ፲፬ ፥ ፵ እንዳለ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ ተመሥርተው የተሠሩ በቅዱሳን ሐዋርያት እና በተከታዮቻቸው አበው ጳጳሳት የተደነገጉት፤ እነኚህ ውሳኔዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስለተሰሩ እንደ እግዚአብሔር ቃል እናከበረዋለን፡፡ የሐዋ. ፲፭ ፥ ፮ - ፳፱፡፡

በተለያዩ ዘመናት በተነሡ ክርክሮች እና ውዝግቦች ምክንያትም ሥርዓታት ተሠርተው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሆነዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት ባስረዳበት ክፍል ሥርዓተ ቁርባን እንዴት መፈጸም እንዳለበት ካስተማረ በኋላ ***‹‹የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።››*** ፩ኛ ቆሮ. ፲፩ ፥ ፴፪ ብሎ ነበር። የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥር የተወሰኑባቸው ጉባኤያትም ተመሳሳይ ምክንያት ነበራቸው።

ሥርዓት (ቀኖና) እንዴት መኖር እና እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለብን እንዲሁም የሁሉንም ልክ ይደነግጋል። የጾም ወቅቶች፣ የበዓላት ቀናት… ለምሳሌ ይጠቀሳሉ።

**ትውፊት፡-** ቅብብል ማለት ነው። ከአባቶች ወደ ልጆች የተደረገ ሃይማኖታዊ ሽግግርን ያመለክታል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ቀጥሎ ስለክርስትና የሚነግረንና ከቅዱሳን ሐዋርያት እና ከአባቶቻችን የተቀበልነው ትምህርት ነው።

እነኚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፉ ነገር ግን ፈጽሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያልወጡ አባቶቻችን ከእግዚአብሔር የተቀበሏቸው በእግዚአብሔር የተወደዱላቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች ናቸው።

ይህን የማይቀበሉ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ከተመሰከረላቸው አባቶች የተቀበለችውን እንደ ሐዋርያት ታሪክ እና ትምህርት ብሎም የጥንታውያን ሲኖዶሶች ውሳኔዎችንም አጥተዋል።

ትውፊት መጽሕፍ ቅዱስ ከመጻፉ በፊት ሃይማኖት የተላለፈበት መንገድ ነው።***‹‹አቤልም ደግሞ ከበጎቹ በኩራት እና ከስቡ አቀረበ።››*** ዘፍ. ፬፥፬ የተባለለት እና አባቶቻችን ኖኅ፣ አብርሃም፣ይስሐቅ እና ያዕቆብ ዘፍ. ፰፥፳፣ ፲፪፥፯ በእግዚአብሔር የተወደደላቸውን መሥዋዕት ያቀረቡት በጹሁፍ ተምረውት ሳይሆን ከአባቶቻቸው አይተውት ነበር። ትውፊትን እንድንቀበል መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል። ***"እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።"*** ፪ኛ ተሰ. ፪ ፥ ፲፭ ይዘው የተገኙትም ተመስግነዋል። ***"ወንድሞች ሆይ በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ።"*** ፩ኛ ቆሮ. ፲፩ ፥ ፪።

www.zeorthodox.org

ከዚህ ከወጡት መለየት ይገባናል። ***"ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።"*** ፪ኛ ተሰ. ፫ ፥ ፲፮።

**ቁሳዊ፣** መጽሐፋዊ እና ተግባራዊ ትውፊቶች አሉ።

**ቁሳዊ** የምንላቸው የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ ሆነው ለእኛ የተላለፉንን ያመለክታል። ይህም አልባሳት፣ መቋሚያ፣ እና እኒህን የመሳሰሉ… ናቸው።

**መጽሐፋዊ** የምንላቸውም በመጽሐፍ ተጽፈው ለእና የተላለፉልን ትምህርቶች ናቸው፡፡

**ተግባራዊዎቹ** ትውፊቶች አባቶቻችን እና እናቶቻችን ሲያደርጉ እያየን የምንፈጽማቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች ሲሆኑ አለባባስ፣ የጽዋ ማኅበራት ሥርዓቶች፣ የቤተ ክርስቲያን አመጣጥና አሳሳም የማማተብ ሥርዓት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ዶግማ እግዚአብሔርን ምን ብለን እንደምናምነውና ከሌሎቹ ጋር ያለንን የእምነት ልዩነት አውቀን ከስህተት የምንጠበቅበት ሲሆን፤ ቀኖና እንደ ክርስቲያን እና የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል እና አካል ሆነን በማኅበር ስንሳተፍ የምንፈጽመው ሥርዓት የምንኖረው ሥርዓት ነው፡፡

ትውፊትም ከኣባቶቻችን የወረስነው መልካም ኑሮ ንጹሕ አምልኮት እና የቀና ትምህርት ነው፡፡

## ተግባር

***‹‹ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፤መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡››*** ፪ኛ. ጢሞ. ፫ ፥ ፲፭፡፡ ሃይማኖታችንን በሚገባ እንወቅ፡፡

ከቤተሰቦቻችን ጋር በመሆን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ እና መንፈሳዊ ተግባራት ላይ እንገኝ የየነውን መፈጸም እንጀምር፡፡ ***‹‹የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩኣችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮኣቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፡፡››*** ዕብ. ፲፫ ፥ ፯፡፡

www.zeorthodox.org

# ስለ እግዚአብሔር ኅልውና የሚያስረዱን

## ዐርባ አምስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ**፡- የእግዚአብሔርን ኅልውና የሚያስረዱንን መግለጽ፡፡

**የሚጠና ጠቅስ** *"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሯል፥"* ዕብ. ፩ ፥ ፩፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት**- ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን፣ ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት መጽሐፍ ከሊቀ ጉባኤ አባ አበራ

### መግቢያ

ባለፈው ትምህርታችን ስለ ሃያማኖትን ስንማር ዶግማ ቀኖና እና ትውፊትን አንስተን፤ ዶግማ ስለ እግዚአብሔር ያለን ትክክለኛ እምነት ምንድነው የሚለውን እንደሚያሳውቀን ተምረናል፡፡ በዛሬው ትምህርታችንም ስለ እግዚአብሔር ኅልውና እንማራለን፡፡

### *የክለሳ ጥያቄዎች*

1. ዶግማ ቀኖና እና ትውፊት ማለት ምን ማለት እንደሆኑ? አስረዱ፡፡
2. ስለ ትውፊት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡትን አስረዱ፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

ኅልዎተ እግዚአብሔር ስንል የእግዚአብሔር መኖር ማለታችን ነው፡፡ *"ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡"* ዕብ. ፲፩ ፥ ፮፡፡

www.zeorthodox.org

እግዚአብሔር ራሱን በብዙ መንገድ ገልጧል፡፡ የምናመልከው እና የምንከተለው በዚሁ ጎዳና ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መኖር ከሚያስረዱን የሚከተሉትን በዋናነት እንመልከት፡-

### 1. ፍጥረት

የምንማርባቸው ደብተሮች፤ የተቀመጥንበት ወንበር ሠሪ እንዳላቸው እናስተውላለን፡፡ ፍጥረታትም አስገኚያቸውን እግዚአብሔርን ያመለክታሉ፡፡ *"ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም*

*የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።"* ዕብ. ፲፩ ፥ ፫

ለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት *"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፥ ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።"* መዝ. ፲፰ (፲፱) ፥ ፩-፪ ሲል ፍጥረታት ስለ እግዚአብሔር እንደሚመሰክሩ የገለጠው።

የማያስፈልግ አካል አለመኖሩና አንዱ ለሌላው የግድ አስፈላጊ መሆኑን ብሎም ምክንያት የሌለው ፍጥረት የሌለ መሆኑን በማስታወስ የፍጥረትን ድንቅ ነገር እንድናስተውል ቅዱስ ጳውሎስ *"የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያል።"* ሮሜ. ፩ ፥ ፳። ብሎናል።

2. የልቦና ሕግ (የኅሊና ምስክርነት)።

በየትኛውም ዓለም ያለ ሰው ከእንስሳት ተለይቶ ሲሳሳት የሚወቅሰው መልካም ሲያደርግም የሚያስደስተው ስሜት አለው። የዚህ ዓይነቱን እውቀት ሕገ ልቦና (የኅሊና ምስክርነት) እንለዋለን። ሰዎች በዚህ ሕግ ተመርተው ፈጣሪያቸውን ማወቅ እና ማስደሰት ይችላሉ።

ዳግመኛም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተጠቅመው በእውነት ያወቁትን ቅዱሳን ብለን እናከብራ ቸዋለን። አባታችን አብርሃም ከጣዖት አምልኮ ወጥቶ የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለው በዚህ ፍለጋው ነው። እግዚአብሔርን ያገኙ መስሎቸው በብዙ መንገድ የተሳሳቱንም ታሪክ እና መጽሐፍ ቅዱስ ይነግሩናል። የሐዋ. ፲፬ ፥ ፰ - ፲፰።

ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ *"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።"* ሮሜ. ፪ ፥ ፲፬ - ፲፭።

3. ቅዱሳት መጻሕፍት።

እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድናውቅ የሰጠን ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለ እርሱ ይነግሩናል።

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

- እግዚአብሔርን በፍጥረቱ፣ በሕገ ልቦና እና በመጽሐፍ ቅዱስ ሊታወቅ ይችላል።

## ተግባር

- ስለ ኅልውናው እንድታውቁ እግዚአብሔርን ያስታወሳችሁን ነገር ለቤተሰብ አስረዱ።
- በማመን ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ዋጋ እናገኛለንና ዘወትር በቤተ ክርስቲያን በማመን ቁሙ።

# የእግዚአብሔር ባሕርይ

## አርባ ስድስተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** በእውነተኛይቱ ቤተክርስትያን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርታ የምታስተምረውን ባሕርየ እግዚአብሔርን መማር።

**የሚጠና ጥቅስ፡-** *‹‹የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤››* ሮሜ፡ ፩ ፥ ፲፱ - ፳።

**ተጨማሪ ምንባባት-** ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን

### መግቢያ

ኀልዎተ እግዚአብሔርን ስንማር እግዚአብሔር በብዙ እንደተገለጠ ተምረናል። በዛሬው ትምህርታችንም እግዚአብሔር በሰው ዕውቀት የማይመረመር መሆኑን በመመልከት ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ እንማራለን።

እንዲሁም *‹‹መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።››* ፩ኛ ቆሮ ፪ ፥ ፲ እንዳለ ይህ መንፈሳዊ ተሰጥዖ የተሰጣቸው አባቶቻችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ያስተማሩንን በዛሬው ትምህርታችን እናያለን፤ እግዚአብሔር እርሱን የምናውቅበትን ጥበብ በመንፈሱ ገልጦልናልና።

### ትምህርቱ

www.zeorthodox.org

#### ባሕርየ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ምሉዕ በኩለሄ (Omnipresence)፤ ሁሉን አዋቂ (Omniscience) እና ሁሉን ቻይ (Omnipotent) ነው::

#### ባህርይው በፍጥረታት የማይመረመረው አምላክ

በፍጥረቱ ለፍጥረቱ በቸርነቱ የሚገለጠው እግዚአብሔር ከማንኛውም ሌላ ሁናቴ የተለየና የላቀ በመሆኑ የእርሱን ባሕርይ በማንም ምሳሌ ለመገለጽ አይቻልም። ኢሳ. ፵ ፥ ፲፰። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚገልጡት መገለጫዎቹ በጥቂቱ ለመግለጥ ያህል፡-

### 1. በሁሉ ምሉዕ /ምሉዕ በኩለሄ/ ነው፡-

እግዚአብሔር በሁሉ ሙሉ ነው፤ ከዚህ አለ ከዚያ የለም ወይም ከዚያ አለ ከዚህ የለም አይባልም በሰማይ ይኖራል መባሉም ስለ ክብሩና ስለ ልዕልናው ነው። *‹‹ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ አለህ። ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች።››* መዝ. ፻፴፱ ፥ ፯ - ፲። *‹‹ለመለኮት ወርድና ቁመት ላይና ታች ቀኝና ግራ ያለው አይደለም፤ በሁሉ የሞላ ነው እንጂ፤ ለመለኮት የሚዘረጋበት የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም፤ ግዛቱ በሀገሩ ሁሉ የሞላ ነው እንጂ፤ ከመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ያለው አይደለም ጠፈሩ እርሱ መሠረቱ እርሱ ነው እንጂ። ››* እንዳለ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም።

*በተጨማሪም የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ* ኤር. ፳፫ ፥ ፳፫ - ፳፬፣ መዝ. ፻፴፰ ፥ ፯ - ፲፣ መዝ. ፺፯ ፥ ፻፲፩፣ መዝ. ፪ ፥ ፬፣ ማቴ. ፭ ፥ ፴፬፣ ዮሐ ፫ ፥ ፲፫።

### 2.ሁሉን አዋቂ ነው፡-

እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነውና ከእርሱ የተሰወረ ነገር የለም፤ *‹‹አንተም፥ ልጄ ሰሎሞን ሆይ፥ እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና፥ የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና፥ የአባትህን አምላክ እወቅ በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው ብትፈልገው ታገኘዋለህ ብትተወው ግን ለዘላለም ይጥልሃል።››* ፩ኛ ዜና. ፳፰ ፥ ፱።

ያለፈውንና ያሁኑን የሚመጣውን ያልተነገሩትንም ሐሳቦች፣ ቃላትንና ተግባራትን ከመሆናቸው አስቀድሞ ያውቃል። *‹‹ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።››* ዮሐ. ፪ ፥ ፳፫።

### 3.ሁሉን ቻይ /ከሃሌ ኩሉ/ ነው፡-

እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ የሚሳነው ነገር የለም። *‹‹ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም››* ዘፍ. ፲፰ ፥ ፲፬። ሁሉንም የፈጠረው ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ነው። ዘፍ. ፩ - ፪። ለማንም የማይቻለው ሁሉ በእርሱ ይቻላል፤ ሌሎች እንዲችሉም ማድረግምይችላል። ዘፍ. ፲፰፥፲፬፣ መዝ. ፻፴፬፥፮፣ ኤር. ፴፪፥፲፯፣ ማቴ. ፲፱ ፥ ፳፮፣ ሉቃ. ፩ ፥ ፴፯።

በቻይነቱ ይታገሰናል። *‹‹ነገር ግን እግዚአብሔር ቍጣውን ሊያሳይ ኃይሉንም ሊገልጥ ወዶ፥ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለ ጠግነት ይገልጥ ዘንድ፥ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎች በብዙ ትዕግሥት ከቻለ፥ እንዴት ነው?››* ሮሜ. ፱ ፥ ፳፪።

www.zeorthodox.org

## ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር

ለእኛ በሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እርሱ እኛን የሚቆጥረን የራሱ ክፋይ አድርጎ ነው፡ -*‹‹እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡››* ዮሐ. ፲፭÷፭፡፡ እንዲህም ብሎናል፡- *‹‹... ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን...››* ኤፌ. ፭÷፴ ከዚህም በተጨማሪ *‹‹...በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፡፡››* ዮሐ ፲፭ ÷ ፬ ብሏል፡፡

እኛን አስመልክቶ ለአባቱ ሲናገርም *‹‹እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ ፤እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹም እንዲሆኑ ...››* ዮሐ ፲፯÷፳፪ ብሏል፡፡ በመጽሐፍ *‹‹... ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች...››* ፪ኛ ጴጥ ፩÷፬ ተብሎ የተጻፈው እና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚያሳየው አገላለጽ ምንኛ ድንቅ ነው!

ከዚሁ በተመሳሳይ *‹‹...የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡››* ፪ኛ ቆሮ ፲፫ ÷ ፬፡፡ ተብሎ ተጽፏል፡፡ በእርግጥ ይህ ኅብረት የሥራ እንጂ የአካልና የባሕርይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ ወንድሙ ስለ ሲላስ ሲናገር ከእርሱ ጋር አብረን የምንሰራ ነን ብሏል፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር ለእኛ ካለው አሠራር አንዱ በእርሱና በእኛ ሰዎች ዘር መካከል የዳበረው ወዳጅነት ነው፡፡ አብርሃም *‹‹አርከ እግዚአብሔር››* ወይም *‹‹የእግዚአብሔር ወዳጅ››* ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ስለ ሄኖክም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡፡ *‹‹ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና፡፡››* ዘፍ ፭ ÷ ፳፬፡፡

ሙሴም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው ላይ ለዐርባ ቀናት ቆይቷል፡፡ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም ሌሎች ምሳሌዎቻችን ናቸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር የነበረው ኅብረት ልዩ ነበርና፡፡ እግዚአብሔር ደስታን ከሰው ልጆች ጋር ማድረጉም ድንቅ ነው፡፡እርሱ የማይወሰን አምላክ ሆኖ በሚወሰኑት ሰዎች ዘንድ ትሕትናውን በመግለጥ ከእነርሱ ጋር ኅብረት ፈጥሯል፡፡ ለእነርሱ በመገለጥም ቃል በቃል አነጋግሯቸዋል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

ታሪክ እንደሚነግረን እነዚህ ሁሉ የእንክብካቤ አስደናቂ መንገዶች የተገለጡት እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የቀይ ባህር ለሁለት መከፈል፣ በምድረበዳ የወረደው መና፣ ከጭንጫ ከዓለት የፈለቀው ውኃ፣ በረሃቡ ዘመን የኤልያስ መጠበቅ፣ ጴጥሮስን ከእስርቤት፣ ዳንኤልን ከአናብስት ጉድጓድ፣ ሠለስቱ ደቂቅን ከእቶነ እሳት ማውጣት እና ሌሎችም ማብቂያ የሌላቸው የእንክብካቤ እና የጥበቃ ታሪኮች ለእኛ ተደርገውልናል፡፡

***‹‹እነሆ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጨሻለሁ፡፡››*** ኢሳ ፵፱፥፲፮፣ ‹‹የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሯል፡፡›› ማቴ ፲፥፴፣ ***‹‹አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፡፡››*** ሕዝ ፴፮፥፳፮፣ ***‹‹ከአባቴም እጅ ሊነጥቃችሁ ማንም አይችልም፡፡››*** ዮሐ ፲ ፥ ፳፱፣ ***‹‹ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤››*** ዮሐ ፲፬ ፥ ፪፡፡ የተሰጡትን ስጦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር የሚገልጡ ናቸው፡፡ የዘላለማዊነት ስጦታ ፣በእርሱ ክብር በአካል የሚሆን የትንሣኤ ስጦታና ሌሎችም ብዛት ያላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፍቅር የተባረኩ ናቸው፡፡

## ተግባር

ይህን የተማራችሁትን ትምህርት ለሌሎች አስረዱ፤ አካፍሉ፡፡

www.zeorthodox.org

# የቃል ኪዳኑ ታቦት

## ዐርባ ሰባተኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** በመገናኛው ድንኳን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የነበሩት ምን ምን እንደሆኑ መግለጽ፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት ትርጉምና አገልግሎት ምን እንደነበርና የቃል ኪዳኑን ታቦት ታሪክና ከቦታ ቦታ መዘዋወሩን ማስገንዘብ፡፡

**ጥቅስ፡-** *"በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፡፡ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ፡፡"* ዘጸአ. ፳፭ ፥ ፳፪፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ኦሪት ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቍ እና ዘዳግም፣ መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ፣ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና ካልዕ፣ ራእ 11፡19፣ ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፡፡

### መግቢያ

በመገናኛው ድንኳን ከነበሩት ሥፍራዎች ከሁሉም የተለየ የነበረው ቅድስተ ቅዱሳን ነው፡፡ ቅድስተ ቅዱሳኑም ከሌሎቹ በመጋረጃ ተለይቶ በውስጡ የቃል ኪዳኑን ታቦት ብቻ ይዞ ይኖር ነበር፡፡ የሕዝቡንም ኃጢአት ለማስተስረይ የመሥዋዕቱን ደም ሊረጭ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚቻለው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፤ ይኸም ብቸኛ ለሆነው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት ምሳሌ ነበር፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

www.zeorthodox.org

በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ልዩ የሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት ነበር፡፡ እርሱም የእግዚአብሔር መኖርና ለእስራኤላውያን የገባውን ቃል ኪዳን የሚያመላክት ምሳሌ ነበር፡፡ የቃል ኪዳኑም ታቦት ከግራር እንጨት የተሠራ ሆኖ በውጭና በውስጥ በወርቅ የተለበጠ ነበር፡፡

በታቦቱ ውስጥም በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ አሠርቱ ሕግጋት የሚገኙባቸው ሁለት ጽላቶች ነበሩ፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት በሥርየት መክደኛ ተሸፍኖ ነበር፡፡ በላዩም የተዘረጋ ክንፍ ያላቸው ሁለት የኪሩብ ሥዕል ነበር፡፡ ክንፋቸውም እርስ በርሱ በመነካካት የሥርየት መክደኛውን ይሸፍነው ነበር፡፡ ይኸም እግዚአብሔር ሙሴን ሲያነጋግረው ድምፁ የሚሰማበት ሥፍራ ነበር፡፡ በመገናኛው ድንኳን የእግዚአብሔር ዙፋን የቃል ኪዳኑ ታቦት ነበር፡፡

የቃል ኪዳኑ ታቦት እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር መርቷቸዋል፡፡ በወርቅ በተሸፈነ ማክበሪያ (መሸከሚያ) ሌዋውያኑ ይሸከሙት ነበር፡፡ ማንኛውም ተራ ሰው ታቦቱን ለመንካት አይፈቀድለትም ቢነካውም ይሞት ነበር፡፡

## የቃል ኪዳኑ ታቦት ታሪክና ጉዞ

ሙሴም ሁለቱን ጽላቶች ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አኖራቸው፡፡ በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ አስቀመጠው፡፡ ቀጥሎም የእግዚአብሔር ክብር በደመና መልክ ሥፍራውን ሁሉ ሞላው፡፡ ከሰባት ሳምንታት በኋላም ደመናው ራቀላቸውና መጓዝ ጀመሩ፡፡ ዘወትርም ደመናው በጠዋት የእሳትም ዐምድ በማታ ሲታይ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በመቆየት ወደ ላይ ሲመለስ ጉዞአቸውን ይቀጥሉ ነበር፡፡

የቃል ኪዳኑ ታቦት የሲናን ተራራ ትተው ሲጓዙ የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ እንዲሁም የኢያሪኮን ቅጥር (ግንብ) ሲዞሩ መሪያቸው ኃይላቸውም ነበር፡፡ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እስራኤ ላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ታቦቱን ይዘው መዋጋት ፈለጉ፡፡ ፩ኛ ሳሙ. ፬፥፬ - ፯፥፳፩፡፡ ነገር ግን ተሸንፈው ታቦቱም ተማረከ፡፡

ታቦቱንም ወስደው በጣዖት ቤት ዳጎን ከተባለው ጣዖት ሥር ሲያስቀምጡት ጣዖቱ ተሰባበረ፡፡ ታቦቱንም ጌት ወደ ተባለው የፍልስጥኤማውያን ከተማ አዞሩት፡፡ ታቦቱም ሲገባ የጌት ሰዎች በአዲስ በሽታ ተመቱ፡፡ በኋላም አስቀሎና ወደ ተባለው ከተማቸው አዞሩት በመጨረሻም በሁለት ላሞች ላይ ተቀምጦ ወደ ዕብራውያን በቤት ሳሚስ በኩል ተመለሰ፡፡ የእግዚአብሔርም ታቦት በቂርያት ይዓሪም ወደ ሚገኘው ወደ አሚናዳብ ቤት ተወሰደ፡፡ በዚያም ለሃያ ዓመታት ተቀመጠ፡፡ ፩ኛ ሳሙ. ፯፥፩-፪፡፡ በኋላም በንጉሥ ዳዊት ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ተወሰደ፡፡ ፪ኛ ሳሙ. ፮ ፥ ፩ እስከ ፍፃሜ፡፡

በመቀጠልም ንጉሥ ሰሎሞን ታላቁን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሠርቶ ታቦቱን በቤተ መቅደሱ በኢየሩሳሌም አኖሩት፡፡

## ማጠቃለያ

www.zeorthodox.org

ያ ታቦት ዛሬ በአገራችን በአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ተጠብቆ ተከብሮ ይገኛል፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ ጌታችን ሰው ሆኖ ሰውን ለማዳን ተአምራትን በማድረግ በየሥፍራው ሁሉ የመዘዋወሩ ምሳሌ ነው፡፡

ውስጡ በወርቅ ተሞልቶ በውጭ በድንኳን የተሸፈነው የመገናኛው ድንኳን አምላክ ሆኖ ሳለ በውጪ ለሚያዩት ግን በፍፁም ትሕትና የባርያውንም መልክ ይዞ የተመላለሰው የጌታችን ምሳሌ ነው፡፡ ኢሳ ፶፫ ፥ ፪ - ፫፡፡ ከዚህም ጋር ታቦቱ በወርቅ የተለበጠ ነበር እርሱም ታቦቱም ወርቅ ንጹሕ እንደሆነ የእምቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የንጽኅናዋ ምሳሌ ነበር፡፡

የመገናኛው ድንኳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝበት ሥፍራ ነበር፡፡ታቦት የእግዚአብሔር ማደርያ እንደነበረም እርሱም ይገለጥበት እንደነበር በእውነተኛይቱ ማደርያው በድንግል ማርያም ክርስቶስ ተገልጦ ዓለሙን አድኗል፡፡

## ተግባር

ስለ ታቦትና ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ስላለው አገልግሎት ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ፡፡

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በምድር ከርሱ ጋር የምንገናኝበት ሥፍራ እንድናዘጋጅ ካዘዘን ከርሱ ጋር በተሰበሰበ ልብ ሆነን መጸለይስ አያስፈልገን ይሆን?
2. የመገናኛውን ድንኳን ከቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ጋር በማነጻጸር ልዩነታቸውን ግለጹ፡፡
3. በመገናኛ ድንኳን ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት የተቀመጠበት ሥፍራ ምን ይባል ነበር?
4. በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ የተቀመጠው ምንድር ነበር?
5. የቃል ኪዳኑ ታቦት በምን የተከበበ ወይም የተሸፈነ ነበር?
6. የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣው ማን ነበር?

www.zeorthodox.org

# አስማተ እግዚአብሔር - የእግዚአብሔር ስሞች

## ዐርባ ስምንተኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** የእግዚአብሔርን ስሞች ማስተዋወቅና የስሙን ኃይል ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"ስሙም ቅዱስ ነው፡፡"*** ሉቃ. ፩ ፥ ፵፱፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን

### መግቢያ

ልጆች ስለ እግዚአብሔር ስሞች ምን ታውቃላችሁ? ለመምህሩ አስረዱ፡፡ በግእዝ አስማት በዕብራይስጥ ሻሚም ማለት በአማርኛ ስሞች ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ የእግዚአብሔር ስሞች አሉ፡፡ በዛሬው ትምህርታችን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን የእግዚአብሔር ስሞች ***ክብር ኃይልና ትርጉም*** እንማራለን፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

### የሳምንቱ ትምህርት

#### የእግዚአብሔር ስም ክብር

***ስሙ ቅዱስ ነው፡፡*** እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡ ፩ኛ ጴጥ. ፩ ፥ ፲፭ - ፲፮፡፡ የእርሱ የሆነው ሁሉም ቅዱስ ነው፡፡ ***"ስሙም ቅዱስ ነው፡፡"*** ሉቃ. ሉቃ. ፩ ፥ ፵፱፡፡ ቅዱስ የሆነው ስሙ የከበረ ነው፡፡ ለዚህ በዕለታዊ ጸሎታችን ***ስምህ ይቀደስ*** ማቴ. ፮ ፥ ፲፱፡፡ የምንለው፡፡

www.zeorthodox.org

***በከንቱ አይጠራም፡፡*** የእግዚአብሔር ስም ታላቅ ነው፡፡ ፪ኛ ሳሙ. ፯ ፥ ፳፮፡፡ ከአሠርቱ ትእዛዛት ሁለተኛው ***"የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ"*** ዘጸ. ፳ ፥ ፯ በመሆኑም በከንቱ በፌዝ፣ ለመጫወቻነት፣ በሐሰት ለመማልም አይጠራም፡፡ እንዲያውም ***"በአንድነት ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።"*** እንጂ ፴፫ (፴፬) ፥ ፫፡፡

#### የእግዚአብሔር ስም ኃይል

ይጠብቀናል፣ ያድናልም፡፡ ***"አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ፥ እርዳን ስለስምህ ክብር፥ አቤቱ፥ ታደገን፥ ስለስምህም ኃጢአታችንን አስተሰርይልን፡፡"*** መዝ. ፸፱ ፥ ፱፣ ማቴ. ፪ ፥ ፳፩ እንማጸንበታለን፡፡

*“ለታላቁ ስምህም የምታደርገው ምንድርነው?”* ኢያ. ፯ ፥ ፱፣ ዮሐ. ፲፯ ፥ ፳፬ ከፍ ያደርገናል። *“የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል።”* ምሳ. ፲፰ ፥ ፲ ድል ያደርጋል። *‹‹ሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው።›› መዝ.፻፲፯፥፲፣‹‹በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን፥ በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን።›› መዝ .፵፫፥፭፣ ‹‹አቤቱ በስምህ አድነኝ።››* መዝ ፶፫ ፥ ፩።

## ስሞቹና ትርጉማቸው

***ስሙ እርሱን ይገልጣል።*** እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፣ በሁሉም ያለ፣ ሁሉን አዋቂና ዘለዓለማዊ ነው። ስሙ ይህን ባሕርይውን ይገልጣል። የሚከተሉትም ስሞች ይህን ያረጋግጣሉ።

***ኤልሻዳይ*** - ሁሉን ቻይ ማለት ነው። ይህ ስም የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነትና አዋቂነት ያመለክታል። በዚህ ስም ለአባታችን ለአብርሃም ተገለጠለት። ***“እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና። እኔ ኤልሻዳይ ነኝ በፊቴ ተመላለስ፥ ፍጹምም ሁን....አለው”*** ዘፍ. ፲፯ ፥ ፩።

***ያህዌ*** - ያለና የሚኖር ማለት ነው። ይህ ስም የእርሱ ብቻ የሆነውን ዘላለማዊነት ያመለክታል። ***‹እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ’ያለና የሚኖር’ (ያህዌ) እኔ ነኝ አለው እንዲህ ለእስራኤል ልጆች። ’ያለና የሚኖር’ ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ አለው።›*** ዘጸ. ፫ ፥ ፲፬ ያለውና ወደፊት የሚኖረው ሁሉ፤ መጀመሪያ አለው አምላካችን ግን ከጊዜያት በፊት ብቻውን የነበረ አምላክ ነው።

ከእነዚህ ሁለት ስሞች ጋር ተያይዘው የሚጠሩና የአምላካችንን ኃይልና ማዳን የሚገልጡ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ አሉ። ለምሳሌ፦

ያሕዌ ይሬኢ ***“አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል።”*** ዘፍ. ፳፪ ፥ ፲፬።

ያሕዌ ንሲ ***“ሙሴም መሠዊያ ሠራ፥ ስሙንም ይህዌህ ንሲ ብሎ ጠራው።”*** ዘጸ. ፲፯፥፲፭

ኤልሮኢ ***“እርስዋም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም ኤልሮኢ ብላ ጠራች የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን? ብላለችና።”*** ዘፍ. ፲፮ ፥ ፲፫።

www.zeorthodox.org

የሰውና የቦታ ስሞችም ይህንን የእግዚአብሔር ስም እንዲያመለክቱ ሆነው በእስራኤል ይወጡ ነበር። ለአጠራርም የመጀመሪያዎችን ፊደሎች ከቃላት ጋር ይጣመሩ ነበር። ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ስሞች በሚባል ደረጃ ከእነኚህ ስሞች ጋር ተያይዘው ይጠሩ ነበር። ለምሳሌ ከአማርኛ ትርጉማቸው ጋር የቀረቡትን አስተውሉ፦ **እስራኤል - የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ዳንኤል - እግዚአብሔር ዳኛ ነው፣ ዮናታን - እግዚአብሔር ሰጠኝ፣ ዮዳሄ - እግዚአብሔር ያውቃል።** እናንተስ የስማችሁን ትርጉም ታውቅታላችሁ? ለመምህር ንገሩ።

ሌሎች እግዚአብሔር ስሞችም አሉ፡- **አዶናይ** - የኔ ጌታ (ጌታዬ) ማለት ነው፡፡ ዘፍ. ፲፫ ፥ ፫፡፡ **ጸባዖት** - የሠራዊት ጌታ ማለት ነው፡፡ ፩ኛ ሳሙ. ፩ ፥ ፲፩፡፡

## በሐዲስ ኪዳን የተገለጡ ስሞች

በጌታችን ሰው መሆን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወሩ ምሥጢሮች ተገልጠዋል፡፡ማቴ. ፲፫ ፥ ፴፭፡፡ የእግዚአብሔርን የአንድነት የሦስትነት ስም ያወቅነውም በጌታችን ሰው መሆን ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉትን ስሞች አንመልከት፡፡

**አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፡-** የግብር ስሞች ናቸው፡፡ አብ አባት ወላዲ ፤ ወልድ ልጅ ተወላዲ፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ፡፡ ይህንን ስም ጌታችን በተለያየ መልክ ሲያስተምር ቆይቶ፤ በዕርገቱ ***"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ፡"*** ብሎ አዘዘ፡፡ ማቴ ፳፰ ፥ ፲፱ በዚህ ስም እንጠመቃለን፣ እናማትባለን ድልም እናደርጋለን፡፡

**ኢየሱስ፡-** አዳኝ (መድኃኒት) ማለት ነው፡፡ ስሙን ነቢያት በተለያየ መንገድ ሲተነብዩት ነበር፡፡ ኢያሱ ኢሳይያስና ሆሴዕ ተጠሩበት፡፡ ያዕቆብ ‹‹***እግዚአብሔር ሆይ መድኃኒትህን እጠብቃለሁ፡፡***›› ዘፍ. ፵፱፥፲፰ ሲል ዳዊትም ***"እግዚአብሔር፦አሁን እነሣለሁ ይላል መድኃኒትን አደርጋለሁ፥"*** መዝ. ፲፪፥፭፡፡ እንዲሁም ኢሳ. ፲፱፥፳፣ ፶፱፥፲፮ ይነበቡ፡፡ ዘመኑ ሲደርስ ቅዱስ ገብርኤል የአዳኙን ስም ለእመቤታችን ***"ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ"*** ሉቃ. ፩፥፴፩ ሲል አበሰራት፡፡ ትርጉሙንም ለጻድቁ ዮሴፍ ነግሮታል፡፡ ***"እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።"*** ማቴ. ፩ ፥ ፳፩፡፡

ይህ ስም ከስም ሁሉ የሚበልጥ ነው፡፡ ፊል. ፪፥፱-፲፩፤ ከሞት ፍርድ ያድናል፡፡ ዮሐ. ፫፥፲፰፤ አጋንንትንና ደዌያትን ያወጣል፡፡ ማር.፲፮፥፲፯፣ ዘላለማዊ ክብርን ለማግኘት መከራን የሚቀበሉበት ስም ነው፡፡ የሐዋ. ፭፥፵፩፤ ድል አድራጊ እና አስገኝ ስም ነው፡፡ ፪ኛ ቆሮ ፪ ፥ ፲፬፡፡

**አማኑኤል፡-** እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው፡፡ ኢሳ. ፯ ፥ ፲፬፣ ማቴ. ፪፥፳፪-፳፫፡፡ ክርስቶስ ሲወለድ የተጠራበት ስም ነው፡፡ ይህ ስምም ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቃችን ስም ነው፡፡

www.zeorthodox.org

**ቃል፡-** የወልድ የኩነት ስም ነው፡፡ ዮሐ. ፩፥፩ **ጰራቅሊጦስ** - አጽናኝ ማለት ነው፡፡ ዮሐ ፲፬፥፲፮፡፡

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ስም ታላቅና ቅዱስ ነው፡፡ በከንቱ አይጠራም፡፡ ከኃጢአት እና ከዲያብሎስ ያድናል፡፡ ድል ማድረጊያ ስምም ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስም እርሱን ይገልጣል፡፡ እኛም በስሙ እንድንታመን ታዘናል፡፡ ስሙንም ማክበር የኦርቶዶክሳውያን መለያ ነው፡፡

**ተግባር፡-** የተማራችኋቸውን የእግዚአብሔር ስሞች በቃላችሁ አጥኑ፡፡

# ቅድስት ሥላሴ

## ዐርባ ዘጠነኛ ሳምንት

**የትምህርቱ ዓላማ፡-** ስለ እግዚአብሔር ሦስትነት ማስገንዘብ፡፡

**የሚጠና ጥቅስ፡-** ***"በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም"*** ማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱፡፡

**ተጨማሪ ምንባባት፡-** ትምህርተ መለኮት በአሥራት ገብረ ማርያም፣ ዶግማ በአቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያልታተመ ጽሑፍ፣ ቤተ ክርስቲያንህን እወቅ በማኅበረ ቅዱሳን፡፡

## መግቢያ

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የእግዚአብሔርን ስሞች ተምረናል፡፡ ከዚያ በፊትም ሃይማኖት ምን እንደሆነና እንዴት እንደተገለጠም አይተናል፡፡ የማይመረመረው የእግዚአብሔርን ባሕርይም በቅዱሳት መጻሕፍት ራሱን በገለጠው መጠን አጥንተናል። መምህር እነዚህን ትምህርቶች ይከልሱላቸው።

በዛሬው ትምህርታችንም የእግዚአብሔርን የሦስትነት ምሥጢር እንማራለን፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

### የእግዚአብሔር ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ

በባሕርይ በመለኮት አንድ የሆነው እግዚአብሔር፤ሦስትነት አለው፡፡ ***"እግዚአብሔርም አለ ሰዉን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር "*** ዘፍ. ፩፥፳፮፡፡ ልጆች እዚህ ላይ እግዚአብሔር አለ ብሎ አንድነቱን፤ ***በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር*** ብሎ ሦስትነቱን እንደነገረን አስተውሉ፡፡

ሰው በነፍሱ የእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ነው፡፡ አንድዋ ነፍሳችን ሦስት ነገር አላት፡፡ እነርሱም ሕያውነት፣ አዋቂነት እና ተናጋሪነት ይባላሉ ወይም በግዕዝ ሕያዊት፣ ለባዊት፣ ነባቢት ይባላል፡፡ ይህ የነፍሳችን ሦስትነት የእግዚአብሔር ሦስትነት አምሳል ነው፡፡

***"እግዚአብሔርም አለ ፡-......ኑ እንውረድ"*** ዘፍጥ. ፲፩ ፥ ፯ - ፺፡፡ እዚህ ላይ አንዱ ሌሎችን እየጠራ ይመስላል፡፡ ኑ ሁለቱን አካላት፤ አለ ሦስተኛውን አካል ያመለክታል፡፡

***"በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት፡፡ ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደ፥ እንዲህም አለ፡- አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ***

www.zeorthodox.org

***እንደሆነ ባርያህን አትለፈኝ ብሎ እለምናለሁ፤ጥቅት ውኃ ይምጣለችሁ እግራችሁን ታጠቡ …ዕረፉ”*** ዘፍ. ፲፰፥፩-፳። እግዚአብሔር የእምነት አባት ለሆነው ለአብርሃም በአንድነትና በሦስትነት ተገልጦለታል። ያየው ሦስት ሰዎች ነው። ነገር ግን ***በፊትህ …ባርያህን አትለፈኝ*** በማለት አንድነቱን ፤ ***ይምጣለችሁ እግራችሁን ታጠቡ … ዕረፉ…*** ብሎም ሦስተነቱን መስክሯል።

**እግዚአብሔር፡-** በስም በግብር እና በአካል **ሦስት** ነው።

***ሀ.*** **<u>የስም ሦስትነት</u>**፡-***‹‹አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ››*** ማቴ ፳፰ ፥ ፲፱።

***ለ.*** **<u>የአካል ሦስትነት</u>**፡- አብ የራሱ መልክ፣ ገጽ እና አካል አለው። ወልድ የራሱ መልክ፣ ገጽ እና አካል አለው ። መንፈስ ቅዱስም የራሱ መልክ፣ ገጽ እና አካል አለው። ማቴ ፫ ፥ ፲፮ - ፲፯። ስለ ክርስቶስ እየመሰከረ በድንጋይ ተወግሮ የሞተው ቅዱስ እስጢፋኖስም ሰማያት ተከፍተው ክርስቶስን በተለየ አካሉ በአብ ቀኝ ተመልክቷል። ***“ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ”*** የሐዋ ፯ ፥ ፶፮ አለ።

***ሐ.*** **<u>የግብር ሦስትነት</u>**፡- አብ ወልድን ወልዶታል ግብሩ ወላዲነት ነው። ወልድ ከአብ ተወልዷልና ግብሩ ተወላዲነት ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለወጣ (ስለ ሠረፀ) ግብሩ ሠራጺ (የሚወጣ) ይባላል። ***‹‹አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ።››*** መዝ. ፪፥፯ ***‹‹የምወደው ልጄ እርሱ ነው።››*** ማቴ. ፫፥፲፯ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረፀ ማለትም ከአካሉ ከባሕርይው ተገኘ ማለት ነው።***“እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።”*** ዮሐ. ፲፭ ፥ ፳፯።

**ኩነት፡-**

ኩነት መሆን ማለት ነው። የአብ ኩነት ልብነት ነው። የወልድ ኩነት ቃልነት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት ነው። ጥቅሶቹን አስተውሉ፡-

***‹‹የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዩች ጸኑ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።››*** መዝ ፴፪ ፥ ፮። ***‹‹የምነግራችሁ ቃል የእኔ አይደለም ፣ በእኔ የሚኖር የአብ ነው እንጂ።››*** በአብ ልብነት የታሰበውን በወልድ ቃልነት ይነገራል። ዮሐ ፲፬ ፥ ፲።

***“ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ያም ቃል እግዚአብሔር ነበር።”*** ዮሐ. ፩ ፥ ፩ - ፫። መንፈስ ቅዱስም ***‹‹እስትንፋስ››*** መዝ ፴፪ ፥ ፮ ተብሏል። ሰው በልቡ (በአእምሮው) አስቦ፣ በቃሉ እንዲናገር እስትንፋስ እስካለው ሕያው ሆኖ እንዲኖር ማለት ነው።

አብ በወልድ ቃልነት ይናገራል በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው። ወልድም በአብ ልብነት ያስባል በመንፈስ ቅዱስ ሕያው ነው። መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባል በወልድ ቃልነትም ይጋራል።

www.zeorthodox.org

ለሦስቱም የየራሳቸው ልብነት ቃልነት እስትፋስነት የላቸውም። ከላይ እንደተባለው በፈቃድ፣ በሥልጣን በሕልውና አይለያዩም።

## ማጠቃለያ

አንዱ እግዚአብሔር ሦስትነት አለው። ይህ ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል።
ሦስትነቱም በስም በአካልና በግብር ነው።
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መበላለጥ፣ መቀዳደም የለባቸውም።

## ተግባር

- ከመምህርና ከቤተሰብ በመጠየቅና መጻሕፍትን በማንበብ የእግዚአብሔርን ሦስትነት በደንብ ተረዱ።

www.zeorthodox.org

# ጾመ ፍልሰታ

# ሃምሳኛ ሳምንት

**ዓላማ፡-** ስለ ፍልሰታ ጾም መግለጽ፡፡

**ጥቅስ፡-** *‹‹አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፤ አንተና የመቅደስህ ታቦት፡፡»* መዝ ፻፴፩፥፰፡፡

**ተጨማሪ ምንባብ፡-** ነገረማርያም፣ ድንግልማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ

## መግቢያ

መምህር ያለፈውን ሣምንት ትምህርትና ጥቅስ ያስታውሱአቸው፡፡

ፍልሰታ ፈለሰ፣ መፍለስ፣ መሰደድ፣ ተማርኮ መሄድ፤ መዞር መባከን ወደ ሌላ ሕዝብ መጠጋት፣ መሞት መለየት፤ ማረግ ወደ ላይ መውጣት፣ ከምድር ከመቃብር መነሣት ማለት ነው፡፡ ጾመ ፍልሰታ ሲባልም የእመቤታችን ሥጋ ከጌቴሰማኒ ወደ ገነት መፍለስን በኋላም በገነት በዕፀ ሕይወትሥር ከነበረበት መነሳቱን ለማመልከት የሚነገር ነው፡፡

ነቢያት አስቀድመው ስለ እመቤታችን ዕረፍትና ትንሣኤ በምሥጢር ተናግረዋል፡፡ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ መዝ ፻፴፩፥፰፡፡ **«አቤቱ ወደ ዕረፍትህተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት»** ብሎአል፡፡ ፈጣሪዬ ሆይ ምእመናንን ወደ ምታሳርፍበት ወደ መንግሥተ ሰማያት የመቅደስህን ታቦት ድንግል ማርያምን ይዘህ ተነሥ ሲል ነው፤ ይህም እመቤታችን እንደ ልጇ ትንሣኤ መነሳቷን የሚያመለክት ነው ታቦት ያላትም ማደሪያው ስለሆነች ነው፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን **«ወዳጄ ሆይ ተነሺ ውበቴ ሆይ ነይ እነሆ ክረምት አለፈ ዝናቡም አልፎ ሄደ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ የዜማም ጊዜ ደረሰ የቀረ… ቃል በምድራችን ተሰማ በለሱ ጐመራ ወይኖችም አበቡ መዐዛቸውንም ሰጡ ወዳጄ ሆይ ተነሺ ውበቴ ሆይ ነይ»** ሲል ስለ እመቤታችን በምሳሌ ተናግሮአል፡፡ መኃ ፪ ፥ ፩-፲፫፡፡

www.zeorthodox.org

ወዳጁን ውበቱን ተነሺ ነይ እያለ የተጣራው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ተጠሪዋም እመቤታችን ናት፡፡ እነሆ ክረምት አለፈ ማለት በስደት በአይሁድ የዘወትር ጠላትነት በልጅዋ መከራና ስቅላት ስምዖን በቤተ መቅደስ እንደተናገረ ልቧ በኃዘን ሠይፍ የተከፈለበት በኀዘን ፍላጻ የተወጋበት የመከራ ክረምት /ወቅት/ አልፎ የክርስቶስ ሕማሙ ሞቱ ቤዛነቱ ተፈጽሟል፡፡ ትንሣኤው በምድር ላይ ተገልጧል፣ ተሰብኳል ማለት ነው፡፡ በምድራችን አበባ ታይቷል ማለት የሐዋርያት ድምፅ በምድር ሁሉ ደርሷል ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣብሎ ስለ ሐዋርያት የተናገረው በዓለም ያለውን መከራ ስደት ሲገልጽ ነው፡፡ መዝ. ፲፰፥፬፡፡

የዜማም ጊዜ ደረሰ ያለው የመከራን ጊዜ ነው፡፡ ሽለቆችም በእህል ተሸፈኑ በደስታ ይጮሃሉ ይዘምራሉም ተብሏል፡፡ መዝ ፷፬፥፲፫፡፡ የመከር ጊዜ ደረሰየተባለው መከር የፍሬ ጊዜ በመሆኑ ክርስትና አፍርቷል ማለት ነው፡፡ በለሱ ጐመራ ማለት ደግሞ በጐ ምግባረ ፍሬ ሳያፈሩ የነበሩ ሰዎች በጐ ምግባር መሥራት መጀመራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመጨረሻም ወይኖች አብበዋል፣ መዐዛቸውንም ሰጥተዋል እንደተባለ በመላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት በሃይማኖት አብበው መዐዛ ምግባራቸውን ማቅረብ ከጀመሩ በኋላ እመቤታችን ዐረፈች፡፡

## የሳምንቱ ትምህርት

እመቤታችንም ጥር 21 ቀን ዕረፍት በሆነበት ዕለት ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ ለማሳረፍ ወደ ጌቴሰማኒ መካነ ዕረፍት /የመቃብር ቦታ/ ይዘው ሲሄዱ አይሁድ በቅንዓት መንፈስ ተሟሥተው «ቀድሞ ልጇ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ እንደገናም ተመልሶ ይህን ዓለም ለማሳለፍ ይመጣል እያሉ በማስተማር ሕዝቡን ፈጽመው ወስደውታል አሁን ደግሞ ዝም ብለን ብንተዋት እርሷንም እንደ ልጇ ተነሣች ዐረገች እያሉ በማስተማር ሲያውኩን ሊኖሩ አይደለምን? ኑ ተሰብሰቡና በእሳት እናቃጥላት፡፡ዓዓ ብለው ተማክረው መጥተው ከመካከላቸው ታውፋንያ የተባለ ጎበዝ አይሁዳዊ ተመርጦ ሄዶ የእመቤታችንን ሥጋ የተሸከሙትን አልጋ ሸንኮር ያዘ፡፡ የአልጋውን ሽንኮር በያዘ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ሠይፍ ሁለት እጁን ስለ ቆረጧቸው፤ እጆቹም ከአልጋው ሽንኮር ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ ታውፋንያ በፈጸመው ድርጊት ተ ጸጽቶ ወደ እመቤታችን ስለተማጸነ በኀቡዕ ተአምር የተቆረጡ እጆቹን እንደ ቀድሞ አድርጋ ፈውሳዋለች፡፡ /ስንክሳር ዘጥር/፡፡

የእግዚአብሔር መልአክ የእመቤታችን ሥጋ ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር ተድላ ደስታ ወደ አለባት ገነት በመንፈስ ቅዱስ ተነጠቁ ጌታምየእመቤታችንን ሥጋ ታወጣ ዘንድ ምድርን እንዲጠ ሩዋት ሰባቱን የመላእክት አለቆች አዘዛቸው እነርሱም ትወጪ ዘንድ እግዚአብሔር አዞሻል አላትያን ጊዜም ከዕፀ ሕይወት በታች ካለ መቃብር የእመቤታችን የማርያም ሥጋዋ ወጣ ጌታችንም ዘላለማዊ ወደሆነ መንግሥተ ሰማያት መላዕክት እናሰማዕታት እየሰገዱላት አሳረጓት ንጉሥ ዳዊት ***«በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋ ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች»*** እንዳለ፡፡ መዝ. ፵፬፥፱፡፡

www.zeorthodox.org

ወንጌላዊ ዮሐንስም ከእርሷ በረከትን ተቀብሎ ተመልሶ ከሰማይ ወረደ፡፡ ሐዋርያት ተሰብስበው ስለ እመቤታችን ሥጋ ፈጽሞ ሲያዝኑና ሲተክዙ አገኛቸው፡፡ እርሱም እንደ አየ እንደ ሰማ ሥጋዋም በታላቅ ክብር ማረጉን ነገራቸው፡፡ ሐዋርያትም ዓመት ሙሉ ቆዩ፡፡ የነሐሴም ወር በባተ /በገባ/ቀን ዮሐንስ እንዲህ አላቸው የእመቤታችንን ሥጋዋን ለማየት ኑ ሁለት ሱባኤ በመጾም እንለምን አለ በጾም በጸሎት ሱባኤ ያዙ ጌታምየእመቤታችንን ሥጋ አምጥቶ ስለሰጣቸው በታላቅ ዝማሬ፣ በውዳሴና በጽኑ ምሕላ ወስደው ቀድሞ በተዘጋጀው መካነ ዕረፍት በጌቴሴማኒ ቀበሯት፡፡

የእመቤታችን የቀብር ሥነ ሥርዓት በተፈጸመ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ቶማስ አልነበረምና ከአህጉረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ እመቤታችን በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ትንሣኤ ተነሥታ ስታርግ ያገኛታል፤ ትንሣኤዋን ሌሎቹ ሐዋርያት አይተው ለእርሱ የቀረበት መስሎት ተበሳጭቶ ***«በመጀመሪያ የልጇን ትንሣኤ አሁን ደግሞ የአንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ»*** ብሎ ከማዘኑ የተነሣ ከደመናው ተወርውሮ ሊወድቅ ቃጣው፡፡ እመቤታችንም ከእርሱ በቀር ሌሎቹ ሐዋርያት ትንሣኤዋን እንዳላዩ ነግራው አጽናናታው ሄዶም ለሐዋርያት የሆነውን ሁሉ እንዲ ነግራቸው አዝዛው ምልክት ይሆነው ዘንድ ሰበኗን /መግነዟን/ ሰጥታው ዐረገች፡፡

ሐዋርያው ቶማስም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት፤ እርሱም «ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር» እንዴት ይሆናል አላቸው፡፡ «አንተ እንጂ የጌታን ትንሣኤ ተጠራጥርከ አሁንም አታምንምን» ብለው በቅዱስ ጴጥሮስ መሪነት ወደ እመቤታችን መካነ መቃብር ይዘውት ሄደው መቃብሩን ቢከፍቱ ሥጋዋን አጡት ደነገጡም «ቶማስም አታምኑኝም ብዬ እንጂ እመቤታችን ተነሥታ ዐርጋለች» ብሎ የሆነውን ሁሉ ነገራቸው ለማረጋገጫ ምልክት እንዲሆን የሰጠችውን ሰበኗን አሳያቸው፡፡ ሰበኗን /መግነዟን/ ለበረከት ቆራርጠው ከተከፋፈሉ በኋላ ወደየ አህጉረ ስብከታቸው ሄደዋል፡፡

ሐዋርያትም ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እኛ እንዴት ይቀርብናል ብለው ከነሐሴ አንድ ቀን ጀምረው ሱባኤ ገቡ በሱባኤው መጨረሻ በነሐሴ ዐሥራ ስድስት ቀን ጌታችን ጸሎታቸውን ተቀብሎ እመቤታችንን መንበር፣ ቅዱስ ጴጥሮስን ንፍቅ /ረዳት/ ቄስ ቅዱስ እስጢፋኖስን ገባሬ ሰናይ /ዋና/ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ ሁሉንም ከአቆረባቸው በኋላ የእመቤታችንን ዕርገቷን ለማየት አብቅቷቸዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያናችንም ሥርዓት ሠርታ ከሰባቱ ዐበይት አጽዋማት ተርታ አስገብታ ይህን ታላቅ የበረከትና የምሥጢር መግለጫ ጾም እንድንጾም አድረጋናለች፡፡ ሐዋርያት ያዩትን ድንቅ ምሥጢር የእመቤታችንን ትንሣኤና ዕርገት ለማየትና ከሐዋርያት አበው በረከት ለመሳተፍ ጌታችን ልጆቼ ይላቸው በነበሩ ሐዋርያት አምሳል ሕፃናትና ወጣቶች፣ ሴቶችና ወንዶች አረጋውያንም የጾመ ፍልስታን መድረስ በናፍቆት እየጠበቁ በየዓመቱ በጾም በጸሎት ያሳልፉታል፡፡

www.zeorthodox.org

## ማጠቃለያ

በእመቤታችን ትንሣኤና ዕርገት መታሰቢያ /በጾመ ፍልሰታ/ ወቅት ብዙዎች ከቤታቸው ተለይተው በመቃብር ቤት ዘግተው፣ አልጋና ምንጣፍ ትተው፣ በመሬት ላይ ተኝተው ዝግን ጥሬ እፍኝ ውኃ እየቀመሱ በጾምና በጸሎት በመትጋት በታላቅ ተጋድሎ ይሰነብታሉ፡፡ ፍልሰታ ምእመናን ለእመቤታችን ያላቸውን ጽኑና ጥልቅ ፍቅር የሚያሳዩበት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ለእመቤታችን ያላቸውን

ፍቅር በተለያዩ መጻሕፍት ላይ ገልጸዋል፡፡ በዚህ የዐሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የማይጾምና የማይቆርብ ሕፃን የለም፡፡ በፍልሰታ ጾም ሁሉም ምእመን የሚያሳየው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የቃል ኪዳን አገር መሆኗን ይመሰክራል፡፡ ይህን የተቀደሰ ሥርዓታችንን ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ደግሞ ልጆች አደራ አለባችሁ፡፡

## ተግባር

- በፍልሰታ ጾም በማስቀደስ ቅዱስ ቁርባን ተቀበሉ፡፡

www.zeorthodox.org

# ዋቢ መጻሕፍት

- ሃብተማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም
- ሃይማኖተ አበው፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም
- አባ መልከ ጼደቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።
- አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1974 ዓ.ም።
- ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓት አምልኮና የውጭ ግኙነት፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም.
- ሊቃውንት ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም.
- ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።
- መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፣ መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1989 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም።
- መጽሐፈ ስንክሳር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም
- መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም
- ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
- ዳኛቸው ካሳሁን (መልአከ ሰላም)፣ ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር፣ አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2003 ዓ.ም
- ደረጀ ጅማ (መጋቤ አእላፍ)፣ ምን ያስጨንቃችኋል ክፍል ፩፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም።

www.zeorthodox.org

- መጽሐፍ ቅዱስ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም
- ሐረገ ወይን ቸርነት፣ ሴትና አህያ፣ አዲስ አበባ፣ 2005 ዓ.ም።
- ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል (ዶ/ር)፣ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2000 ዓ.ም
- ኅሩይ ኤርምያስ (መምህር)፣ መዝገበ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ 2002 ዓ.ም
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ 1996 ዓ.ም።
- ቸርነት አበበ (መምህሩ)፣ የመጽሐፍ ቅድስ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም
- H.G. Bishop Moussa@ The Characteristics of Orthodox Teaching@ Bishopric of Youth@ Harmony Press, 2007.
- H.G. Bishop Mouusa, An Introduction to the New Testament, Bishopric of youth, Dar EL Geel Press, 2001.
- H.G. Bishop Raphail, The Meaning of Miracles, Bishopirc of Youth, 2010.
- Sunday School Curriculum, Grade 1 to Grade 12. The Coptic Orthodox Diocese of The Southern USA.
- Sunday School Lessons, Class 1 to Class 10, E.O.T.C Latin America Diocese.

www.zeorthodox.org